# ሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# “ፎክሎራዊ ፋይዳ በተመረጡ 3 ትውፊታዊ ተውኔቶች ማሳያነት”

በ


ንጉሥ ባይሌ


በ ፎክሎርእና ስነጽሁፍ ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሀምሌ፣ 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ዩኒቨርሲቲ

# “ፎክሎራዊ ፋይዳ በተመረጡ 3 ትውፊታዊ ተውኔቶች ማሳያነት”

በ

ንጉሥ ባይሌ

በ ፎክሎርእና ስነጽሁፍ ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

አማካሪ

የወንድወሰን አውላቸው (ዶ\ር)

## ሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

ሀምሌ፣ 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂውማኒቲስ ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


## የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# ፎክሎራዊ ፋይዳ በተመረጡ 3 ትውፊታዊ ተውኔቶች ማሳያነት


በ

ንጉሥ ባይሌ


የፈተና ቦርድ አባላት

| <u>የአማካሪ ሥም</u> | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| ዶ/ር የወንድወሰን አውላቸው | ________________ | ____________ |
| <u>የውጭ ፈታኝ</u> | | |
| የውጭ ፈታኝ ________________ | ________________ | ____________ |
| የውጭ ፈታኝ ስም____________ | ________________ | ____________ |


መጋቢት፣ 2017 ዓ/ም

አዲስ አበባ

# ምስጋና

በመጀመሪያ ‹‹ምስጋና በሰማይ ለእግዚአብሔር ይሁን በምድርም ላይ ሰላም ለሰውም እርሱ በሚፈቅደው››

በመቀጠል ‹‹ቅድስት ሆይ ብፅዕት ነሽ የተመሰገንሽና የተባረክሽ ነሽ…››

ይህን ፅሁፍ በማዘጋጅበት ጊዜ ከርዕሱ ጀምሮ ሀሳብህን በማካፈል፤ ስህተቶችን በማረምና በማስተካከል ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ውድ ጊዜህን ሰውተህ ያማከርከኝ ዶ/ር የወንድወሰን አውላቸው ስለ መልካምነትህ ቸሩ አምላክ መልካሙን ሁሉ ያድርግልህ፡፡

ትምህርቴን ጀምሬ እስክጨርስ ያለምንም ችግር እንድማር በሞራልም ሆነ በገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ከአጠገቤ ሆናችሁ ያበረታታችሁኝ አባቴ አቶ ባይሌ ሽቴ፣ እናቴ ወ/ሮ ህብስቴ ሽቴ፣ ታላቅ ወንድሜ ስሜነህ ባይሌ፣ታናሼ አብርሃም ባይሌ፣ራሔል ባይሌ እግዚአብሔር እድሜና ጤና ይስጥልኝ፡፡ ቀሪ ዘመናችሁንም ፈጣሪ በነገር ሁሉ አብዝቶ ይባርክ፡፡

እንዲሁም በሀሳብ እና በሞራል ጓደኛዬ አማኑኤል የሽወንድ፣የማታወርቅ ታደሰ፣ምትኩ በቀለ የተመኛችሁት ሁሉ ይሳካላችሁ ዘንድ ከልብ እመኛለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከመጀመሪያው ረቂቅ ጀምሮ የሚያስፈልገኝን በመተባበር ከጎኔ ላልተለያችሁኝ እጩ ዶ/ር መሰረት አሰፋ ፣ ዶ/ር ዳዊት አሞኘ፣ እጩ ዶ/ር ቴዎድሮስ ይደግ እና ዶ/ር መኩሪያ የእናንተ ሀሳብ እና አበርክቶ ትልቅ ነውና ምስጋናዬ ባላችሁበት ይድረስ፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት "ምስጢሩ" (2011 ዓ.ም)፣ "ተጠየቅ" (2013 ዓ.ም) እና ሽምጋይ" (2015 ዓ.ም) በተሰኙ ትውፊታዊ ተውኔቶች ውስጥ የሚገኙ የፎክሎራዊ ጉዳዮችን በመለዬት ፋይዳቸውን የመተንተን አላማ ይዞ የተሰራ ነው። ይህንንም ለማሳካት ተውኔቶቹን በቀዳማይ ምንጭነት፤ ከተለያዩ ቤተ-መጽሀፍት፣ የምርምር ተቋማት እና ድረ-ገጾች ላይ ተገኙትን ንደፈ-ሀሳብ እና ጽነሰ-ሀሳሳቦች የያዙ ጽሁፎችን በካልዓይ ምንጭነት ተጠቅሟል።እነዚህን መረጃዎችንም የሰነድ ትንተና (Textual analysis) የመረጃ አተናተን ዘዴን ጥቅም ላይ በማዋልጥናቱን አካሂዷል። ትንታነው ሲደረግም ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብን (Functional theory) ማሳያ በማድረግ ነው። በትንተናው መሰረትም ማዎቅ ተችሏል። በ"ሽምጋይ" ተውኔት ወስጥ በፊውዳሉ እና በሰራተኛው መደብ መካከል የሚታዩ የአኗኗር እሴቶችን እና ልማዶችን መመልከት የሚቻል ሲሆን "ተጠየቅ" በተሰኘው ተውኔትም ባህላዊ የእርቅ ሥነ-ሥርዓት የተውኔቱ ማዕከላዊ ሀሳብ ሆኖ ቀርቧል። ከዚህ በተጨማሪም "ምስጢሩ" በተሰኘው ተውኔት ደግሞ በተውኔቱ ውስጥ የተጠቀሰው ወንጀለኛን ለመለየት የሚጠቀምበት "አውጫጭኝ" ተብሎ የሚታወቀው ባህላዊ የወንጀለኛ ምርመራ ዘዴ ለተውኔቱ ዋና ጭብጥነት ቀርቧል። በተውኔቶቹ ውስጥ የቀረቡት የተለያዩ ባህላዊ ሥርዓቶች፣ ልማዶች፣ እምነቶች እና አስተሳሰቦች ግልጽ እና አዝናኝ በሆነ ኪነ-ጥበባዊ በሆነ መንገድ በመቅረባቸው ፎክሎራዊ ጉዳዩን በቀላሉ ለመረዳት ያስችላሉ። ይህ አቀራረብም ፎክሎርን መሰረት አድርገው የሚሰሩ ተውኔቶች የአንድን ሀገር ባህላዊ እሴቶች፣ ታሪክና ማኅበራዊ እምነቶችን ለማሳወቅ፣ ለመጠበቅና ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ የራሳቸውን ሚና እንደሚጫወቱ በጥናቱ ለመገንዘብ ተችሏል። ከዚህም በተጨማሪ፣ እነዚህ ተውኔቶች በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ አስተያየት በመስጠት፣ በትውልዶች መካከል ግንኙነት እንዲፈጠር፣ ማህበራዊ ግንዛቤ እንዲያድግ እና ለመዝናኛነት እንደሚያገለግሉ ጥናቱ አረጋግጧል። ይህ ጥናት ለቀጣይ ተመራማሪዎች በኢትዮጵያ ፎክሎርና ትውፊታዊ ቴአትርን በየበልጥ ለማስተዋወቅ የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል።

# ማውጫ

ምስጋና ........ II
አጠቃሎ ........ IIII
ማውጫ ........ II
ምዕራፍ አንድ ........ 1
. መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 2
1.3 የጥናት አላማ ........ 3
1.3.1 ንዑሳን ዓላማዎች ........ 3
1.4. የምርምር ጥያቄዎች ........ 4
1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 4
1.6. የጥናቱ ወሰን ........ 4
1.7 የጥናቱ ዘዴ ........ 5
1.7.1 የመረጃ ምንጮች ........ 5
1.7.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........ 5
1.7.3 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ........ 6
ምዕራፍ ሁለት ........ 8
. ክለሳ ድርሳናት ........ 8
2.1 ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝት ........ 8
2.1.1. የፎክሎር ምንነት ........ 8
2.1.2 የፎክሎር ምደባ ........ 10
2.1.3 .ፎክሎርና ቴአትር ........ 12
2.2.ንድፈ ሀሳባዊማህቀፍ ........ 15
2.2.1 ተምሳሌታዊ ንድፈ ሀሳብ ........ 15
2.2.2 አውዳዊ ንድፈ ሀሳብ ........ 16
2.2.3 የክዋኔ ቲዎሪ ........ 19
2.2.4 የፎክሎር ዳያክሮኒክና ሲንክሮኒክ ንድፈ ሀሳብ ........ 21
2.2.5 የሐይማኖት ንድፈ ሀሳብ ........ 21
2.2.6 የመሠረታዊ ፍላጎት ንድፈ ሀሳብ ........ 22
2.2.7 የማህበረሰብ እዉቀት አዋቃሪያን ንድፈ ሀሳብ ........ 23
2.2.8 ተግባራዊ ንድፈ-ሀሳብ (Fuctional Thory) ........ 24
2.3 የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ........ 25
ምዕራፍ ሦስት ........ 33
. የመረጃ ትንተና ........ 33
3.1 የተውኔቶቹ አህጽሮተ ታሪክ (Synopsis) ........ 33

3.1.1 “ምስጢሩ” ..... 33
3.1.2 “ሽምጋይ” ..... 34
3.1.3 “ተጠየቅ” ..... 34
3.2 የፎክሎራዊ ጉዳዩ ማኅበራዊና ሀገራዊ ፋይዳ ..... 35
3.2.1 የ“ምስጢሩ” ተውኔት ፎክሎራዊ አውድ ትንተና ..... 36
3.2.1.1 ፍቻዊ አውድ ..... 37
3.2.1.2 ተቋማዊ አውድ ..... 38
3.2.1.3 የማኅበረሰቡ የተግባቦት ሂደት አውድ ..... 39
3.2.1.4 ማኅበራዊ መሰረት ..... 39
3.2.1.5 ግለሰባዊ አውድ ..... 42
3.2.1.6 ሁኔታዊ አውድ ..... 44
3.3 የፎክሎራዊ ጉዳዩ (የ“አውጫጭኝ”) ማህበራዊና ሀገራዊ ፋይዳ ..... 45
3.3.1 የ“ተጠየቅ” ተውኔት ፎክሎራዊ አውድ ትንተና ..... 46
3.3.1.1 ፍቻዊ አውድ ..... 47
3.3.1.2 ተቋማዊ አውድ ..... 49
3.3.1.3 የማኅበረሰቡ የተግባቦት ሂደት አውድ ..... 50
3.3.1.4 ማኅበራዊ መሰረት ..... 51
3.3.1.5 ግለሰባዊ አውድ ..... 52
3.3.1.6 ሁኔታዊ አውድ ..... 54
3.4 የፎክሎራዊ ጉዳዩ ማኅበራዊና ሀገራዊ ፋይዳ ..... 56
3.4.1. የ“ሽምጋይ” ተውኔት ፎክሎራዊ አውድ ትንተና ..... 58
3.4.1.1. ፍቻዊ አውድ ..... 58
3.4.1.2. ተቋማዊ አውድ ..... 60
3.4.1.3. የማኅበረሰቡ የተግባቦት ሂደት አውድ ..... 61
3.4.1.4. ማኅበራዊ መሰረት ..... 62
3.4.1.5. ግለሰባዊ አውድ ..... 63
3.4.1.6. ሁኔታዊ አውድ ..... 63
3.5 የፎክሎራዊ ጉዳዩ (የሽምግልና) ማኅበራዊና ሀገራዊ ፋይዳ ..... 64
ምዕራፍ አራት ..... 66
4. ማጠቃለያ እና መደምደሚያ ..... 66
ዋቢ ፅሑፎች ..... 68
አባሪዎች ..... 73

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

የአንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ አቀራረብ በሚከውነው ማህበረሰብ ማህበራዊ ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶች እንዲሁም እንደ ከዋኙና ተሳታፊው አቅም ይለያያል፡፡

በዚህ ምክንያት መልዕክቱም ስለሚለያይ የክዋኔው ደረጃ በሚቀርብበት አጋጣሚ ይወሰናል፡፡

የከዋኙና የተሳታፊው ጾታ፣ እድሜ፣የእውቀት ደረጃ፣ ክዋኔውን ለመከወን የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፣ ጉዳዩ የሚቀርብበት ወቅትና ጊዜ፣ እንዲሁም የፎክሎራዊ ጉዳዩ ዓይነት፣ ጭብጥና የአቀራረብ ስልት ሁሉ የክዋኔው አካል በመሆናቸው ለሚከወኑበት አጋጣሚ የሚመጥኑ ሆነው መቅረብ አለባቸው::

እነዚህን ጉዳዮች በደንብ ለመረዳት ማህበረሰቡ ፎክሎራዊ ጉዳዩን እንዴት እንደሚተርት፡ እንደሚያዜምና እንደሚናገር መመርመር ተገቢ ነው:: በመሆኑም ክዋኔ እንድ ማህበረሰብ በፈጠረው ማህበረ-ባህላዊ አውድ ውስጥ ባህሉን፡ እሴቱንና አስተሳሰቡን በድርጊት የሚገለጽበት ዘዴ ነው (Ben-Amos፣ 1993፣ 223) የአንድን ፎክሎራዊ ጉዳይ ክዋኔ ለማጥናት ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ሁለት መሰረታዊ አተያዮች እንዳሉ Bauman(1992፣ 5) ጠቁመዋል፡፡ የመጀመሪያው ማህበረሰቡ ጉዳዩን የሚያከናውነው ተስማምቶ ባዋቀረው ስርዓትና ደንብ መሰረት በመሆኑ ታዳሚው አዳዲስ ፎክሎሮችን የመፍጠር እድል ሊኖረው እንደሚችል የሚያመለክት ሀሳብ ሲኖረው፤ ሁለተኛው ደግሞ ከዋኙ በተሳታፊዎች ብሎም በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ የሚጠቀመው ቋንቋ፡ የአነጋገር ለዛ እና የአከዋወን ሂደት ሳቢ እና እንዳስፈላጊነቱ አሳታፊ መሆን እንዳለበት የሚያመለክት ሀሳብ አለው፡፡ ይህ ጥናትም ከክዋኔ ጥበባት መካከል አንዱ የሆነው የቴአትር ጥበብ ላይ መሰረት አድረጎ የተሰራ ነው፡፡ በዚህም መሰረት "ምስጢሩ" የተሰኘ በ 2011 ዓ.ም አና ሽምጋይ" ተብሎ የሚጠራ 2015 ዓ.ም በኢትዮጵያ በብሄራዊ ቴአትርእና የቀረቡ፤ እንዲሁም "ተጠየቅ" የተሰኘ በ2013 ዓ.ም በሀገር ፍቅር ቴአትር የቀረቡ ትውፊታዊ ተውኔቶችን ፎክሎዊ ይዘት በመለዩት ፋይዳቸውን የመተንተን አላማ ይዞ ተሰርቷል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ፎክሎር ዘርፈ ብዙ ከሆኑ የሙያ መስኮች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ዝምድና ያለው በተለያዩ የስምምነት መስኮች /ሳይንሳዊመስኮች/መሀል አብረው የሚከወኑሰራ ወይም ጥናት የሆነ ዘርፍ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ከእነዚህ ዝምድና ከሚፈጥርባቸው ሙያዎች አልያም የሙያ መስኮች መካከል ደግሞ ቴአትር አንዱ እና ዋነኛው ነው፡፡ በቴአትር እና በፎክሎር መካከል ስላለው ዝምድና ለማስረዳት የቴአትርን አጀማመር መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ ወሰን ባዩ የተባሉ አጥኚ "በኢትዮጵያ ቴአትር የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ፋይዳ በተመረጡ ተውነቶች ማሳያነት" በሚል ርእስ (2010 ዓ.ም) ባደረገው ጥናት ስለ ቴአትር አጀማመር ሲያወሳ ቴአትር በርግጥ በዚህ ግዜ ተጀመረ ብሎ በርግጠኝነት መናገር ባይቻልም ከጥንታዊያን ማህበረሰቦች የአምልኮ ስርአት እና ከበራ ጋር የሚገናኝ ስለመሆኑ ይገልፃሉ፡፡ ከበራ ደግሞ የፎክሎር ዋነኛ ማጠንጠኛ መባያ ጉዳይ ከሆኑት መካከል ተጠቃሽ ነው፡፡

ቴአትር እና ፎክሎር ከመነሻው ጅምሮ ይህንን ያህል ቁርኝት ያላቸው ዘርፎች መሆናቸው እሙን ነው፡፡ አጥኒው ይህንን ጥናት ለማድረግ ሲነሳ በርእሰ ጉዳዩ ዙሪያ የተደረጉ የምርምር ስራዎችን ለመመልከት ሙከራ ያደረገ ሲሆን ተያያዥነት ያላቸውን ጥቂት የምርምር ስራዎች ማግኘት ችሏል፡፡ እነዚህም ማርታ ንጉሴ፣ "የሰላሌ አካባቢ የጉማ ሥርዓት ክዋኔዎችና ተውኔታዊ አላባዎች" (1998 ዓ.ም)፣ ተመስገን ፋናዬ፣ "የዛር ትውፊትና በውስጡ የሚገኙ የቴአትራዊ አላባውያን በራያና ቆቦ አካባቢ" (1995 ዓ.ም)፣ እንግዳ ሐብቴ፣ "የሶዶ ብሄረሰብ ትውፊታዊ ድራማ" (1984 ዓ.ም)፣ እና በላይ መኮንን፣ "የደቡብ ንግስት ተውኔት ከአፈ-ታሪኩ አንፃር" (1999 ዓ.ም) ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር ፍፁም የማይገኛኙ ናቸው ማለት ባይቻልም በእጅጉ ልዩነት ያላቸው ጥናቶች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ከዘርፉ ስፋት እና ጥልቀት አንፀርም በቂ የሚባሉ አይደሉም፡፡ በዚህ ጥናት እና ከላይ በተጠቀሱት የምርምር ስራዎች መካከል ያለው ተመሳስሎ እና ልዩነት ከታች ተዛማጅ ፅሁፎች በሚቃኙበት ክፍል ቀርቧል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት እንዲዘጋጅ ምክንያት ከሆኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ በዘርፉ በቂ ምርምር ያልተደረገ መሆኑ በመስኩ ያለውን የእውቀት ክፍተት መሙላት አንድ አነሳሽ ምክንያት ነው፡፡

አጥኚው የቴአትር ባለሙያ መሆኑ እና ዝርዝር ሙያዊ ጉዳዮችን ጭምር በቅርበት መከታተል መቻሉ እንዲሁም በቴአተሮች ላይም ተሳታፊ በመሆን ባህሉን በቅርበት የማወቅ እድል ያለው

መሆኑ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ጥናት የማድረግ ፍላጎቱ እንዲጨምር፡፡ ይህ በተለይም ለቴአትር ሙያ ቅርብ የሆነ ሰው የመሆን ጉዳይ በዘርፉ ምርምር ለማድረግ መነሳሳቱን ከመፍጠርም ባሻገር አጥኚው በዚህ የምርምር ርእስ ይበልጥ ተገቢ ይበልጥ ተገቢ የሆነ ሰው እንዲሆንም ጭምር ያደርገዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በቴአትር ውስጥ ያለን ዘርፈ ብዙ ፎክሎራዊ ፋይዳ ሳይንሳዊ በሆነ ምርምር የማሳየት እና ሰንዶ የማስቀመጥ ዝንባሌም ሌላው ለዚህ ጥናት መሰራት አንድ ምክንያት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሀገር በቀል እውቀት ተጠቃሚ እንዲሆን እና ለሌላው የማህረሰብ ክፍልም መተዋወቅ እና ተደራሽ መሆን ይችል ዘንድ እንቅስቃሴዎች ሲደረጉ አይስተዋልም፡፡ ማህበረሰቡ በአካባቢያቸው ውስጥ ሰው ሲገደል ቤት ሲቃጠል እህል ሲወድም ባልና ሚስት ሲጣሉ እንዲሁም የተለያዩ ማህበራዊ እክል ሲገጥሟቸው ፍትህ ለማስፈን የሚደረገው ክዋኔ ለማህበረሰቡ ያለውን እሴት እንዲሁም ፎክሎራዊ ፋይዳና ትውፊት በሳይንሳዊ ምርምር በመታገዝ ሰንዶ ማስቀረት ሌላኛው የዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያት ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ አላማ

ይህ ጥናት “ምስጢሩ”፣ “ተጠየቅ” እና “ሽምጋይ” በተሰኙ ትዉፊታዊ ተውኔቶች ውስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በመለዬት ፋይዳቸውን መተንተን ዋና አላማ ያለው ሲሆን፤ይህንን ዋና አላማ ከግብ ለማድረስ የሚያግዙ የሚከተሉት ንዑሳን አላማዎችም አሉት፡፡

### 1.3.1 ንዑሳን ዓላማዎች

1. በተውኔቶቹ ውስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን መለየት፣
2. የተውኔቶቹ አቀራረብ በፊክሎራዊ ክዋኔው ያላቸውን ግንኙነት ማሳዬት፣
3. በተውኔቶቹ ጭብጥ ውስጥ የፎክሎራዊ ጉዳዩ ሚና መመርመር፣
4. በተውኔቶቹ ውስጥ የተነሱት ፎክሎራዊ ጉዳዮች ጥቅም ላይ የሚውሉበትን መንገድ ወይም አውድ መመልከት

## 1.4. የምርምር ጥያቄዎች

ጥናቱ ከላይ የተቀመጡትን አላማዎች ከግብ ለማድረስ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል፡፡

1. "ምስጢሩ"፣ "ተጠየቅ"እና ሽምጋይ" ትውፊታዊ ቴአትሮች ላይ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?

2. በተውኔቶቹ ላይ የተነሱት ፎክሎራዊ ጉዳዮች ፋይዳቸው ምንድን ነው?

3. የተውኔቶቹ አቀራረብ በፊክሎራዊ ክዋኔው ውስጥ ያላቸው ጉዳይ ምንድነው?

4. በተውኔቶቹ ጭብጥ ውስጥ ፎክሎራዊ ጉዳዩ ምንድነው?

### 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት የሚከተሉት ፋይዳዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

1. ፎክሎራዊ ጉዳየችን መሰረት አድረገው የሚሰሩ ተውኔቶች ያላቸውን ፋይዳ ለመገንዘብ አስረጂ ሆኖ ይቀርባል፡፡

2. በተውኔቶቹ ውስጥ የሚታዩ ፎክሎራዊ ሥርዓቶችና ልማዶች ቅርጽና ይዘት ምን እንደሚመስል ሳይንሳዊ ሆነ መንገድ በመመርመር ግኝቱን ያስቀምጣል፡፡

3. ፎክሎራዊ ጉዳዮች በተለይም በተውኔት ውስጥ ምን ሚና እንዳላቸው እና በምን መንገድ ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ያሳያል፡፡

4. በመስኩ ያለውን የእውቀት ክፍተት ይሞላል (Identifying the gap):::

5. ለሌሎች አጥኚዎች እንደ መረጃ ምንጭነት ያገለግላል፡፡

6. ለአዲስ መረጃ እና ለመስኩ ማስፋፋት (New knowledge) መረጃ የመስጠት አቅም አለው፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት "ምስጢሩ" (2011 ዓ.ም)፣ "ተጠየቅ" (2013 ዓ.ም) እና ሽምጋይ" (2015 ዓ.ም) የተሰኙ ትውፊታዊ ተውኔቶች ውስጥ የሚገኙ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በመለዩት ፋይዳቸውን መተንተን ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡

## 1.7 የጥናቱ ዘዴ

### 1.7.1 የመረጃ ምንጮች

በዚህ ጥናት ሂደት ላይ የተጠቀሰው መረጃ ምንጮች በተለምዶ ከመስክ ውስጥ በቀጥታ ተሰብስበው የታወቁ፣ ከቤተ-መጽሐፍት እና ከድረ-ገጾች ከተዘጋጀ ምርምር፣ መጽሐፍት እና የታተመ ጽሁፍ ሰነዶች ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት ሂደት ላይ የተጠቀሰው መረጃ

በብሔራዊ ቴአትር፡ በሀገር ፍቅር ቴአትር ቤቶች ተሰብስበው የተቀረቡ ሦስት ተውኔቶችን ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

እንዲሁም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኬነዲ ቤተ መጽሀፍ፣ ከየኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም፣ ከብሔራዊ ቤተ መፅሐፍትና ቤተ መዛግብት ኤጀንሲ እና ከተለያዩ የኢንተርኔት ድረ-ገጾች የተሰበሰቡ መጽሐፍት፣ ጥናታዊ ሥራዎች፣ መጽሔቶች እና አርቲክሎችን ይጠቀማሉ፡፡ ይህ የመረጃ ምንጮች ስብስብ በጥናቱ ላይ የተደረገውን የሳይንሳዊነት ትክክለኛነትና ውሳኔ እንዲጠናከር ያግዛል፡፡

### 1.7.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

በአንድ ጥናት ውስጥ የምርምር ችግሮችን መሠረት ያደረጉ የምርምር ጥያቄዎችን በመመለስ የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ እንደ ጥናቱ ባህርይ ልዩ ልዩ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም በዚህ ጥናት ውሰጥ ሥራ ላይ ሁለት ዘዴዎች ሲሆኑ እነሱም **ሰነድ ዳሰሳና ንባብ** ናቸው፡፡

**ሰነድ ዳሰሳ፡-**

ማለት ከጥናቱ ርዕሰ -ጉዳይ ጋር ተዛማጅ የሆኑናመረጃ ሊሰጡ የሚችሉትን የተለያዩ መጻህፍት ፓምፍሌቶች፣ ፖስተሮች፣ ጥራዞች፣ የተማሪ መጽሀፍት፣ መመሪያዎች ማዕቀፎች ፖሊሲዎች ስትራቴጅዎች ጋዜጠች፣ መጽሄቶች፣ የጥናትና ምርምር ጽሁፎች ወዘተ. ፍተሻ ማድረግ ማለት ነዉ የሰነድ ዳሰሳ ሊሰራ ከታሰበበትጊዜ ጀምሮ እስከ ጥናቱ ፍጻሜ ድረስ ባሉት ተግባራት ሁሉ የሚከወን የጥናትና ምርምር ሂደትና ተግባር በዚህ ጥናት የሰነድ ዳሰሳ ተግባራዊ የተደረገበት ሂደትም ይህን የተከተለ ነዉ፡፡

"**ፎክሎራዊ ፋይዳ በተመረጡ 3 ትውፊታዊ ተውኔቶች ማሳያነት**" የሚለው ጥናት በማእከላዊ አመራረት (qualitative approach) የተከናወነ ሲሆን፣ በእውቀታዊ ጥናት ሂደት ላይ በተከታታይ የተከተሉት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

1. **የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ** (Data Collection Methods)

- **. የማስተዋል እና የይዘት ትንተና** (Content Analysis) የተመረጡት "ምስጢሩ" (2011), "ተጠየቅ" (2013), እና "ሽምጋይ" (2015) ትውፊቶች በብሔራዊ ቤተ-ቴአትር የተቀረቡ ነበሩ። እነዚህ ተውኔቶች በመመልከት፣ ማዳመጥ፣ እና መተንተን በይዘታቸው ውስጥ ያሉ ፎክሎራዊ አካላት ተዘጋጁ።
- **በቃለ መጠይቅ** (Interview) ከተውኔቶቹ ምርቃኞች፣ ደራሲዎች፣ አርቲስቶች እና ባህላዊ አሳዋቂዎች ጋር በቀጥታ ቃለመጠይቅ ተነጋገሩ።
- **አይነት እይታ** (Observation) በተደረገ ተውኔት አቀራረብ የታየው ባህላዊ አካል፣ የዘፈን አንባቢዎች፣ ልብስ እና ሌሎች ዝርዝሮች ተመረመሩ።

2. **የተሰበሰበ መረጃ አይነት** (Types of Data Collected) **የአካላዊ ዝርዝር** (Primary Data) የተውኔቶቹ አቀራረብ ማየትና መተንተን የተጠቀሱ፣ በተመረጡ ሰዎች ላይ የተሰበሰበ መረጃ። በቃለመጠይቅ የተሰጡ መረጃዎች።

**የሁለተኛ አካላዊ መረጃ** (Secondary Data) የተፈለጉ ቴአትሮች ዝርዝር መጽሐፍት፣ የዚህ ዓይነት ጥናቶች፣ ማስታወቂያዎች እና ሰነዶች ናቸው።

### 1.7.3 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

የተቀመጠው ጥናት ስነ-ጽሑፋዊ መሆኑ ምክንያት በመሆኑ የምርምር መሠረታዊ ዘዴ አይነታዊነትን በመቀበል በቴክስት ትንተና (Textual Analysis) ትንተና ተደርጓል። በዚህ ሂደት ውስጥ የተሰበሰቡ መረጃዎች፣ መጽሐፍት፣ እና ተዛማጅ ጥናታዊ ሥራዎች ትንተና ተደርገዋል። በመረጃ ትንተና ላይ ተግባራዊ ቲዎሪ (Functional Theory) ነው። **This theory explores in depth the similar practices observed in both social and natural life, revealing the processes through which societies establish and maintain order and harmony.** *(Radcliffe-Brown, 1935: 394—397)*

/ይህ ቲዎሪ በማህበራዊ እና በስነ-ተፈጥሯዊ ህይወት ውስጥ የሚታዩ ተመሳሳይ ተግባራትን በጥልቀት በመተንተን ማህበረሰቡ የሚያሟሉትን ሂደቶች ይገልፃል፡፡ Radcliffe-Brown (1935: 394—397)/ በተግባራዊ ትንተና ዘዴው ላይ ተመስርቶ ፎክሎር እንደ ማህበረሰብ ህይወትን የሚያጠናክልና የሚያደርግ ተግባር መሆኑን ያብራል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ Bascom (1954: 344—346) ፎክሎርን ከሰው ህይወት ጋር በቀዳሚነት የተያያዘ መሆኑን ይገልፃል፡፡ ፎክሎር የማስተማር፣ የመዝናናት፣ የመማር እና ባህላዊ ማንነትን የማስጠበቅ ተግባር እንዳለው ያሳስባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ ተግባራዊ ቲዎሪው ማህበረሰብ በአንድነትና በየተዘረዘረ ክዋኔ ላይ ምን እየሠራ እንደሆነ ለማቅረብ ያግዛል፡፡ Okpewho (1992: 173) በተግባራዊ ቲዎሪ መንገድ በማህበረሰብ ውስጥ የሚካወኑ ነገሮች በእውነተኛው ማህበራዊ ተግባራቸውና በመመርመር እንደሚታወቁ ይገልፃል፡፡ ከፍተኛ ትክክለኛነትና በግልጽ ስርዓት የተዘጋጀ ይሆናል፡፡

ለመረጃ መተንተኛነት የሚያገለግለው ተግባራዊ ቲዎሪ ሲሆን በማህበራዊ ህይወትና በስነ-ተፈጥሯዊ ህይወት ውስጥ ያለውን ተመሳሳይነት ያንፀባርቃል። የአንድ ፍጡር መላ አካላት የሚፈጽሟቸው ተግባራት ተደምረው ፍጡሩን ሙሉና ህያው የሚያደርጉት ከሆነ የፎክሎር ክዋኔዎችም ተደምረው የከዋኙን ማህበረሰብ ህልውና ሙሉ የሚያደርጉ ተግባራዊ ፋይዳዎች አሏቸው (Radcliffe-Brown 1935: 394-397)። ፎክሎርና የፎክሎር ትርጉም ከሰው ጋር የተሳሰረ መሆኑንና ፎክሎር የማስተማር፣ የማዝናናት፣ የማስተላለፍ እና ባህላዊ ማንነትን የማስጠበቅ ተግባር እንዳለው Bascom (1954:344-346) ያስረዳል። ከዚያም በላይ የተግባራዊ ቲዮሪ እሳቤን ማወቅ አንድ የሰዎች ቡድን በአንድ ውስን ሁነትና ውስን ክዋኔ ውስጥ ምን እየሰራ እንደሆነ ለመረዳት ያግዘናል። ተግባራዊ ቲዮሪ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከወን ማንኛውም ነገር ያለውን ተግባርና አገልግሎት ለመመርመር ይረዳል (Okpewho (1992:173)።

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምእራፍ ስር የተካተቱት ጉዳዮች የዘርፉ ምሁራን ከጻፏቸው ውስጥ ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ ዋና ዋና ጽንሰ ሀሳቦች ምንነትና ጠቀሜታ ላይ ያተኮሩ ናቸው። ይህ ምእራፍ ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች አሉት። የመጀመሪያው የጥናቱ ጽንሰ ሀሳብ ማዕቀፍ ዳሰሳ የተደረገበት ሲሆን ከዚሁ አንጻር ስለ ፎክሎር ምንንትና ምደባ እንዲሁም የተለያዩ ብያኔዎች እና ማብራሪያዎችን የጥናቱ ንድፈ ሃሳባዊ ማእቀፍ በመሆን የሚቀርብበት ነው። የፎክሎር ምንነትና ሚና በሚመለከት በዘርፉ የሚካተቱ ዓይነቶች የተዘረዘሩበት እና የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ ባህላዊ ገጽታዎች በማንጸባረቁ ረገድ የፎክሎር ሚና የተብራራበት ነው።

## 2.1 ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝት

በዘህ ንዑስ ርዕስ ስር የተካተቱት ጉዳዮች ጥናቱ የሚከናወንበትን ሙያውን በተመለከተ የዘርፉ ምሁራን ከጻፏቸው ውስጥ ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ ዋና ዋና ጽንሰ ሀሳቦች ምንነትና ጠቀሜታ ላይ ያተኮሩ ናቸው። በመሆኑም ስለፎክሎር ምንነት እና ፋይዳ ሰለ ፎከሎር ምደባ ፣ ሰለ ተግባራዊ ፎክሎር፣ ስለ ስነቃል ምንነትና ፋይዳ፣ ስለ ሀገርሰባዊ ልማድ እና ሀገረሰባዊ እምነት ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር የምንመለከት ይሆናል።

### 2.1.1. የፎክሎር ምንነት

ፎክሎር የሚለው ቃልም ህዝብና ልማድ የሚሉ የሁለት ጽንሰ ሃሳባዊ ቃላት ውህድ ነው (Schoemaker 1990:3)። ህዝባዊ የሚለው ቃል ቡድናዊ የሆኑ ሰዎችን የያዘ አካል ሲሆን ልማድ ደግሞ በባህል ክፍል ውስጥ የሚመደብ ነው። የሰው ልጅ ማህበራዊ በመሆኑ እንደ ሰው ልጅነታችን ሁላችንም በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ተሳታፊዎች እንደሆን፤ ከዚህም የተነሳ አንዱ ከአንዱ ጋር መግባባትና ግንኙነት መፍጠር እንደሚችል ተጽፏል። ከዚህ አገላለጽ ጋር በሚስማማ ሁኔታ ፈቃደ (19982) "ፎክሎር ህይወት ስለሆነ" በግለሰብም ይሁን በማህበረሰብ ደረጃ የእለት ተእለት አኗኗር ውስጥ የሚከናወን ማንኛውም ነገር እንደሚያጠቃልል ያስረዳል። ከዚህ ገለፃ መነሻነት ፎክሎር የሚለው ቃል ማንኛውንም የሕዝብ ቡድን የሚመለከት ሆኖ ቢያንስ አንድ በጋራ የሚያገናኛቸው ጉዳይ ያላቸውን የኅብረተሰብ ክፍል የሚገልጽ መሆን

እንዳለበት እንረዳለን፡፡ በጋራ የሚያገናኛቸው ጉዳይ ትምህርት፣ ሥራ፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣...ወዘተ ሊሆን ይችላል (Dndes, 1965)፡፡ ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር ፎክሎር ማለት ጥበባዊ ተግባቦት ያላቸው የኅብረተሰብ ቡድን መሆኑንና በቡድኑ አባላት መካከል ያለው ግንኙነት ሰዎቹ የሚናገሩትን፣ የሚያደርጉትን፣ የሚሠሩትን ...ወዘተ ጉዳዮች የተመለከተ መሆኑን Ben- Amos (1971:13)" ፎክሎር የሚለው ቃል የፈጠረው ዊሊያም ጆን ቶምስ መሆኑን ተጽፎ ይገኛል (Schoemaker 199013 ፈቃደ 199172):

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ ፎክሎር የሚለውን ቃል ፈቃደ አዘዘ (2003) ለማስተማሪያነት (Steiner Mathisen, 1999:35) Dundes : ፎክ እና ሎር በማለት ቃሉን ለሁለት በመክፈል ብያኔ ይሰጣል፡፡ ይሄም "ፎክ (folk) አንድ የጋራ ነገር ያላቸው የትኛውንም የሰዎች ስብስብ ይመለከታል፡፡ "በማለት ሎር (lore) ን ደግሞ "የጋራ የሆነውና ያ የሚያገናኛቸዉ እውቀት ነው፤ የጋራ እውቀቱ ምንም ይሁን ምን ሎር ይባላል፡፡" በማለት የሚያገናቸው ዋናው ነገር የጋራ ልማድ (tradition) መሆኑን ይገልጻል፡፡ ባጭሩ ፍክሎርን የሁለት ክዋኔዎች መግለጫ አድርገን ልንወስደው እንችላለን፤ ሰዎች በዘልማድ (በባህል) የሚናገሩት እና ሰዎች በዘልማድ (በባህል) የሚተገብሩት የሰዎች መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ባህል ነው ማለት ይቻላል (ፍቃደ አዘዘ፣ 1996 V)፡፡ በሰነዱ ውስጥ "Intangible Cultural Heritage" ተብሎ የቀረበው ጽንሰ ሀሳብ የፎክሎርን ጽንሰ ሀሳብ የያዘ ነው፡፡ ከዚህ ጋር  የኢትዮጵያ የቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 209/92 የፎክሎርን ጽንሰ ሀሳብ ግዙፍነት ከሌላው የሰው ልጅ እውቀት አንጻር ይመለከተዋል፡፡

> "ግዙፍነት የሌለው ቅርስ ማለት በእጅ ለመዳሰስ የሚያዳግት ነገር ግን በዓይን ለማየት፡ በጆሮ ለመስማት የሚቻል ቅርስ ሲሆን የብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦች ልዩ ልዩ ትርዒትና ጨዋታ፣ ሥነ ቃል፣ የሃይማኖት፣ የእምነት፣ የጋብቻ፡ የሐዘን ሥነ-ስርዓት፡ ሙዚቃ፡ ድራማና ሌሎች ተመሳሳይ ባህላዊ እሴቶች፡ ወግና ልማድን ይጨምራል" በማለት ይተረጉመዋል፡፡

በዚህ ትርጉም መሠረት የማይዳሰስ ባህላዊ ቅርስ የሰው ልጅ ማህበራዊና ባህላዊ ክዋኔ ውጤት መሆኑን እንረዳለን፡፡ ፎክሎር አንድ ሕዝብ በማህበራዊና ባህላዊ ሕይወቱ ውስጥ ማሕበረሰቡ የሚገኝበትን ሁኔታ በማንጸባረቁ ረገድ የተለየ ሚና እንዳለው በርካታ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

Dundes, (1965) ፎክሎር ያለፈውን የሚያወሳ ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅ የእውቀት ምንጭ በመሆኑ በዕለታዊ የሰው ልጅ እንቅስቃሴ ውስጥ ወቅታዊ የትኩረት ጉዳዮችን በማሳየት ባህላዊና ሥነልቦናዊ ጠቀሜታዎች ያሉት በመሆኑ በጭንቀት ምክንያት ድብቅ የሆኑ ጉዳዮችን ሳይቀር ይፋ የማድረግ አቅም እንዳለው በፎክሎር ትንተናው ላይ ያብራራል። ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር ድብቅ ከሆኑት ጉዳዮች ውስጥ ዋናዉ ከወሲብ ጋር የተያያዙ ተግባራት ሲሆኑ ይህንንም አንድ ግለሰብ የሚማረዉ ከማህበረሰቡ መሆኑንና ለዚህም የቋንቋ ሚና ከፍተኛ መሆኑን Rosenthal (2006) Susan Moore & Doreen በሌላ አገላለጽ Ben-Amos, (1979) ፎክሎር ማህበረሰቡ በቋንቋው አማካይነት ባህላዊ እሴቶቹን የሚገልጽበት መስታወት ከመሆኑ አንጻር የማህበረሰቡ ማንነት መገለጫና በውስጡም በርካታ እሴቶችን ያካተተ መሆኑን ይናገራል። በመሆኑም ፎክሎር አገልግሎት ለሚሰጥበት ማህበረሰብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ንብረቱ እንደመሆኑ መጠን የሕዝቦችን ልማድ፣ ወግ፣ እምነት እና ጥበቦችን ያካተተ የባህል ዘርፍ መሆኑን ገልጿል።

### 2.1.2 የፎክሎር ምደባ

ፎክሎር እንደ ስርዓተ ባህል ለመቆጣጠርና ለማጥናት የሚደረገውን ስርዓተ ሥራ በተመለከተ፣ Dorson ፎክሎርን በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ሲያከፍል እና በመስኩ የሚፈጸም ምርምር በተደነገገ መልኩ እንዲሰራ የሚያበቃ መሆኑን ፈቃደ (1991: 2-4) ገልጿል። እነዚህ አራት ዋና ዋና ክፍሎች ስነ-ቃል፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት፣ ሀገረሰባዊ ልማድና ቁሳዊ ባህል ናቸው። ከሌላ በኩል ዩኔስኮም (UNESCO) ፎክሎርን እንደ "Intangible Cultural Heritage" በማቅረብ በአምስት ዋና ዋና ምድቦች እንዲመደብ ይገልጻል። እነዚህ ምድቦች የሀገረሰባዊ ቃላትና ልምዶች፣ የድራማና ዘፈኖች እና ዳንስ፣ ሀገረሰባዊ ልማድና ሥርዓቶች፣ ቁሳዊ ባህላዊ ዕቃዎች እና የተፈጥሮ እውቀትና ትግበራዎችን ያካትታሉ። ቢሆንም፣ የተፈጥሮ እውቀትና ትግበራ እሱ ብቻውን ምድብ በመሆን ሳይቆም፣ በሀገረሰባዊ ልማዶች ውስጥ እንደ አንድ አካል የሚተካ መሆኑ ይገልጻል። በዚህ ጥናት፣ በፈቃደ (1991: 2-4) ልክ ፎክሎር በአራት አበይት ዘርፎች እንደሚከፈል በተናገረው መሰረት እንመለከታለን።

1. **ስነ-ቃል (Oral Literature)** በዚህ ዘርፍ የሚተካው ፎክሎር ዓይነት ሰው ልጆች የውስጣዊ ስሜታቸውን፣ ፍላጎታቸውን፣ ችግራቸውን፣ ደስታና ሐዘናቸውን፣ ደግነትና ተግባራቸውን በቃል ማቅረብ የሚያሳይ ነው። ከዚህ የተነሱ ዓይነቶች ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ተረቶች፣ እንቆቅልሾች፣ ቀልዶች፣ አፈ-ታሪኮች እና በቃል የሚተካ ሌሎች ልቦናዊ ማቅረቦችን

ያካትታሉ። እነዚህ በተለያዩ የማህበረሰብ ቦታዎች በተለያዩ ሁኔታዎች የተሰጡ ሲሆኑ፣ በሕዝብ መካከል በትምህርት እና በሥርዓተ ህይወት ማህበራዊ ዘርፎች መሆናቸው ይገለጻል።

2. **ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት** (Traditional Performing Arts) ይህ ዘርፍ የፎክሎር ሀቅ በሙዚቃ፣ በዳንስ፣ በድራማ (ቲያትር) የሚገለጽ ነው። **ሀገረሰባዊ ሙዚቃ**፡ በባህላዊ መሳሪያዎች ላይ በምትና በትንፋሽ ተመሳሳይ የሚደረግ እና ባህላዊ ጉባኤዎችን የሚሰማና የሚያቀርብ ዘፈን ነው። **ዳንስ**፡ የሰውነት አካላትን በተለያዩ እንቅስቃሴዎች እንደ ጭፈራ፣ እስክስታ፣ ዳንኪራ ወዘተ የሚያቀርብ ነው። **ሀገረሰባዊ ድራማ (ቲያትር)**፡ የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ትውልድ ህይወትን በትዕይንት ሁኔታ የሚያበራ ነው። ተጨማሪ ሆኖ፣ እነዚህ ሦስት በተያያዘ መልኩ አንዱ ከአንዱ ጋር በተዋሃዱ እንዲቀሩ ይታወቃል።

3. **ሀገረሰባዊ ልማድ** (Traditional Social Practices) ይህ ዘርፍ የሰው ልጅ በግልና በጋራ በሚከናወኑ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ እና ኢኮኖሚያዊ ድርጊቶችን ይዞታ ያደርጋል። እነዚህ ልማዶች የህይወት ዑደቶችን (ልደት፣ ጋብቻ፣ ሞት)፣ የእምነትና የማህበራዊ ደረጃ ትውልድን፣ የስም አወጣጥና የአካል ሥርዓት፣ ባህላዊ ምግብ አዘገጃጀት እና ሌሎችም ልማዶችን ያካትታሉ።

4. **ቁሳዊ ባህል** (Traditional Crafts) ቁሳዊ ባህል በሰው ልጅ በልምድና በምልክት ማስተላለፍ የሚያገኘው የአገልግሎት እና የምግባር ክህሎት ነው። ይህ በእንጨት፣ ቆዳ፣ ሸክላ፣ ሳር፣ ብረት እና ሌሎች የተደረጉ ዕቃዎችን እና የጥበብ ሥራዎችን ይጨምራል። እነዚህ ዕቃዎች የተለያዩ ማህበረሰቦች በቀናቸው ህይወት ውስጥ ትልቅ ሚና ይኖራቸዋል። እንመለከታለን።

ስለዚህ ፎክሎር ኢመደበኛ በሆነ መንገድ አለምን የምናውቅበት እውቀት ጭምርነው። እኛነታችንን፣ ማህበረሰባችንን፣ እምነታችንን፣ ባህላችንን እና ልማዶቻችንን በቃላት፣ በሙዚቃ፣ በልማድ፣ በድርጊት፣ በባህሪ እና በቁስ የምንገልጽበት ፈጠራ ነው።

### 2.1.3. ፎክሎርና ቴአትር

ፎክሎር በትውፊት ውስጥ አንድ መሳሪያ ነው። የትውፊት ሐሳቦች ፎክሎርን እንደ መዋቅር አካላት ታውቃሉ። ማለትም፣ የባህላዊ ሐሳብ፣ ልምድ በፎክሎር ውስጥ የተስተካከለ ነው። እነዚህ ሁሉ በቴአትራዊ ትውፊት ውስጥ በማዕከላዊነት ይገኛሉ።

በሁለቱ  መካከል ያለዉን ቁርኝት ለመረዳት ወደ ኋላ መለስ ብሎ የቴአትር አጀማመርና እድገትን ማጥናት ያስፈልጋል።

ስለ ቴአትር አጀማመርሁኔታ እርግጠኛ የሆነ ማስረጃ ባይገኝም፣ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ከሆኑ የአምልኮ ሥርአቶች ሳይመነጭ እንዳልቀረ እና መነሻውም ከወደ ግሪክ እንደሆነ በዘርፉ የተደረጉ የተለያዩ ጥናትና ምርምሮች ይጠቁማሉ። ጥቂቶችን ለመጥቀስ ያህልም፦ "The origins of theater go back far into the past to the religious rites of the earliest communities."1 ይህ ማለት የቴአትር አጀማር ከጥንት ማህበረሰቦች ሃይማኖት እና የአምልኮ ሥርአቶች ጋር እንደሚያያዝ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ አጀማመሩን በተመለከተ እንደሚከተለውም ይባላል። ይኸውም፡

> **- no one knows exactly how theater originated. We know where it emerged. In Greece in fifth century B.C.; in India in the fourth century after Christ, and -after being dormant in western civilization- again in Europe in the middle ages.?2**

---

1 Hartnoll, Phyllis.A Concis History of the Theatre. London:Thames and Husson,1968, p. 7.

2 Edwin, Wilson and Alvin, Goldfarb, Living Theatre: An Introduciton to Theatre Hisotry, 2nd ed. 1994, p. 10.

የቴአትር አጀማር ከጥንት ማህበረሰቦች ሃይማኖት እና የአምልኮ ሥርአቶች ጋር እንደሚያያዝ ነው።ቴአትር እንዴት እንደተጀመረ ርግጠኛውን የሚያውቅ የለም። የሚታወቀው ነገር ቢኖር፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ5ኛው ክፍለ ዘመን በግሪክ፡ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ4ኛው ክፍለ ዘመን በህንድ እና በምዕራቡ ዓለም የስልጣኔ ዘመን ወቅት (ተደብቆ የቆየ ቢሆንም)፣ በመካከላኛው ዘመን ወቅት በአውሮፓ፣ የተከሰተ ስለመሆኑ ነው።

ሌላው ስለ ቴአትር አጀማመሩ አስመልክቶ የቀረበው ሀሳብ ደግሞ መሰረቱ ሀይማኖታዊና መንፈሳዊ ከበራዎች እንደሆኑ የሚያነሱ አሉ  ሀይማኖታዊና መንፈሳዊ ከበራዎች ለቴአትር መጀመርቀደምት መሠረቶች ስለመሆናቸው ብዙዎቹ የሚከራከሩ ሲሆን፣ ማስረጃቸው ደግሞ፤ የግሪክ ቴአትር ታሪክ ከዳይኖስስ ክብረ በዓል፣የሮማ ቴአትር ታሪክ ከጁቲር (ዚዩስ) ፌስቲቫል እና የመካከለኛው ዘመን ቴአትር ታሪክ ከሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ጋር የተገናኘ ነው የሚል ነው።

የቴአትር መነሻ በጥንታዊ ማህበረሰቦች ሃይማኖታዊ እና አምልኮ ሥርአቶች ግንኙነት እንዳለው ብዙ ምርምር ያመለከተዋል። ምንም እንኳን ትክክለኛ እና ግልጽ ማስረጃ እንዳልተገኘ፣ ቴአትሩ ከሃይማኖታዊ እና መንፈሳዊ ሥርአቶች ሳይመነጭ እንዳልቀረ ግልጽ ነው። ተጨማሪም፣ ቴአትር በአምስተኛው ክፍለ ዘመን በግሪክ፣ በአራተኛው ክፍለ ዘመን ዲዮን በህንድ፣ እና በመካከለኛው ዘመን ዳግም በአውሮፓ የተነሳ መሆኑ ታወቀ። ፎክሎር በማህበረሰብ ውስጥ አስፈላጊ ተግባራዊ ሚና አለው። Bascom (1954) እንደሚገልጽ፣ ፎክሎር የተቀበለውን ባህላዊ ደንብ ለማስከበር እና ከትውልድ ወደ ትውልድ ለመስተላለፍ በትምህርት ተግባሩን ይፈጽማል።  ... no one knows exactly how theater originated. We know where it emerged. In Greece in fifth century B.C.; in India in the fourth century after Christ, and - after being dormant in western civilization-again in Europe in the middle ages[1]

ፎክሎራዊ ገጽታ በሚመለከት Bascom (1954) እንደሚከተለው ተገልጿል።

---

[1] 1 Hartnoll, Phyllis. A Concis History of the Theatre. London: Thames and Husson, 1968, p. 7.
2 Edwin, Wilson and Alvin, Goldfarb, Living Theatre: An Introduciton to Theatre Hisotry, 2nd ed. 1994, p. 10.

The functions of folklore can be classified differently; Folklore operates within a society to insure conformity to the accepted cultural norms, and continuity from generation to generation through its role in education and the extent to which it mirrors culture. To the extent inwhich folklore contrasts with the accepted norms and offers socially acceptable forms of release through amusement or humor and through creative imagination and fantasy, it tends to preserve the institutions from direct attack and change. (http://www.jstor.org Fri Apr 13, 2017).

ከዚህ የምንገነዘበው ይህ ንድፈ ሃሳብ የማህበረሰቡ ባህላዊ ጉዳዮች ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገሩ ፋይዳቸውን የሚመለከት ቢሆንም ከጠቃሚ ባህላዊ እሴት በተቃራኒ ያሉትን ጉዳዮችም የሚተነተኑበት መንገድ ነው፡፡ በሌላ መልኩ እያንዳንዱ የፎክሎር ቅንጣት ዘውግ (genre) ለሰው ልጆች ትርጉምና አገልግሎት አላቸው፡፡ ይህም ማለት ዘውጉ ለምን ዓላማ እንደሚነገር፣ እንደሚከወንና ምን አገልገሎት እንዳለው አውድን መሠረት አድርጎ የሚገለጽበትና የሚተነትንበት መሆኑን Malinowski (1946 [1923]) ይገልጻል፡፡በዚሁ ቲዮሪ መሰረትም ሥነቃል፤ የማስተማር፣ የማዝናናት፣ ባህልን የመጠበቅ፣ የመቆጣጠርና በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ባህላዊ ወጎቹን የሚጠብቅበትና ማህበራዊ ግንኙነቱን የሚያጠናክርበት ነው (Bauman, 1977)

Malinowski (1946 [1923]) እንደሚገልጽ፣ ፎክሎራዊ ዘውጎች በልዩ ትርጉምና አገልግሎት ይተነትናሉ፡፡ የእያንዳንዱ ዘውግ አላማ፣ አሰራር እና ተግባር ሊገለጽበት ይችላል፡፡ በመሆኑም፣ ፎክሎር የማስተማር፣ የማዝናናት፣ የባህል ጥበቃ፣ የማህበረሰብ መቆጣጠርና የማህበራዊ ግንኙነት መጠናከር ዓላማዎችን ይወስናል (Bauman, 1977)፡፡ በአጠቃላይ፣ ተግባራዊ ቲዎሪው ፎክሎርን በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሥነ ልቦናዊና ተምሳሌታዊ መስኮች ማብራራት ይችላል፡፡ ይህ መንገድ፣ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ተግባራቸውንና ፋይዳቸውን በተመራማሪ መልኩ ለማቅረብ የተመረጠ ነው፡፡

## 2.2.ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ

ተመራማሪዎች ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ለመተንተን እንደሚጠናው ጉዳይ እና እንደአጥኚው አላማ ተገቢ ናቸው ያሏቸውን የተለያዩ ንደፈ ሀሳቦች መርጠው ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ንደፈ ሀሳቦች ተቀራራቢ ሀሳብን የያዙ ቢመስሉም በውስጣቸው ግን የአንጻር ልዩነት አለ፡፡ በዚህ ክፍልም በአብዛኛው አጥኚዎች ዘንድ የሚመረጡ የፎክሎር ንድፈ ሀሳቦችን ምንነት እና ባህሪ በማሳዬት ለዚህ ጥናት የተመረጠውን ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ተገቢነት አስረዳለሁ፡፡

### 2.2.1 ተምሳሌታዊ ንድፈ ሀሳብ

በፎከሎር ዘውግ ተምሳሌታዊ ንደፈ ሀሳብን የተለያዩ ሙሁራንበተለያኡ አሰተምሮትንና የጥናት ዘርፎች የተለያዩ ምርምራዊ ሃቲታዎች በማሰረጃ አቅርበዋል፡፡ከነዚህም ውስጥ Dorson (1972) በፎከሎር ዘውግ ተምሳሌት በቁሳዊ ባህል የፎክሎር ዘውግ ስር የሚካተት ነው በማለት አቅርበዋል፡፡ በተጨማሪም, Victor Turner (1961) ተምሳሌታዊ ባህላዊ ነገሮች የማህበረሰብን እውቀት በውስጣቸው እንደሚያከብሩ ይገልጻል፡፡ ተምሳሌት በቅርፁ እና በይዘቱ ላይ የማህበረ-ባህላዊ ፍቺን የሚያመለክት ነው፡፡ በዚህ መሠረት, ተምሳሌት በቁሳዊ እና በረቂቅ (አብስትራክት) መስፈርቶች ይከፋፈላል፡፡ Eahleman, J. Ross, Barbara G. Cashion, እና Laurence A. Basirico (1993) እንደሚገልጡት፣ ቀለማት፣ ድምፆች፣ አቅጣጫዎች እና ክስተቶች እንደ ረቂቅ ተምሳሌት ሊገለጹ ይችላሉ፡፡

በአፍሪካ, በተለይም በዛምቢያ ማህበረሰብ ላይ የአደረገው ጥናት መሠረት, Victor Turner (1967) ተምሳሌቶች ብቻ በቁሳዊ ነገሮች ላይ የሚታዩ አይደሉም፣ በሰዎች ድርጊቶች፣ በማህበራዊ ግንኙነቶች፣ በአካላዊ እንቅስቃሴዎች እና ሥፍራዎች ጭምር ተምሳሌታዊ አገልግሎት ይዘው እንደሚገኙ ይገልጻል፡፡

ከእነዚህ ከተዘረዘሩት የተምሳሌት አይነቶች የሚያመለክተው የማህበረሰብ እውቀትና ፍቺ በሥነቃል ተወካይነት ማሳያ እንደሆነ በአውዱ ውስጥ ማህበራዊ እውቀቱ ያለውን ድርሻ ማጉላቱ ላይ ነው፡፡

በመሆኑም የሰነቃል ተምሳሌት በቁጥሮች፣ በስሞች፣ በቀለሞች፣ በአቅጣጫዎች፣ በክስተቶች እና በቦታዎች የተምሳሌታዊ ትርጉም ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ ተምሳሌትን በአንድ ባህል ሲመለከት በሌላ ባህል ሌላ ትርጉም ሊኖረው እንደሚችል Gusfield and Jerz (1984) ይገልጻሉ፡፡

Dundes (1989) ተምሳሌት በቋንቋ፣ በቁሳቁስ፣ በክዋኔ እና በርካታ ትርጉሞች የተሰበሰበ መሆኑን ይገልጻል።

በፎክሎር ውስጥ አብዛኛው ተምሳሌታዊ ንግግር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ይወከላል። Mills (2008) እና ባይለየኝ ጣሰው (2009) እንደሚገልጡት፣ እነዚህ በተለምዶ ሜታፈሮች (Metaphors) እንደሚቀርቡ ይገልጻሉ። እንዲሁም, ሌሎች የሥነቃል አይነቶች የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ ትርጉሞች እንደሚወከሉ ይገልጻሉ። ከዚህም ተነስቶ, የተምሳሌት ንጽጽር ውስጥ የሜታፈር ስርአት የተጠቀመ መሆኑ ይገለጻል። ስለዚህ፣ በዚህ ጥናት ተምሳሌታዊ ጉዳዮችን ለመተንተን የተምሳሌት ቲዎሪ ተመርጧል።

## 2.2..2 አውዳዊ ንድፈ ሀሳብ

የዚህ ቲዮሪ አቀንቃኞች Bascom (1954) እና Ben Amos (1993) ዋነኛ ትኩረት አንድ የፎክሎር ዘውግ የተከናወነበትን አውድ ማሳየት ነው። ቀደምት የBascom (1954) እሳቤዎችን መሰረት በማድረግ ምሁራን እንዳመለከቱት ማንኛውም ክዋኔ ሲተነተን የክዋኔው ዓውድ መገለጽ አለበት (Okpewho 1992:10፤ Ben Amos 1993:1 ፈቃደ 1991:37)። Jackson (1986:4) አውድ በስነ ሰብእ (Anthropology) ጥናት ውስጥ ላለ ሁሉም ተመራማሪዎች ወሳኝ ጉዳይ ቢሆንም ለሁሉም ግን ዓውድ ወሳኝ እና በተመሳሳይ መንገድ የሚያገለግል አይደለም። እንደዚሁም Sims and Stephens (2005:137) ዓውድ የፎክሎር አንድ ቅንጣት የሚከወንበት ውስን ማህበራዊ ሁነት መሆኑን ይገልጻሉ።

**አውዳዊ** ንድፈ ሀሳብ **(Contextual Theory) -** በጥልቅ እንዳማራጭ ትንታኔ ፎክሎር እንደ ማህበራዊ እና ባህላዊ ምህዳር የሚገለጽ ትምህርታዊ የጥናት መሰረት አንዱ አውዳዊ ቲዎሪ ነው። በዚህ መንገድ፣ ፎክሎር በተፈጥሮ በአውድ (context) የተቀመጠ ነው። አውድ የሚለው ግንባር በትምህርት፣ በጊዜ፣ በቦታ፣ በማህበራዊ እና ባህላዊ ሁኔታዎች እንዲሁም በስነፍትህ ተመን ተደርጎ ይታያል።

1. **አውዳዊ ቲዎሪ በፎክሎር ጥናት ውስጥ** አውዳዊ ቲዎሪ ፎክሎርን ከእርሱን የወሰደው ምህዳር እና ዘመን ጋር አጠቃላይ እንዲመሳሰል ይጠይቃል። ይህ እይታ ከፎክሎር ዝርዝር ማንኛውም አባል አንደኛ በሆነ መልኩ ተቆርጦ ማገናኘት እንዳይቻል ይገልፃል። በሌላ አገልግሎት፣ አንድ ተረት ወይም ቀልድ እንኳን ሲወሰድ፣ የተቀመጠበትን አውድ ሳይመረመር መረዳት አይቻልም። ምሳሌ፣ የኢትዮጵያ ሰፊ ቦታዎች የሚነገሩ ተረቶች እና

ዝናዎች የእያንዳንዱ አካባቢ ባህላዊ እና ማህበራዊ ሁኔታ የተፈጠረ መሆናቸው የታወቀ ነው። በዚህ ዓይነት ምሳሌዎች፣ ሙሉ ፍቺን ለማግኘት የተረት ወገኖችን፣ ዘመኑን፣ ምን ዓይነት ማህበረሰብ ውስጥ እንደተቀረበ ማስተዋል ያስፈልጋል።

2. **የአውድ አይነቶች** እንደ Bascom (1984) እና Dundes (1965) በጥናት ተሰናብተው የተቀመጡት አውድ አይነቶች፡- **ማህበራዊ አውድ** (Social Context): የፎክሎሩ የተግባር ሁኔታ፣ በምን ዓይነት ተቋማት ውስጥ የሚከናወን እና ተሰናባሪዎቹ በማን እንደሆኑ የሚገልጽ ነው። **ባህላዊ አውድ** (Cultural Context): የማህበራዊ እምነት፣ ዘውድ፣ ስርዓት እና አመለካከት እንዴት እንደሚተካ የሚያመለክት ነው። **ታሪካዊ አውድ** (Historical Context): ፎክሎሩ በምን ዓይነት ታሪክ ሂደት ውስጥ ተወስዷል እና ከተዘመኑ ጋር ተያይዟል? **ቦታዊ አውድ** (Geographical Context): ፎክሎሩ የተወሰነ ቦታ ውስጥ እንደተፈጠረ የሚገልጽ አውድ ነው።

3. **አውዳዊ** ንድፈ ሀሳብ **የሚደግፉ የጥናት ስምምነቶች** Ben-Amos (1971): "ፎክሎር እንደ ሂደት" አለ። ይህም ፎክሎሩ ከአንደኛ ሰው ወደ ሌላ በሚያስተላለፍበት ሁሉ አውዱ ማስተዋል አስፈላጊ ነው የሚል ነው። Dundes (1965): "ፎክሎር ባህላዊ እና ማህበራዊ አውድ ውስጥ ሊገባ ይገባል።" Bascom (1984): "ፎክሎሩ በማንበብ ወይም በአውድ የተገባ ስርዓት መሆኑን ያረጋግጣል።"

4. ***ሐተታ መደምደሚያ*** አውዳዊ ቲዎሪ በፎክሎር ምርምር ውስጥ ከፍተኛ ተፅዕኖ አለው። የፎክሎሩን ሰነድ እንደ ተቀረበበት እና ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን በትክክል ሳንመርመር ፎክሎሩን ሙሉ በሙሉ ማረዳት አይቻልም።

**የአውድ ግንዛቤ በፎክሎር ጥናት ውስጥ** በዘመናዊ አጠቃቀም አውድ ሲታይ፣ የአንድ ድርጊት ክንውንና በፎክሎር ጥናት ውስጥ ደግሞ ቲዮሪዎችና ዘዴዎችን የሚመለከት መሆኑን Ben-Amos (2006) እና Goldstein (2004) ይገልጻሉ። ተናጋሪው *ሥነቃሉን* ሲያቀርብ የአቀራራብ ሁኔታ፣ የሚከውኗቸው ድርጊቶች፣ አካላዊ እንቅስቃሴ፣ የከዋኙ ችሎታ፣ እና የተመልካቹ ስሜት አቀራረብ በአውድ ውስጥ ይታያሉ (Bauman, 1977)። በፎክሎር ጥናት ውስጥ አውድ ማለት የታየና የተሰማ መረጃ ማብራሪያ ብቻ ሳይሆን፣ ባህላዊና ማህበራዊ አይነት ሁኔታዎችን በጥልቀት መተርጎምና መተንተንን ይጨምራል (Ben-Amos, 1993:210-211)። አውድ በሥነቃል ግንዛቤ ሲታይ፣ ከሦስት ቁልፍ አካላት ይመዘገባል፡- የከዋኙ ሰብእና፣

የመከወኛው ድባብ፣ እና የማህበራዊና ባህላዊ አውድ (Okepewho, 1992:105)። የከዋኙ ሰብእና የግለሰቡ የተፈጥሮ ዝንባሌ፣ ቤተሰባዊ ዳራ፣ ተመክሮችና የትምህርት ታሪኮችን ያካትታል። የመከወኛው ድባብ ከከዋኙ አንደበት የሚወጡ ቃላት፣ ሙዚቃዊ መሳሪያዎች፣ ታዳሚዎችና በከዋኙ ላይ ያሳድሩ ተጽዕኖዎችን ይጨምራል። Sims & Stephens (2005:138) አውድን እንደ ድርጊት ከሚከወንበት ጊዜና ቦታ ጋር በተያያዥነት ያቀረቡት ሲሆን፣ የፎክ ቡድኑ አባላት፣ ተቀማጭነትና ማህበራዊ ሁኔታዎች ይወሰናሉ። ስለዚህ አውድ በቴክስትና ክዋኔ ዙሪያ በሚፈጸሙ ግንዛቤዎች ላይ ይታያል። የአውድ ዓይነቶች አውድ በሁለት ዓይነት ይከፈላል። ማህበራዊ አውድ፡ የሚከወነው ጉዳይ በማህበራዊ ሁኔታ ውስጥ የሚቀርብ ነው።

**ባህላዊ አውድ**፡ የሚከወነው ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲሆን፣ በውስጡ እምነታዊ፣ ቋንቋዊ፣ ታሪካዊና ሥነ-ምግባራዊ ህጎችን ይጨምራል (Ben-Amos, 1993:216)።

የእነዚህን አውድ ትኩረት እንደሚከተለው እንመልከታለን።

1. **ፍቻዊ አውድ፡-** የዚህ አውድ ትኩረት የሚያጠነጥነው ፎክሎራዊ ጉዳዩ ምን ለማለት ተፈልጎ ነው? የሚለውን ጥያቄ ከመመለስ ላይ ነው። ይኸውም ማህበረሰቡ ስለሚከውናቸው ፎክሎሮች (የሥነቃል ዓይነቶች) ያለው ግንዛቤ፣ አረዳዱ፣ ለመከወን ያነሳሳው ጉዳይና የትኛውን የህይወት ገጽታ እንደሚያሳዩ ለመረዳት ያስችለናል።

2. **ተቋማዊ አውድ፡-** በአውድ ተኮር ጥናት ሊተኮርበት ከሚገባው ውስጥ ተቋማዊ አውድ ሌላኛው ጉዳይ ነው። ይህ ደግሞ ፎክሎራዊ ጉዳዩ የት ቦታ ይከወናል? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ነው። ጉዳዩ የሚከወንበት በባህሉ ውስጥ የት ቦታ ላይ እንደሆነ ለይተን ማስቀመጥ እንዳለብን የሚያስገነዝበን አውድ ነው። ይኸውም የሚከወኑት የት እንደሆነ ከማስገንዘቡም በላይ ፎክሎራዊ ጉዳዩ መከወናቸው የሚያስገኘውን ተቋማዊ ፋይዳ ለመመርመር ያግዛል።

3. **የማህበረሰቡ የተግባቦት ሂደት አውድ፡-** በአውድ ተኮር ጥናት ውስጥ የሚጠናው ፎክሎራዊ ጉዳይ ከሌላ የፎክሎር ቅርጽ ጋር እንዴት ይዛመዳል? ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚሻ ነው። ይሄም የሚጠናውን ፎክሎራዊ ጉዳይ ቅርጽ ምንነት፣ አንዱ ከሌላው ጋር ያለውን ዝምድና አንዱን ከሌላው ለመለየት ማህበረሰቡ የሚጠቀምበትን ዘዴ በውስጡ ያካትታል።

4. **ማህበራዊ መሰረት፡-** ማህበራዊ መሰረት የሚባለው የማህበረሰቡን የኑሮ ሁኔታ ከግምት ውስጥ መግባት እንዳለበት የሚያመለክተን ነው፡፡ ይሄ ማለት የሚጠናው ፎክሎር የሚከወነው በየትኛው የማህበረሰብ ክፍል እንደሆነ፡ የትኛውን ማህበራዊ ደረጃ እንደሚያሳይ፣ በክዋኔው ሌላው የማህበረሰብ ክፍል ተሳትፎ ምን እንደሆነ በመረዳት የተሻለ አውዳዊ ትንታኔ መስጠት ማለት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉት አባላት በጾታ፣ በዕድሜ፣ በሙያ፣ በማህበራዊ ደረጃ፣ በሃይማኖትና በመሳሰሉ ቡድኖች ይከፈላሉ፡፡

5. **ግለሰባዊ አውድ፡-** ግለሰባዊ አውድ የሚመለከተው አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከወን የግለሰቡን ሕይወት ምን እንደሚመስል ከማወቅ ላይ ነው፡፡ በዋናነት የሚከወነው ፎክሎራዊ ጉዳይ ከግለሰቡ ኑሮ፣ ሀሳብና ስሜት ጋር እንዴት ይያያዛል? ለሚል ጥያቄ ምላሽ ከመስጠት ላይ የሚያጠነጥን ነው፡፡ በዚህ አውድ ውስጥ የግለሰቡን የመከወን ችሎታና ፎክሎራዊ ጉዳዩ ለግለሰቡ የሚሰጠውን ስሜት ሊጤን ይገባል፡፡ ይህም ከግለሰቡ መንፈሳዊ፣ አስተዳደራዊ እና ባህላዊ ማንነት ጋር ሊያያዝ ይችላል፡፡

6. **ሁኔታዊ አውድ፡-** በመጨረሻ በአውዳዊ ትንተና ውስጥ የሚነሳው ጉዳይ ሁኔታዊ አውድ ሲሆን፣ማህበረሰቡ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን የሚከውነው በምን አይነት ሁኔታ ውስጥ ነው? ለሚለውና በማህበራዊ ሁኔታ እንዴት ጠቃሚ እንደሆነ ምላሽ የሚሰጥ ነው፡፡ ሁኔታዊ አውድ ሲባል በባህሉ የተወሰነ የአንድ ገጠመኝ መግለጫ አንድ ትርጉም ያለው ድርጊት የሚከናወንበት አውድ ማለት ነው፡፡ በዚህ ውስጥ አካላዊ መቼቱ፣ የተሳታፊዎቹ ማንነትና በክዋኔው ውስጥ የሚኖራቸው ሚና፣ክዋኔውን የሚገነዘቡባቸው የተለያዩ ህግጋት፣ በከዋኙና በታዳሚዎቹ መካከል ያለው ተግባቦት፣ የክዋኔው አተረጓጎም የሚከናወንበት መመሪያ፣ በየደረጃው የሚከናወኑ ድርጊቶችና ተግባራት፣ ቅደም ተከተላቸውን ጭምር ያካትታል፡፡

### 2.2.3. የክዋኔ ቲዎሪ

ፎክሎርለሚያጠና ሰው ከፍ ያለ ድርሻ የሚወሰድበት ጉዳይ ክዋኔ ነው፡፡ ክዋኔ ማለት፣ ሰዎች አንድን ድርጊት እንዴት እንደሚፈጥሩ፣ እንዴት እንደሚለዋወጡ እና ከዚህ ከድርጊቱ መልእክት ጋር እንዴት እንደሚተዋወቅ መገንዘብ ማለት ነው፡፡ በዚህ መሠረት፣ አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ በክዋኔ እንዲታወቅ ሁለት መሰረታዊ አተያዮች እንዳሉ በBauman (1992:5) በአርታኦቱውስጥ ጠቁመዋል፡፡ የመጀመሪያው አተያይ፣ ድርጊቱ በማህበረሰቡ ተስማሚ ስርዓትና

ደንብ ላይ ተመስርቶ መካከል እንዲፈጠር እና ታዳሚው አዳዲስ ፎክሎሮችን የመፍጠር እድል እንዲኖረው ይጠቀሳል። ሁለተኛው አተያይ፣ ክዋኔው በተሳታፊዎች እና በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው የሚያስችለውን ቋንቋ፣ የአነጋገር ስርዓትና የአከዋወን ሂደት እንዴት እንደሚተገበር ይመረምራል።

ፎክሎራዊ ጉዳይ በሚቀርበው ማህበረሰብ ማህበራዊ፣ ሀይማኖታዊና ፖለቲካዊ እንዲሁም ከዋኛና ተሳታፊው ባለው አቅም መሠረት ይለያያል። በዚሁ ምክንያት፣ የክዋኔው ደረጃና የመልእክቱ መግለጫ በተለያዩ አጋጣሚዎች ይለዋዋጣል። ከዋነኛና ተሳታፊው ጾታ፣ እድሜ፣ የእውቀት ደረጃ፣ ክዋኔውን ለመከወን የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፣ የጉዳዩ አቀራረብ ጊዜና ቦታ፣ ዓይነት፣ ጭብጥ እና የስልት አማካይነት ሁሉ በክዋኔ ትርጓሜ ውስጥ ይካተታሉ። ይህም ማለት፣ ከዚህ ጉዳይ የተነሳ ትንታኔ የተወሰነ ተስማሚነት እንዲኖረው ይገባዋል።

በፎክሎር ጥናት ውስጥ የክዋኔ ጽንሰ ሃሳብ በማህበራዊ ዓውዶችና ግንኙነቶች ላይ ተደጋጋሚ በመሆኑ፣ ከዋኞችን እና ታዳሚዎችን በጥልቀት ማስተዋል ይጠየቀዋል። ከዋኛው እና ታዳሚው እርስ በርስ እንዴት እንደሚያዳምጡ፣ ፎክሎርም በህይወት ዕድል ላይ እንዴት እንደሚያስተጋልጥ ይመረምራል። በFinnegan (1992) መሠረት፣ ክዋኔ በሥነ-ቃል ሁሉ ውስጥ የጥበብ አላባዎችን ያካትታል። እንዲሁም፣ (Dundes 2005:389: Sims and Stephens 2005:128) በፎክሎር ጥናት ውስጥ የክዋኔ አስፈላጊነትና የፉክክር ጉዳይም መመዝገባ እና መተንተን እንዳለበት ይገልጻሉ።

አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ አቀራረብ በሚከውነው ማህበረሰብ ማህበራዊ፣ ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶች እንዲሁም እንደ ከዋኙና ተሳታፊው አቅም ይለያያል። በዚህ ምክንያት መልዕክቱም ስለሚለያይ የክዋኔው ደረጃ በሚቀርብበት አጋጣሚ ይወሰናል። በሌላ በኩል የከዋኙና የተሳታፊው ጾታ፣ እድሜ፣ የእውቀት ደረጃ፤ ክዋኔውን ለመከወን የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፣ ጉዳዩ የሚቀርብበት ወቅትና ጊዜ እንዲሁም የፎክሎራዊ ጉዳዩ ዓይነት፣ ጭብጥና የአቀራረብ ስልት ሁሉ በክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ውስጥ የሚጠቃለሉ በመሆናቸው ለሚከወኑበት አጋጣሚ የሚመጥኑ ሆነው መቅረብ አለባቸው።

በመሆኑም በዚህ ጥናት የፎክሎራዊ ጉዳችን ክዋኔ በተዉኔቶች ዉስጥ ለመተንተን የክዋኔ ቲዎሪ ተመርጧል።

### 2.2.4 የፎክሎር ዳያክሮኒክና ሲንክሮኒክ ንድፈ ሀሳብ

በዳይክሮኒክ እሳቤ መሰረት አንድ በንግግር የሚከወን የፎክሎር ዓይነት የታሪክና የማህበራዊ ድርጊቶች ውጤት ነው (Bauman & Brigges 1992):: አንድ የስነ ቃል አይነት በተለያዩ የታሪክ ወቅቶች ውስጥ የነበረውን ቀጣይነት ለማየት፣ የማህበረሰቡን ህይወት ከማንጸባረቅ አኳያ የተጫወተውን ሚናና የነበረውን ተግባር ለመመርመር ይህ ቲዮሪ ይረዳል፡፡ ከሲንክሮኒክ አቅጣጫም ስነ ቃሎች ይተነተናሉ፡፡ ይህ አቅጣጫ በዚህ ጥናት ውስጥ በተለያዩ ስነ ቃሎች መካከል ያለውን የይዘት ገጽታዎች (Textual Features) ስምረት ለመፈተሽ ይረዳል፡፡ እነዚህ የይዘት ገጽታዎች በስነ ቃሎች አማካይነት የተላለፉት መልዕክቶች ምን ያህል ጥምረትና ስምረት እንደነበራቸው ለመግለጽ ያገለግላሉ፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥም የተካተቱ አንዳንድ ስነቃሎችን ለመተንተን የመሰኩ ምሁራን ዳያክሮኒክና ሲንክሮኒክ ብለው የሚጠሩት ይህ ቲዎሪ ተመርጧል፡፡

### 2.2.5 የሐይማኖት ንድፈ ሀሳብ

ሃይማኖትና እምነት ምንም እንኳን በራሳቸው የተለየ የጥናት መስክ ቢሆኑም፣ በፎክሎር እንደገና በተለይም በሚቶሎጂ መስክ ከታሰቡ እና ከሐሳብ ዐቢያት መካከል አንዱ ናቸው፡፡ ፎክሎር ከሀገረ-ሰባዊ ልማዶችና ከሃይማኖታዊ እሴቶች ጋር በሚታወቀው ቁርኝት መሰረት፣ ሃይማኖትና ፎክሎር የተቃራኒ ሀሳቦች መሆናቸው የሚገለጽ አስተያየት እንደማይቀመጥ በግልፅ ቃላት የተናገረ ነው (Larry 1986, in Fekade 2003:53)፡፡ የሃይማኖት ትርጉምን በተመሳሳይ አሳተፉ፣ በተለያዩ መልኩ የሚያቀርቡ ጽሁፎች ተገኝተዋል፡፡ ለምሳሌ፣ O'Neil ሃይማኖትን ሰዎች በልዕለ ተፈጥሮ ኃይላት የሚያምኑበት የእምነት ስርዓት መሆኑን ይገልጻል (O'Neil 2009)፡፡ Schoemaker ደግሞ ሃይማኖትን ከመንፈሳዊ ልማዶች የተነሳ የሕይወት ስርዓት እንደሆነ ይቀርባል፡፡ የተለያዩ ሃይማኖቶች በቅርጻቸውና በይዘታቸው ሊለያዩ ቢችሉም፣ ከተከታዮቻቸው ዘንድ በመመኘትና በእምነት ለመገባባት የሚደረጉ ከበራዎች ተመሳሳይ ባህላዊ ማስተዋል ያላቸው ናቸው (Schoemaker 1990:238)፡፡ Peoples እና Bailey ደግሞ

> "The three components of all religions, then are (1) belifes about the existence and nature of supernatural powers, (2) mythologies about the historical deeds of these powers, and (3) rituals intended to influence these powers to intervene favorably on behalf of the performances" (Peoples, J. and Bailey, G. 1991:293).

ሁሉም ሃይማኖቶች በተለያዩ ሁኔታዎች የሚገኙ አሶስዬትዎች አሉት ብለዋል። እነሱም (1) የልዕለ ተፈጥሮ ኃይላት ላይ የሚኖሩ እምነቶች፣ (2) እነዚህ ኃይላት የፈጸሙትን ታሪካዊ ሥራዎች የሚነግሩ ሚቶች፣ (3) እነዚህን ኃይላት በአዎንታዊ መንገድ ለመግባባት የሚከናወኑ ከበራዎች ናቸው (Peoples, J. and Bailey, G. 1991:293)።

ከዚህ መሠረት በመንሳት፣ ሃይማኖት እምነቶች (beliefs)፣ ሚቶች (mythologies)ና ከበራዎች (rituals) በመካከላቸው ያለው ግንኙነትን የሚያሳየው ተዋህዶ ስርዓት መሆኑ ይገልጻል። በአጠቃላይ፣ ሃይማኖት ዓለምን ፈጥሮ በላይነት የሚቆጣጠር የልዕለ ተፈጥሮ ኃይል ላይ እምነት መሰረት ያደረገ፣ በእምነት መርዳት የሚገለጹ ሚቶች እና እነዚህን ተመልከት የሚያደርጉ ከበራዎች የተያዙ እሴቶችን የሚያሳዩ ዘርፎች ናቸው። በዚህ ጥናት፣ ሃይማኖትን የመሠረት መንፈስ በማድረግ፣ ከፎክሎራዊ ዘርፎች ጋር የሚኖሩ ዝምድናዎችን ለመተንተን የሃይማኖት ቲዎሪ በመተግበር ተመራጭ መሆኑ ተግለጿል።

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ሃይማኖት በውስጡ እምነቶች (belifes)፣ ሚቶች (mythologies) እና ከበራዎች (rituals) እርስ በርስ የሚደጋገፉ ጽንሰ ሀሰቦችን እንደሚያካትት ነው።

ጠቅለል ባለ አገላለጽ ሃይማኖት ዓለምን በፈጠረና ተፈጥሮን በበላይነት ይቆጣጠራል ተብሎ በሚታመንበት ልዕለ ተፈጥሮ (supematural being) ልዩ ኃይል በእምነት መቀበል፣ ስለልዕለ ተፈጥሮው እውነትነትና ሀያልነት የሚያስረግጡ ሚቶች ያላቸውና ሃይማኖታዊ ድርጊቶቹ ያዘሉትን እሴቶች የሚገልጹ ከበራዎች ውጤት እንደሆነ ከተለያዩ ብያኔዎች ለመረዳት እንችላለን።

በዚህ ጥናት ከሃይማኖት ጋር ተያይዘዉ የሚነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ለመተንተን የሀይማኖት ቲዎሪ ተመራጭ ሆኖአል።

## 2.2..6 የመሠረታዊ ፍላጎት ንድፈ ሀሳብ

የመሠረታዊ ፍላጎት ቲዎሪ ዋና ትኩረቱ ወሲብን እንደ ሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎት ለመለየት ነው። የሰው ልጅ ወሲባዊ ብቃት በአካላዊ እድገትና በወሲባዊ አዝግመት ለውጥ ይጠናቀቃል። ወሲባዊ ባህርይ ብቻ ደስታን ሳይፈጥር ፣ ዘርያዊ ቀጥታንም እንደ ተፈጥሯዊ ግዴታ ይቆጠራል። Erikson (1959, 1963, 1968) እና Susan Moore & Doreen Rosenthal

(2006) በሥራቸው ይህንን ገልጸታል፡፡ ተጨማሪ በ Kantor (1999) መሠረት የሰው ልጅ ወሲባዊ ፍላጎት ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ በቀስታ እያደገ የሚከተለው እና በማህበረሰብ ባህላዊ ስርአት የሚታወቀው መሆኑን ያበራል፡፡ Wolf (1962) ደግሞ ልጆች ከተወለዱ በኋላ ወሲብን እየተማሩ እንደሚያድጉ ያመለከታል፡፡ እንደ ምሳሌ፣ ጡትና ጣት መጥባት ወሲባዊ ተግባራት መሆናቸውን ይገልፃል፡፡ ልጆች ሲደግፉ ፣ በቤተሰብ ደረጃ የሚያነሱ ጥያቄዎች ለተመሳሳይ ምላሽ ካላገኙ ፣ ጉጉታቸው ይጨምራል፡፡ ይህም በቀጣዩ ወደ ግብረ ሥጋ ግንኙነት ሊወስድ ይችላል፡፡ የተለያዩ ምሁራን ጥናቶች የሚያሳዩት የወሲባዊ ልምድ ቅርጸ ባህልን እና የማህበረሰብ አስተሳሰብ ምን ያህል እንደሚገዛ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ፣ አንድ ግለሰብ ወሲብ የሚፈጽመው በሚኖረው ማህበረሰብ ባህል የተገዛ ነው፡፡ ስለዚህም ወሲብን አስመልክቶ የሚነገሩ የሥነ-ቃል ዓይነቶች እና ከባህል የተነሱ የወሲባዊ ተግባራት እንዴት ግልጽ እንደሆኑ ይገለጻል፡፡

### 2.2..7 የማህበረሰብ እዉቀት አዋቃሪያን ንድፈ ሀሳብ

የማህበረሰብ እውቀት አዋቃሪያን ቲዎሪ (The Social Construction of Knowledge Theory) ይህ ንድፈ ሀሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ ገኖ የወጣው እ.ኤ.አ. በ1966 በእነ Berger,P. & Luckman T. ካሳተሙት "The Social Construction of Reality" ከሚለዉ መጽሀፋቸው በኋላ ነው፡፡  የማህበረሰብ እውቀት አዋቃሪያን ቲዎሪ በመጀመሪያ ጊዜ በ1966 ዓ.ም በPeter Berger እና Thomas Luckmann በተጻፈው **"The Social Construction of Reality"** መጽሐፍ ውስጥ ተቀምጦ ተቀምጧል፡፡ ይህ ንድፈ ሀሳብ እውቀት እንደ ተፈጥሮ አይደለም፣ ነገር ግን በሰው መካከል በመግባባት በማህበረሰብ የተገነባ እንደሆነ ያሳያል፡፡ በዕለታዊ ዕድል የሚከናወኑ ተግባራት በማህበረሰብ ላይ እያደጉ ይሄዳሉ፤ እነዚህ ደግሞ በመቀጠል ተቋማትን እየገነቡ የእውቀት ድንጋጌ ይሆናሉ፡፡ በዚህ ትውልድ እና በሌሎች ዘመናት ማህበረሰብ እውቀቱን በቅርንጫፍ በተለያዩ አይነቶች ያቀርባል፡፡፡

> "The primary knowledge about the institutional order is knowledge on the pretheoretical level. It is the sum total of 'what everybody knows' about a social world, an assemblage of maxims, morals, proverbial nuggets of wisdom, values & beliefs', myth, and soforth... (Berger and Luckman, 1966:83).

ማህበራዊ መዋቅር ወሲባዊ ትርጉም ቲዮሪ የሰው ልጅ ወሲባዊ ባህርይን ከማህበረሰቡ የሚማር መሆኑንና ይህንንም በቋንቋ አማካይነት እንደሚገለጽና ሁሉም ማህበረሰብ ባህሉን፣ ወጉን፣ እምነቱን፡ አስተሳሰቡን እና አመለካከቱን መሠረት የሚያደርግ የራሱ የሆነ የወሲብ አፈጻጸም ባህርይ እንዳለው (Banks and Banks (2001) ያብራራሉ፡፡ ይህም የሚያሳየን ወሲባዊ ጉዳዮችን በተመለከተ የማህበረሰቡ ባህል ወሳኝ ሚና ያለው መሆኑን ነው፡፡

በመሆኑም ከዚህ ንድፈ ሀሳብ አተያይ ዕውቀት ተፈጥሮአዊ ሳይሆን ማህበራዊ ውቅር መሆኑን ነው፡፡ ንድፈ-ሀሳቡ ማህበረሰቡ በጋራ ያዋቀሩት ዕውቀት በግለሰብ ደረጃም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ በእኩል የሚሰራ ድንጋጌ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ግለሰቦች ማህበረሰቡ ባኖሯቸው ድንጋጌዎች ይገለገላል፤ ይመራል፤ ይቀጣል፡፡ ንድፈ-ሀሳቡ ዕውቀቱ በሂደት ባዋቀሯቸው የጋራ ጉዳዮች ውስጥ በግለሰብ ደረጃና በማህበረሰብ ደረጃ ትርጉም አዘል ሆኖ ሊሰራ እንደሚችል ያወሳል፡፡

ይህ ንድፈ ሀሳብ እውቀት በሰው መካከል በተጋላጭ ሁኔታ የሚተላለፍ እና በግለሰብና በማህበረሰብ ደረጃ የሚሠራ ማህበራዊ ግንኙነት ነው፡፡ ሰዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ባለው የእውቀት እቃው ይመራሉ፣ ይቀጣሉ እና ይገለግላሉ፡፡ በወሲብ ጉዳይ የሚመለከቱ ፆታዊ ባህሪያት በማህበረሰብ ባህላዊ መዋቅር የተሠሩ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ Susan Moore እና Doreen Rosenthal (2006) እንደሚያሳዩት፣ የፆታ እውቀትና ባህሪ የተደጋጋሚ ሂደት በአምስት ደረጃዎች ይታያል: ፆታዊ የነገሮች ግንኙነት ፆታዊ ማንነት የፆታ ሚና ወሲባዊ ችሎታን፣ እውቀትና ወግ መውረስ በማህበረሰቡ ውስጥ ወሲባዊ ተሳትፎ ይህ እንዲፈጠር በማህበረሰቡ የተዘጋጀው ቋንቋ እና በዘፈን፣ በቀልድ፣ በምሳሌ ወይም በተረት ያሉ ዓይነቶች ይጠቀማሉ (Olson, 2000)፡፡ እነዚህ በባህላዊ ድንጋጌ ውስጥ የፆታ ትርጉምን በመፍጠር ወይም በመተላለፍ በማህበረሰብ ላይ ተጽዕኖ ያሳያሉ፡፡

## 2.2.8 ተግባራዊ ንድፈ-ሀሳብ (Fuctional Thory)

ተግባራዊ ንድፈ-ሀሳብ (Fuctional Thory) በማህበራዊ ህይወትና በስነ-ተፈጥሯዊ ህይወት ውስጥ ያለውን ተመሳሳይነት ያንፀባርቃል፡፡ የአንድ ፍጡር መላ አካላት የሚፈጽሟቸው ተግባራት ተደምረው ፍጡሩን ሙሉና ህያው የሚያደርጉት ከሆነ የፎክሎር ክዋኔዎችም ተደምረው የከዋኙን ማህበረሰብ ህልውና ሙሉ የሚያደርጉ ተግባራዊ ፋይዳዎች አሏቸው (Radcliffe-Brown 1935: 394-397)፡፡ ፎክሎርና የፎክሎር ትርጉም ከሰው ጋር የተሳሰረ መሆኑንና ፎክሎር የማስተማር፣ የማዝናናት፣ የማስተላለፍ እና ባህላዊ ማንነትን የማስጠበቅ

ተግባር እንዳለው Bascom (1954:344-346) ያስረዳል፡፡ ከዚያም በላይ የተግባራዊ ቲዮሪ እሳቤን ማወቅ አንድ የሰዎች ቡድን በአንድ ውስን ሁነትና ውስን ክዋኔ ውስጥ ምን እየሰራ እንደሆነ ለመረዳት ያግዘናል፡፡ ተግባራዊ ቲዮሪ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከወን ማንኛውም ነገር ያለውን ተግባርና አገልግሎት ለመመርመር ይረዳል (Okpewho (1992:173)፡፡ እዚህ ላይ ማንኛውንም የሚለው አባባል ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ በማህበረሰቡ ውስጥ በግንባታ ሚና ብቻ ሳይሆን በአፍራሽ ሚናም የሚገለጽ መሆኑን ነው፡፡ የፎክሎር ተግባር የማህበረሰቡን ባህል ከትውልድ ወደ ትውልድ በማሸጋገር ሚና እንዳለው ሁሉ ይህ ጥናትም የተመረጡትን ቴአትሮች ፎክሎራዊ ፋይዳ የሚተነትን በመሆኑ ተግባራዊ ንደፈሀሳብ ዘዴን መጠቀም ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

## 2.3 የተዛማጅ ጽሐፍች ቅኝት

ይህ ምርምር ከሚመለከተው ጉዳይ ጋር በቅርብ የተያያዙ የቀድሞ ጥናታዊ ስራዎችን በተመሳሳይ ማዕከላዊነት ሲያቀርብ ይመለከታል፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ቤት እና የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ለዲግሪ ማሟሚያ ያቀረቡትን እንዲሁም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ውስጥ በትውፊታዊ ቴአትር እና በምርምር ክፍል የተሰሩ ስራዎችን የሚካተት ነው፡፡ በእነዚህ ጥናቶች መካከል፣የበላይ መኮንን (1999 ዓ.ም) "የደቡብ ንግስት ተውኔት ከአፈ-ታሪኩ አንፃር" የሚል ጥናት ፣ የተመስገን ፋናዬ (1995 ዓ.ም) "የዛር ትውፊትና በውስጡ የሚገኙ የቴአትራዊ አላባውያን በራያና ቆቦ አካባቢ" የሚባል ጥናት፣ የእንግዳ ሐብቴ (1984 ዓ.ም) "የሶዶ ብሄረሰብ ትውፊታዊ ድራማ" የሚለው ምርምር፣ እና በወሰን ባዩ "በኢትጵያ ቴአትር የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳች ፋይዳ በተመረጡብተውኔቶች ማሳያነት" የፒ.ኤች.ዲ ማሟያ የቀረበ ጥናት 2010 ዓ.ም ይህ በተዉኔቶች ማሳያነት በሚል ርዕስ የተደረገነዉ፡፡ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ጽሑፎች ከዚህ ምርምር ጋር በተመሳሳይ መስክ ያደረጉትን ጥናታዊ ትኩረት በማሳየት በመሳሰሉ ባህላዊ አላባዎች እና ትውፊታዊ የቴአትር ተውኔቶች ላይ በሚመለከቱ አካባቢያት ላይ እውቀትና መረጃ በመስጠት የዚህ ምርምር መሰረታዊ ቅርፅን ያጠናክራሉ፡፡

**በበላይ መኮንን** (1999 ዓ.ም) በተዘጋጀው "የደቡብ ንግስት ተውኔት ከአፈ-ታሪኩ አንፃር" የሚባል ጥናታዊ ጽሁፍ ውስጥ፣ አፈታሪኩ ምን እንደሆነ እና ምን ዓይነት አገልግሎት እንደሚሰጥ በዝርዝር ተቀምጧል፡፡ በትክክል የተጠቀሰውን መሠረት ሲያደርግ፣ አፈታሪኩ

የአንድ ሰው የታላቅነት መንገድን፣ የህይወቱን ተግባራዊ ታሪኮችን፣ የተረፉትን መከራና ውጣ ውረዶችን፣ እና ከሌላው ሰው የሚለየውን ብዙሀን መልካም ገጽታና ተሰጥኦን እንደሚያሳየው ታወቀ። እንዲሁም፣ አፈታሪኩ ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል ወይም በጽሑፍ የሚተላለፍ በመሆኑ፣ የሥነ-ቀል አንደኛ ዓይነት መሆኑን ይጠቁመናል። ይህም አፈታሪኩ የሚነገረው በመዝናኛ እንጂ ሳይሆን፣ ሰዎች ለባህላቸው አሳሳቢ ሁኔታዎችን እንዲቀየሩ እና በሕይወታቸው ላይ አሳሳቢ ጉዳዮችን እንዲያውቁ ማስተማሪያ መሆኑን ያመለከተ።

ይህ የበላይ መኮንን አቀራረብ ከእኔ ጥናት ጋር በፎክሎራዊ ፋይዳ ላይ በተመሳሳይ መንገድ የሚያዛምድ ቢሆንም፣ በአቀፍ አድራጎቱ ላይ ግን አየት ያለየ ነው። የእሱ ጥናቱ በዋናነት በአፈታሪክ ላይ ብቻ አተኮረ ሲሆን፣ እኔ ግን በፎክሎር መስክ ውስጥ በተወሰኑ ተውኔታዊ አላባውያን ላይ እይታ እንዳለኝ የሚገልጽ ልዩነት አለ።

- ፅንሰ-ሀሳባዊ መሠረቶች እና ትኩረት "የደቡብ ንግስት ተውኔት ከአፈ- ታሪክ" በዋነኛነት የደቡብ ኢትዮጵያ ንግሥና መጋጠሚያን በታሪካዊ ትረካዎች በተለይም በአመራር፣ በፖለቲካ አስተሳሰቦች እና በንግሥና ትሩፋት ላይ ያተኮረ ይመረምራል። "ፎክሎራዊ ፋይዳ" የቲያትር ልምምዶችን ባህላዊ ጠቀሜታ እና በመገናኛ፣ ወግ እና በማህበራዊ ጥቅማ ጥቅሞች ወይም "ጠቃሚነት" ላይ የሚኖራቸውን ተፅእኖ በጥልቀት የባህል እሴቶችን ያስተላልፋል።

- የጭብጣዊ ንጽጽር አንድነት እና ቀጣይነት; የመኮነን ስራ ማህበረሰባዊ ውጣ ውረዶች ወይም ታሪካዊ ፈተናዎች ቢኖሩትም የባህላዊ የሃይል አወቃቀሮችን (መንግስታትን) ቀጣይነት በትውልዶች ላይ ያጎላል። ሁለተኛው ጥናት የሚያተኩረው በባህላዊ ልምምዶች ጭብጥ ቀጣይነት እና በዘመናዊ አውዶች ውስጥ በተለይም በባህል ጥበቃ ላይ እንዴት ጠቃሚ ሆነው እንደቆዩ ነው። የባህል ጠቀሜታ፡- ሁለቱም ስራዎች የርዕሰ ጉዳዩን ባህላዊ ጠቀሜታ አፅንዖት ይሰጣሉ፣ ምንም እንኳን መኮንን የንግሥና ጉዳዮችን ቢናገሩም፣ ሌላኛው ደግሞ የባህልን ቀጣይነት በቲያትር አካላት ይመረምራል።

- ዘዴያዊ አቀራረቦች የመኮንን ምርምር በታሪክ ትንተና ላይ የተመሰረተ ነው, በቀደሙት ክስተቶች, በፖለቲካ ስርዓቶች እና በዘመናዊው ማህበረሰብ ላይ ያላቸውን አንድምታ ላይ በመመርኮዝ. "ፎክሎራዊ ፋይዳ" ባህላዊ እና ማህበራዊ መልእክቶችን በመቅረጽ እና

በማስተላለፍ ረገድ ያለውን ሚና በመፈተሽ የበለጠ የስነ-ብሔረሰብ ወይም የባህል አፈጻጸም ዘዴን ይጠቀማል።

- የወሰን ልዩነት የመኮነን ስራው ያተኮረው በልዩ ክልላዊ ታሪካዊ ትረካዎች እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች (ደቡብ ኢትዮጵያ) ላይ ሲሆን "ፎክሎራዊ ፋዳ" ግን በሰፊው ያተኮረው በተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች እና ባህላዊ አካባቢዎች የቲያትር ልምምዶች አጠቃቀም ላይ ነው። ሁለተኛው ጥናት ዘመናዊ ቲያትር እንዴት እንደሚስማማ እና ትውፊትን እንደሚያስተላልፍ በማንፀባረቅ ለዘመናዊ አፕሊኬሽኖች ብዙ ቦታ የሚሰጥ ሲሆን የመኮነን ጥናት ደግሞ በታሪክ ላይ ያተኮረ ሊሆን ይችላል።

- መደምደሚያ በማጠቃለያው፣ ሁለቱም ሥራዎች ጠቃሚ ባህላዊና ማኅበራዊ ክስተቶችን ሲያብራሩ፣ ከተለያዩ አቅጣጫዎች አንፃር መኮንን በታሪካዊ ትሩፋትና በፖለቲካዊ መዋቅር ላይ በማተኮር፣ ሁለተኛው ጥናት ደግሞ በባህላዊ አፈጻጸምና በተግባራዊ አንድምታው ላይ ያተኮረ ነው።

**የተመስገን ፋናዬ** ጥናት በሦስት ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን፣ የመጀመሪያው ምዕራፍ ጥናቱ የተካሄደበትን አካባቢ ዳራዊ ገለፃና በአካባቢው የሚዘወተሩ ሌሎች ተዛማጅ ትውፊታዊ ክንዋኖችን የያዘ ነው። ሁለተኛው ምዕራፍ የዛር ትውፊት በራያና ቆቦ ሲመለከት፣ ሦስተኛውና የመጨረሻው ምዕራፍ ደግሞ የዛር ትውፊት ይዘትን በአጠቃላይ ያጠቃልላል።

የተመስገን ፋናዬ ጥናት በዋናነት ያተኮረው የቴአትርና የዛር ትውፊታዊ ክንዋኔን በማዛመድ፣ በዛር ትውፊት ውስጥ የሚገኙ ተውኔታዊ አላባዎችን ነቅሶ በማውጣት የሁለቱን ዝምድና ባህርያት ማመላከት ነው። ቴአትሩ ከአምልኳዊ ሥርዓት በቀስበቀስ ወደ ድራማ ከዚያም ወደ ቴአትር ያለውን ሽግግር ደረጃዊ መቀየሩን ያሳያል። እንዲሁም አምልኳዊ ሥርዓት በድራማ አማካኝነት ወደ ቴአትር የመሸጋገሩ ሂደት ከብዙ ጊዜ የወሰደ መሆኑን፣ እና የተወሰኑ አላባዎች (እንደ የሚና ክፍልል፣ ድባብ፣ ቃላዊና ኣካላዊ ምላሽ) በቀስበቀስ ተሻሽለው መጡና ሌሎች ባህርያት ደግሞ እየጠፉ መሆናቸው ታዋቂ ነው።

ይህ የተመስገን ጥናት ከዚህ በፊት የተከናወነው የዛር ትውፊት እና ቴአትር መካከል ያለው ትምህርታዊ እና ባህላዊ ግንኙነት ላይ በብዙ ደረጃ ልዩነት ያለውን አመለካከት በግልፅነት ያሳያል። እርሱም በራያና ቆቦ አካባቢ ላይ ብቻ በመመስረት እንዲሁም በዛር ትውፊት ውስጥ የሚገኙ ተውኔታዊ አላባዎችን አበልፎ በመቅረፍ የቴአትር እና የአምልኳዊ ሥርዓት ዝምድናን

በባህርያት ማመላከት የቻለ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ቴአትር ውስጥ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሚያሳዩበት ፋይዳ መኖሩንም በቅርብ ያቀርባል፡፡

**አንድነትና ልዩነት** የተመስገን ፋናዬ (1995 ዓ.ም) "የዛር ትውፊትና በውስጡ የሚገኙ የቴአትራዊ አላባውያን በራያና ቆቦ አካባቢ" እና "ፎክሎራዊ ፋይዳ በተመረጡ ትውፊታዊ ተውኔቶች ማሳያነት" በትናቱ መካከል ያለውን አንድነት እና ልዩነት ለማቅረብ በተስፋፋ መልኩ የተዘጋጀ የትንታኔ ትንታኔ እንደሚከተለው ነው፡፡ አንድነት፡- ሁለቱም ጥናቶች በተለያዩ ቅርጸ ተውኔቶች ውስጥ ያሉ ፎክሎራዊ ዘይቤዎችን በመመልከት፣ እነዚህ ዘይቤዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ላላቸው ተግባራዊ እና ማህበራዊ እሴት በትንታኔ እንዲታወቅ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

የተመስገን ፋናዬ ጥናት በተለይም በተወሰኑ አካባቢዎች የተስተናገዱ የቴአትራዊ ቅርፀ ተውኔቶችን በማስረጃ ያቀረበ ሲሆን፣ "ፎክሎራዊ ፋይዳ..." የሚባል ጥናት ደግሞ በአጠቃላይ ቅርፀ ተውኔቶች የሚታዩትን የማህበረሰብ እሴትና ተግባራት በማቅረብ ያካትታል፡፡ ልዩነት፦ "የዛር ትውፊትና..." በተመስገን ፋናዬ ጥናት በተወሰኑ አካባቢዎች ላይ ትኩረት በማድረግ በማህበራዊ ክንዋኔና ቴአትራዊ ባህርያት መካከል ያለውን ዝምድና በቅርብ ያቀረበ ሲሆን፣ "ፎክሎራዊ ፋይዳ..." የሚባል ጥናት ግን እሱ የመረጠው ተውኔቶች ያላቸውን እሴታዊነትና ማህበራዊ ጥቅም በአጠቃላይ ማሳያነት ነው፡፡ እንዲሁም፣ የተመስገን ፋናዬ ጥናት የቴአትርና የሥርዓተ አምልኮ ዝምድናን እንደ ዋና አሳሳበ ቢያቀርብም፣ "ፎክሎራዊ ፋይዳ..." ግን እነዚህን እንደ አንዱ ክፍል በማየት ከፍ አድርጎ አያቀርብም፡፡

**እንግዳ ሐብቴ** (1984 ዓ.ም) የተዘጋጀው "የሶዶ ብሄረሰብ ትውፊታዊ ድራማ" እንደ ጥናታዊ ስራ፣ አራት ትኩረት ክፍሎች ላይ ተመስርቶ የተደረገ ነው፡፡ በመጀመሪያው ክፍል አጠቃላይ መግቢያ በመሆኑ፣ ስለ ጉራጌ ክልል ታሪካዊ አያያዝና በተለይ ስለ ሶዶ ብሄረሰብ በጥቂት ቃላት መግለጫ ሊሰጥ ተሞክሮ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ በሁለተኛ እና ሶስተኛ ክፍሎቹ፣ ከጋብቻ ምርጫ ጀምሮ እስከ መልስ ድረስ የሚከተሉ የባህላዊ ሥነ-ሥርዓቶች በተወሰነ ቅደም ተከተል በተገለጹ የልምዶች እና ተግባራዊ ምስክሮች ድርድር ተሰጥቷል፡፡ በመጨረሻ ክፍል ግን፣ የትውፊቱ መስመራዊ ዝርዝር ውስጥ ያሉ አበይት የድራማ አላባውያን በተመረጡ መልኩ ተቆጥተዋል፡፡ እንግዳ በጥናቱ ውስጥ፣ ትውፊት እንደ ትውልድ ከሌላ ወደ ሌላ የሚተላለፍ፣ በአካልና በሐሳብ እንቅስቃሴ የሚደረግ የእውቀት ተላላፊ መንገድ ነው ብሎ ይገልጻል፡፡

እነዚህም በትውፊቱ ውስጥ የሚካተቱ የዳንሶች፣ የጨዋታዎች፣ የግስጋሴ ዘውትር ነው። ነገር ግን፣ እንዳሳሰበው፣ እነዚህ የትውፊት ዘውትሮች በማህበረሰቡ ውስጥ የህይወት መቅረትን በተመለከቱ እንጂ የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሥነ-ልቦናዊ ውጤቶች ብቻ አይደሉም፤ ይህም የእውቀት መረዳጃ የሆነ ነገር እንደሚካተት ያመለክታል። ይህ በእኔ ጥናት የተነሳ እና በፎክሎር በመመስረት የሚገለጽ ሃሳብ ጋር በተዛማች ሲሆን፣ በሌላ አንጻር ደግሞ የተለያዩ ማህበራዊ ዘዴዎች፣ ባህላዊ ጉዳዮች እንዲደገፉ፣ ወይም እንዲሻሻሉ የሚጠይቁ ትኩረቶችን ያቀርባል። ለምሳሌ፣ የጋብቻ ምርጫ፣ የሠርግ አይነቶች፣ የጥፍር ቀፈፋ፣ የጫጉላ ፍቻ፣ የመልስ ሥነ-ስርዓቶች በአብዛኛው እርስ በርሳቸው አንደኛ ዓመፃ ተያያዥነት እንዳላቸው ታየ። በአጠቃላይ፣ የእንግዳ ሐብቴ የተሰኘው ጥናታዊ ጽሁፍ በሶዶ ብሄረሰብ የተለያዩ ባህላዊ ሥርዓቶችን በሙሉ በድርሰት አቀረበ፣ እኔም ያለኝ ሃሳብ ከነዚህ ውስጥ አንዳንድን በፎክሎር አመሳሳቢ መንገድ ለቴአትራዊ ትንታኔ መሳሰሉ የሚሆኑ እንደ ተረት ቁልፍ ማዕከላዊ ተግባሮች እየተመለከትኩበት ነው።

ተመሳሳይ እና ልዩነት (Comparative Discussion) ተመሳሳይነት (አንድነት)

- ሁለቱም ጥናቶች በትውፊታዊ ዘመናዊነት ያተኮሩ ናቸው። ሶዶ ብሄረሰብ በተመረጠ ድራማ ቅርፅ የታየ በሆነ የልምድ መሠረት እና ባህላዊ እንቅስቃሴ ተገልጿል። እንዲሁም፣ ፎክሎራዊ ፋይዳ ጥናት እንዲሁን በመሆኑ ፎክሎር የታሰረ የትውፊት ክፍል በድራማ ውስጥ እንዴት እንደሚታይ አሳይቷል።

- . ባህላዊ አስተዋጽኦን እና ማህበራዊ እሴቶችን አሳየ። ሁለቱም ጥናቶች ከዘመናዊ ትውፊቶች ጀምሮ እስከ ቤተሰብ ዋጋ እና እንደተለመደ መቀባት እሴቶችን በፎክሎር መሰረት በግልጽ ሁኔታ አሳየ።

- የተውኔት ቅርንጫፎችን የመንገድ ዘዴ አካትተዋል። የትውፊት እንቅስቃሴ ምሳሌዎች፣ ሙዚቃ፣ የመሣሪያ ጥበባት፣ የመነሻ አካላት እና የግልፅ ምሳሌዎች በሁለቱም ጥናቶች ተሳትፎ አሉባቸው።

**ልዩነት**

- የጥናቱ አላማ እና እሴት መግለጫ የተለየ ነው፡፡ እንግዳ ሐብቴ በትውፊታዊ ድራማ የሶዶ ብሄረሰብን መኖሪያ ዘዴ እና የትውፊት ትምክህት በማዕከሉ ሲያደርግ፣ ፎክሎራዊ ፋይዳ ጥናት ግን በአጠቃላይ ፎክሎርማሳያነትና የትውፊት አስተላለፊ ኃይልን በትውልድ መሪ አሳይቷል፡፡

- የጥናቱ መሰረታዊ መርሃግብር የተለየ ነው፡፡ "የሶዶ ብሄረሰብ ትውፊታዊ ድራማ" በተወሰነ ብሄረሰብ ላይበሚደረግ ልምድ ተመስርቶ ሲወሰን፣ "ፎክሎራዊ ፋይዳ..." ጥናት ግን በተለያዩ ተውኔቶች እና በብዙ አካባቢያት ተዘጋጀ ነው፡፡

- የትውፊት መዋቅሮች እና አቋማቸው በግልጽ ሁኔታ የተለያየ ነው፡፡ በ"ሶዶ ትውፊታዊ ድራማ" ስለተወሰነ አካባቢ ትምህርት ተሰጥቷል፣ ፎክሎራዊ ፋይዳ ግን በዝርዝር የተመረጡ የትውፊት አካላትን እና ፋይዳቸውን ከፎክሎር ዓይነት ጋር አቀናጀች፡፡

**የጫንያለው ወ/ጊዮርጊስ እና ደስታ ሎሬንሶ** የጋራ ጥናት የሆነው የቃቂ ወርዶዎት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር የትውፊታዊ ቴአትር ትውን ጥበባት ጥናትና ምርምር ክፍል ከተሰሩ ጥናትና ምርምሮች መካከል  ይገኝበታል፡፡ "የቃቂ ወርዶወት" ይህ ጥናት በዋናነት ሁለት ክፍሎችን ያካትታል፤ የመጀመሪያው ክፍል "የቃቂ ወርዶወት ትውፊታዊ የጥናት ውጤቶችና አንትሮፓሎጂያዊ ትንተና" ተብሎ ይጠራል፤ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ "የቃቂ ወርዶወት ታሪክ፣ የጉራጌ ብሔረሰብ ባህል፣ ሥነ-ቃልና ትውፊታዊ አላባውያን" የሚል መሆኑን ተገልጿል፡፡

አጥኝዎቹ በጥናታቸው ውስጥ፣ በ1860 ዓ.ም. የተቀመጠች ቃቂ ወርዶወት በጉራጌ ባህል እና ታሪክ ላይ አስፈላጊ ተጽእኖ እንዳሳደረች አሳውቀዋል፡፡ በዚያን ዘመን፣ አለም ላይ የሴቶች መብት እና እኩልነት ጥያቄ ገና ሳይቀርብ፣ ቃቂ ወርዶወት ይህንን እውነተኛ ጥያቄ በመያዝ እና በጥበባዊ ቅርፅ ማቀላጠፍ ቻላ፡፡ የምርምራቸው አፈ-ታሪኮች፣ ሥነ-ቃሎች፣ ግጥሞችና ዘፈኖች ይህንን አስተዋጽኦ ያመለከቱ መሆናቸውን በደረሰባቸው ውጤቶች በግልፅ ቋንቋ ያሳያሉ፡፡ ይህ ጥናት በ"የወፍ ንግር በምስጢሩ ትውፊታዊ ድራማ" ርዕስ ተመርቷ የቀረበ ሲሆን፣ የሴቶች ድምፅ እና ኃላፊነት በማህበራዊ ዘርፍ የሚገለጽበት አንዱ አስፈላጊ ብቃት መሆኑ ይታወቃል፡፡

**በወሰን ባዩ** "በኢትጵያ ቴአትር የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳች ፋይዳ በተመረጡብተውኔቶች ማሳያነት" የፒ.ኤች.ዲ ማሟያ የቀረበ ጥናት 2010 ዓ.ም ይህ በተዉኔቶች ማሳያነት በሚል ርዕስ የተደረገነዉ፡፡ ከዚህ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የተለያዩ ጥነናትና ምርምሮች የተደረጉ ቢሆንም፣ በዋናነት የፎክሎርን በቴአትር ውስጥ ከማጥናትና ፋይዳውን ከማሳየት አንጻር እስካሁን በሀገራችን የተደረገ ጥናትና ምርምር የለም፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት የመጀመሪያና ወጥ ሥራ ነው:: ጥናቱ ይዞ የተነሳዉ ዓለማ በኢትጵያ ቴአትር የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳች ፋይዳን በተመረጡ ተዉኔቶች ዉስጥ ማሳየት ነዉ፡፡ በመሆኑም ለዚህ ማሳያ የሚሆኑ ሰባት ተዉኔች በኢላማ ተኮር የናሙ አመራረጥ ስልት ተመርጠዋል፡፡

እነዚህም ተዉነቶች፡- ፋቡላ ( ተክለ ሀዋርያት ተክለማርያም፣1906)፣ ያላቻ ጋብቻ (መንግስቱ ለማ፣1952) ፣ አልቃሽና ዘፋኝ (ፍስሀ በላይ ይማም፣1952)፣ ሾተላይ (አያልነህ ሙላት 1991) ፣ የቴዎድሮስ ራዕይ (ጌትነት እንየወ, 2000)፣ የቃቄ- ወርዶወት (ጫንለዉ ወልደ ጊዮርጊስ፣2005) እና የአሻ ልጅ (አስታጥቃቸዉ ይሁን 2009) ናቸዉ፡፡ ጥናቱ በዋናነት ያተኮረዉ በተዉኔቶቹ ዉስጥ በተነሱ ስነ ቃልን እና ሀገረሰባዊ ልማድን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ሲሆን ከልዩ ልዩ ቲዎሪዎች አንጻር ሰፊ ገለጻ እና ማብራሪያ ተደርጎባቸዋል። ትንተናው የተከናወነው በዋናነት ከተግባር ቲዎሪ አኳያ ሲሆን፣ ትንታናውን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ቦታ ደግሞ ሌሎች ልዩ ልዩ ቲዮሪዎች ማለት ተምሳሌታዊ ቲዎሪ፣አውዳዊ ቲዎሪ፣የክዋኔ ቲዎሪ፣የፎክሎር ዳይክሮኒክና ሲንክሮኒክ ቲዎሪ፣የፌሚኒዝም ቲዎሪ፣ የሐይማኖት ቲዎሪና የማህበረሰብ እዉቀት አዋቃሪያን ቲዎሪ ደጋፊ መተንተኛ በመሆን አገልግለዋል።

በተጨማሪም በቃል-መጠይቅ ከተለያዩ ሰዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመጠቀም በአንዳንድ ተዉኔቶች ዉስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን አካባቢያዊናባህላዊ ትርጉም በተሟላ ሁኔታ ተገንዝቦ ለመግለጽ፣ ለመተርጎምናለመተንተን ተሞክሯል፡፡በዚሁ መሰረት በተዉኔቶቹ ዉስጥ የተነሱት ስነ ቃል እና ሀገረሰባዊ ልማድን የተመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳች ፋይዳ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ባህላዊ ፣ ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ስነ ልቡናዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሞራላዊ፣ ግብረገባዊ፣ መንፈሳዊ፣ ስነጽሁፋዊና ኪነ ጥበባዊ ፋይዳ ያላቸዉ መሆኑን የጥናቱ ዉጤት ያመለክታል፡፡

አንድነት፡- 1. ሁለቱም ጥናቶች ፎክሎርን እንደ የባህል ትርጓሜ መለያ አስቀድሞ ያወጣሉ። 2. በተወሰኑ ተውኔቶች ላይ መመርመር፡ ሁለቱም የተመረጡ ተውኔቶችን መመርመራቸው አንድነት ያሳያል። 3. ፎክሎርን በተውኔት ውስጥ እንደ አካል አውቅ፡ ፎክሎር በቴአትራዊ ማሳያነት ውስጥ እንደ ትርጉም የተገኘ አካል እንደሆነ ተቀባይነት አላቸው።

ልዩነት ፡- "በኢትዮጵያ ቴአትር..." ጥናት ፎክሎር በቴአትራዊ አሰራር ላይ እንዴት ተጠቅመና በመድረኩ ላይ እንዴት ይታያል በሚል የመድረክ አቀራረብ ነው መነሻው። ፎክሎርን በትውፊታዊ ተውኔቶች ውስጥ እንደ ቅዱሳን የባህል መሳሪያ በውስጣዊ መርሃግብር ላይ ያቀርባል።

የተወሰነው ፎክሎር፡ - ቴአትራዊ ጥናቱ ፎክሎርን እንደ ተወካይ የመልዕክት መላኪ ይወስዳል። ጥናቱ ደግሞ ፎክሎርን እንደ ሕዝባዊ አካባቢ የህይወት ወጣበት መለያ ይያዛል።

የግለሰቡ ተመን፡ - የተመረጡ ቴአትራዊ አብራሪዎች በቴአትር ሥራ ላይ ትኩረት አድርገው ፎክሎርን እንደ ዕይታ ተጠቀሙበት። - በዚህ ጥናት ውስጥ ፎክሎርን እንደ የህዝብ መነሻ ህልውና እና አንደኛ ባህላዊ እሴት ያቀርባል።

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. የተመረጡ 3 ትውፊታዊ ተውኔቶች  የመረጃ ትንተና

ይህ ምዕራፍ ከተውኔቶቹ የተወሰዱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ከንድፈ ሐሳባዊ ማሕቀፉ ጋር እየተንሰላሰሉ የሚተነተኑበት ነው፡፡

## 3.1 የተውኔቶቹ አህጽሮተ ታሪክ (Synopsis)

በቀጥታ ወደ መረጃ ትንተና ከመግባቴ በፊት የተውኔቶቹን አህፅሮተ ታሪክ (Synopsis) ባጭር ባጭሩ ይቀርቡበታል፡፡

### 3.1.1 “ምስጢሩ”

ተውኔቱ በአንድ ገጠራማ አካባቢ የተፈጸመ የግድያ ወንጀልን ለመፍታት የሚደረገውን የአውጫጭኝ ሸንጎ ውሎ ይተርካል፡፡  “አውጫጭኝ” ማንነቱ ባልታወቀ አካል ወንጀል ሲፈጸም የአካባቢው ነዋሪ ወንጀለኛውን የሚያጋልጥበት ሂደት ነው፡፡ ተውኔቱ የሚያጠነጥነው በዚህ አውጫጭኝ ሸንጎ ሂደት ላይ ሲሆን፣ ከምስጢር ሞት ጋር ግንኙነት ሊኖራቸው የሚችሉ ሰዎች በሸንጎው ፊት ቀርበው ጥያቄዎችን እንዲመልሱ፣ እንዲመሰክሩ እና እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ የተደበቁ ምስጢሮች፣ የቆዩ ቂሞች፣ የፍቅር ግንኙነቶች፣ እና የገንዘብ ሽኩቻዎች አንድ በአንድ ተፈትሸዋል፡፡ በመጨረሻም ባልተጠበቀ ሁኔታ እውነታው ተጋልጧል፡፡ ገዳዩ ማን እንደሆነ መታወቁ ብቻ ሳይሆን፣ ከግድያው በስተጀርባ ያሉት ምክንያቶችም ታውቀዋል፡፡ ተውኔቱም ይህንን የአውጫጭኝ ውሎ ሂደት ያሳያል፡፡

### 3.1.2 "ተጠየቅ"

"ተጠየቅ" የተሰኘው ተውኔት በ1980ዎቹ ጎጃምን ዳራ አድርጎ የአቶ ካሳ እና የወ/ሮ አጀቡሽን ፈተና የተጋረጠበት የትዳር ሕይወት ይተርካል፡፡ አቶ ካሳ በጤና እክል ምክንያት የባልነት ግዴታቸውን መወጣት ባለመቻላቸው ወ/ሮ አጀቡሽ ከፍተኛ ቅሬታ ውስጥ ይወድቃሉ፡፡ ይህ አለመግባባት እየሰፋ ሲሄድ፣ ጉዳያቸው በአካባቢው ሽማግሌዎች እንዲታይ ይደረጋል፡፡ ሽማግሌዎቹም ሁለቱን ወገኖች በጥሞና ካዳመጡ በኂላ ውሳኔያቸውን ያስተላልፋሉ፡፡ ተውኔቱም የእርቁን ጠቅላላ ሂደትና ስነ ስርዓት ያሳያል፡፡

### 3.1.3 "ሽምጋይ"

"ሽምጋይ" የተሰኘው ተውኔት በ19ኛው ክፍለ ዘመን ጎንደርን ዳራ አድርጎ የአለቃ ገብረ ሐናን እና የቤተሰባቸው ህይወት ላይ መሰረት አድረጎ የተሰራ የኪነጥበብ ስራ ነው፡፡ አለቃ ገብረ ሐና በሃይማኖታቸውና በባህላቸው የጸኑ አባት ሲሆኑ፣ ተውኔቱ የትውፊትንና የዘመናዊነትን ግጭት፣ የቤተሰብን አንድነት እና በለውጥ ውስጥ ያለ ማኅበረሰብ የማንነት ጥያቄዎችን ያሳያል፡፡ በኅብረተሰቡ ተገልሎ የሚኖረው እና በፋቂነት የሚተዳደረው የወጣቱ ጌታነህ የአለቃ ገብረ ሐናን እርዳታ ለማግኝት የሚያደርገው ጥረት ተውኔቱን ይበልጥ ሳቢና አጓጊ አድርጎታል፡፡ ጌታነህን የመሰሉት በማኅበረሰቡ ውስጥ በተለያዩ የእጅ ሥራዎች የተሰማሩ - ሸክላ ሠሪዎች፣ ሸማኔዎች፣ ቀጥቃጮች፣ ወዘተ. - የሚደርስባቸውን መገለልና በደል ለማስቆም፣ አለቃ ገብረ ሐና ለንጉሠ ነገሥቱ ደብዳቤ ይልካሉ፡፡ ይህ "ሽምጋይነት" ወይም አስታራቂነት የተውኔቱ ማዕከላዊ ጭብጥ ነው፡፡

እነዚህን ተውኔቶች የቀረበቡበት አውድ፣ ታሪካቸውን፣ ከአቀራረባችው ን፣ ድራማዊ ቴክኒካቸውን መሰረት በማድረግ ያላቸውን ፎክሎራዊ ፋይዳ ተተንትኖ ቀርበዋል፡፡

በዚህም መሰረት የሚከተለው ማጠቃለያ ላይ ተደርስዋል በሶስቱ ትውፊታዊ ተውኔቶች ("ምስጢሩ" 2011, "ተጠየቅ" 2013, "ሽምጋይ" 2015) የተነሱ ፎክሎራዊ ፋይዳን በትክክል ለማቅረብና ለመተንተን አስፈላጊ ማሳያ ናቸው፡፡

## 3.2 የተውኔቶቹ ፎክሎራዊ አውድ ትንተና

አንድ ፎክሎረኛ መረጃ ለመተንተን ሲነሳ አውድን በተመለከተ ሊያተኮርባቸው የሚገቡ ስድስት ነጥቦች እንዳሉ የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ። እነሱም ፍቻዊ አውድ፣ ተቋማዊ አውድ፣ የማኅበረሰቡ የተግባቦት ሂደት አውድ፣ ማኅበራዊ መሰረት፣ ግለሰባዊ አውድ እና ሁኔታዊ አውድ ናቸው። የአውድ ትንተናውም በእነዚህ ስድስት ነጥቦች ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

1. በተውኔቶቹ ውስጥ የሚገኙ የፎክሎራዊ ጉዳዮችን አቀራረብ እንዲሁም በተውኔቶቹ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉበትን መንገድ መግለፅ። ይህ ዓላማ ፎክሎር የሚታወቀው መሰረታዊ መረጃ (እንደ ምስል፣ ቃል፣ ልምድ፣ መነሻ እና ተሞክሮ) እንዴት በትውፊት የተያዘ እና ምሳሌ በሆነ መልኩ በትውፊት ውስጥ ያቀረበ እና እነዚህ በእውነተኛው ባህላዊ አካባቢ እንዴት እንደተጠቀሱ መቀረብ ነው። ምሳሌ: በ"ምስጢሩ" ውስጥ የአያት ምክር፣ የጠላት በቃል መቀበል፣ የአገባብ ሥርዓት፣ የተማረከ እና ተረፈ የማንነት ምልክቶች እንዴት በፎክሎራዊ ጥቅም ላይ እንደዋሉ ያብራራል።

2. የተውኔቶቹ አቀራረብ በፎክሎራዊ ክዋኔው ያላቸውን ግንኙነት ማሳየት። ትውፊቱ እንዴት የፎክሎር አወቃቀር እና ቅርጸ-ጽሁፍ (structure) ላይ ታመነ? የመሰረታዊ ድራማዊ ተውኔት ቁልፍ ስነ-አቀራረብ ምን ያህል የፎክሎራዊ ቅርጸ ትምህርት ያሳያል? ምሳሌ: በ"ተጠየቅ" ውስጥ የትምህርታዊ ጥያቄና መልስ ቅርጸ-አቀራረብ በየመንገዱ እንደ የባህል እና የታሪክ እንደሚያመለክት እንዴት ተቀመጧል።

3. በተውኔቶቹ ጭብጥ ውስጥ የፎክሎራዊ ጉዳዩ ሚና መመርመር። የፎክሎር መረጃ እንደ ድራማ ውቅር ምን ዓይነት ሚና አለው? የታሪክ መታሰቢያ፣ የባህላዊ እሴት መግለጫ፣ የአብያተ ህይወት አስተዳደር እና የህብረተሰቡ መረብ እንዴት ተካትተዋል? ምሳሌ: በ"ሽምጋይ" ውስጥ የተወለደው ውህደት ፍላጎትና የአካባቢው ከትውልድ ትውልድ ተላልፎ ወገናዊ ግጭቶች በፎክሎራዊ እይታ ምን እንሚመስል ይገልጻል።

4. በተውኔቶቹ ውስጥ የተነሱት ፎክሎራዊ ጉዳዮች ጥቅም ላይ የሚውሉበትን መንገድ ወይም አውድ መመልከት። እነዚህ ፎክሎራዊ ጉዳዮች በትውፊቱ መሀከል እንደ ምሳሌ፣ መረጃ፣ ማሳሰቢያ፣ የአመለካከት መንገድ ወይም የተሰናዳ ግንዛቤ እንዴት ተጠቀሙ? ምሳሌ: በ"ተጠየቅ" የሚካሄደው የአሳዳጊ ሙከራ ፎክሎራዊ ጥያቄና መልስ እንዴት የተያዘ ነው? እነዚህ ንዑሳን ዓላማዎች የመረጡትን ተውኔቶች በትክክል ለመተንተን፣ የፎክሎር ዋጋና

ተግባራዊ እንቅስቃሴን ማሳየትና የፎክሎራዊ ፋይዳ በተመረጡ ትውፊታዊ ተውኔቶች ማሳያነት ስር የተቀመጡ አላማዎችን እና ተመን የሚሰጡትን ጥያቄዎች እንዲህ በሚል መልኩ መልስ ማቅረብ ይቻላል፡፡

### 3.2.1 የ"ምስጢሩ" ተውኔት ፎክሎራዊ አውድ ትንተና

*የ"ምስጢሩ" ተውኔት ፎክሎራዊ አውድ ትንተና*

- *የቃላት ማህበረሰቡ የሚጠቅምበት ቀበሌኛ ቃላትና ዘይቤ (የተለየ ቋንቋ አጠቃቀም): በ"ምስጢሩ" ውስጥ የተለያዩ የአማርኛ ቃላት፣ አንቀጾች፣ አነጋገሮች፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ቃላት እና የተለያዩ ቅርጸ ያላቸው ሲሆን ዘንድሮ የሚያመለክቱ ቃላት ተጠቅመዋል፡፡ የቋንቋ ፎክሎር ነው፡፡*

- *የመንፈሳዊ እምነቶች መቀላቀል: በተውኔቱ ውስጥ የነበሩ ድሮና አስገራሚ ሀሳብና መንፈሳዊ እምነቶች፣ እንዲሁም የምስጢር ቃላት እና አሳቦች ከባህላዊ እምነት መንገዶች የተነሱ ናቸው፡፡ እንዲሁም የዳኝነት ሥርዓቶች የተገኙት ከፎክሎራዊ ባህላት እና ማህበረሰቡ ከትውልድ እየተቀባበለ ይዞ በደረሰው የአካባቢው ባህል ነው፡፡*

- *የተወላጅ የመኖሪያ መልክ (ባህላዊ ቅርንጫፍ): የቤተሰብ ውስጥ ግንኙነት፣ የወንድና ሴት ተያያዥነት፣ የወጣቶች ድምብና ባህላዊ መረጃ የሚያሳየው ዕይታ በፎክሎራዊ አቀራረብ ተደርጓል፡፡ በተውኔቱ ውስጥም በአንድ ቤተሰብ ላይ የተፈፀመውን ድርብ ወንጀል ለማውጣጣት ከመላው የአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በመሆን የቤተሰብ ፍትህ የሚያገኝበት ስርአት ነውና*

- *የሥርዓተ-ሕግና ፍትሕ መዋቅሮች: በተውኔቱ ውስጥ የተቀመጡ ሽማግሌና የማህበራዊ ፍትሕ ውሳኔዎች ማህበረሰቡ ያመነባቸው ፍትህ ርትዕ ያሰፍናሉ ብሎ የሾማቸው ዘመናዊ ዳኝነት የሚቀበለው ነገር ግን በባህሉ በልማዱ ወንጀለኛን ለማውጣጣት የሚደአግ ፎክሎራዊ ስርአት ነውው፡፡ ይህ ከባህላዊ የዳኝነት ስርአት ፣ መጥፎ ድርጊቶች በማውገዝ ወንጀል ኛውን ለፍትህ አሳልፎ ለመስጠት እና ችግርን መፍቻ መንገዶች የሚታዩበት ነው፡፡*

### 3.2.1.1 ፍቻዊ አውድ

ፍቻዊ አውድ በፎክሎራዊ ጉዳዩ ምን ለማለት እንደተፈለገ የሚመረምርና ማኅበረሰቡ ስለሚከውናቸው ፎክሎሮች ያለውን ግንዛቤና አረዳድ እንዲሁም ፎክሎሩን ለመከወን ያነሳሳውን ጉዳይና የትኛውን የህይወት ገጽታ እንደሚያሳይ ይዳስሳል።

"ምስጢሩ" ባህላዊ የፍትሕ ስርዓት ሂደትን የሚያሳይ ሲሆን ማኅበረሰቡ ስለ ፎክሎሩ ያለው ግንዛቤና አረዳድ እንዲሁም ፎክሎሩን ለመከወን ያነሳሳው ጉዳይና የትኛውን የህይወት ገጽታ እንደሚያንጸባርቅ እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል።

ማኅበረሰቡ ባህላዊ የፍትሕ ስርዓቱን ለመከወን ያነሳሳው ጉዳይ ምንድን ነው?

ባህላዊ የፍትሕ ስርዓት ከቦታ ቦታ የተለያየ ስያሜ አለው። "አውጫጭኝ" በአንድ አካባቢ ውስጥ ወንጀል ሲፈጸም የአካባቢው ነዋሪዎች በአንድ ስፍራ በመሰብሰብ ወንጀለኛውን የሚያጋልጡበት ሂደት ነው። በ"አውጫጭኝ" የአካባቢው ነዋሪዎች ሆኑ የአካባቢው ሹም በጥፋተኛው ላይ ቅጣት የማስተላለፍ ስልጣን የላቸውም። የሸንጎው አላማ ወንጀለኛውን አጋልጦ ለመንግስት አሳልፎ መስጠት ነው። አስረጅ እንመልከት፦

> አቶ ተሁሉ፡- ሌላው ላስገነዝበው የምሻው ነገር ቢኖር ይኽ ሀገር አጥፊ ወንበዴ እስታልተጋለጠ ድረስ እንደተይህ ቀደሙ ሁሉ ቀኑ መሽቶ ቢነጋ እንኳ አውጫጭኙ እንደማይበተን ተገንዝባችሁ የሟች አስክሬን በሥርዓቱና በግዜው ቶሎ እንዲፈጠም ተሟች ጠብና ግንኙነት ነበረው አልያም እሱ ሊሆን ይችላል የምትሉትን ሰው ታለምንም ፍራቻና ይሉኝታ ታሁኗ ቅጥበት አንስቶ እንድትጠቁሙ ነው። /ሕዝቡ ያጉረመርማል/ አለኽኝ (2009፣ 13) (ሰረዝ የኔ)

አቶ ተሁሉበላይ የአካባቢው ሹም ሲሆኑ ሸንጎው ከመጀመሩ በፊት ነዋሪው ያለምንም ፍራቻና ይሉኝታ ወንጀለኛውን አጋልጦ እንዲሰጥ ሲጠይቁ እንመለከታለን። ነዋሪውን ለመሰብሰብ ያበቃው "ምስጢሩ" የተባለ አንድ የአካባቢው ነዋሪ መገደል ነው። ከሰረዙ ለመረዳት እንደምንችለው የአውጫጭኙ ዋና ዓላማ ወንጀለኛውን አጋልጦ ለመንግስት በመስጠት ሠላም የሰፈነበትና የተረጋጋ አካባቢ መፍጠር ነው።

ባህላዊ የፍትሕ ስርዓቱ የትኛውን የሕይወት ገጽታ ያሳያል?

ሌላኛው በዚህ ክፍል ሊመለስ የሚገባው ጥያቄ ፎክሎራዊ ጉዳዩ ወይም ባህላዊ የፍትሕ ስርዓቱ የትኛውን የሕይወት ገጽታ ያሳያል የሚለው ነው። በ"ምስጢሩ" ውስጥ የተነሳው ፎክሎራዊ ጉዳይ ("አውጫጭኝ") በገጠራማው የጎጃም ክፍል የሚተገበር ባህላዊ የፍትሕ ስርዓት ሂደት ነው። ፎክሎሩም የፍትሕ ተቋም በሌለበት አካባቢ ዘመናዊ የፍትሕ ተቋምን ወክሎ ያገለግላል።

ማኅበረሰቡ ስለ ባህላዊ ፍትሕ ስርዓቱ ያለው ግንዛቤ ምን ይመስላል?

ማኅበረሰቡ "አውጫጭኝ"ን የሚመለከተው እንደ ፍትሕ ተቋም ነው። የተበደለ የሚካስበት፣ ያልታወቀ ወንጀለኛ የሚጋለጥበት፣ ተጠርጣሪ ዉንጀላዉን እንዲያብራራ የሚጠየቅበት፣ ምስክር የሚሰጥበት፣ የክህደት ቃለ መሃላ የሚፈጽምበት፣... በአጠቃላይ ማኅበረሰቡ ለራሱና ለአካባቢው ሠላምና ደህንነት ሲል በወንጀለኛነት የተጠረጠረዉን ግለሰብ የሚያጋልጥበት ሂደት ነው።

### 3.2.1.2 ተቋማዊ አውድ

ተቋማዊ አውድ ፎክሎራዊ ጉዳዩ የት ቦታ እንደሚከወን ያብራራል። በተጨማሪም ፎክሎራዊ ጉዳዩ መከወኑ የሚያስገኘውን ተቋማዊ ፋይዳ ይመረምራል። አስረጅ እንመልከት፦

> /የጥሩንባ ድምጽ ከሩቅ ይሰማል ጭቃሹም ሙሉ ቀን አመሽ ከአስተዳዳሪው በደረሰው ትዕዛዝ መሰረት የአካባቢው ነዋሪ ዕውስ እንዲወጣ ያሳስባል/ ጡጥ ...ጡጥ ጡጡጡጥ ... በጎበና አውራጃ ለምትገኙ ነዋሪዎች በሙሉ ዛሬ ተጠዋቱ ሁለት ሠዓት ጀምሮ ተደረሳችሁ ታራስ ሴቶችና ሕጻናት በስተቀር "አውጫጭኝ" እንድትወጡ አስተዳዳሪው አዘዘዋል። /የጥሩንባ ድምጽ እየራቀ ይሄዳል ወዲያው ያንዲት ሴት ልቅሶ ይተካል/ አለኸኝ (2009፣ 12)

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደምንችለው "አውጫጭኝ" ሁሉም የአካባቢው ነዋሪዎች የሚሰባሰቡት እንደመሆኑ መጠን ማዕከላዊ ስፍራ ላይ የሚደረግ ሸንጎ ነው። ብዙ ጊዜ ትልቅ ዛፍ ስር ወይም ደግሞ ተራራማ ስፍራ ላይ ይከወናል። አብዛኛውን ጊዜ ወንጀሉ በተፈጸመ ማግስት ከቁርስ ሰዓት በፊት ይደረጋል። ይሄም የሚሆንበት ምክንያት ነዋሪው በንጹሕ መንፈስ ይገኛል ተብሎ ስለሚታመን ነው። ቀደም ሲል በፍቻዊ አውድ ለመግለጽ እንደሞከርኩት የ"አውጫጭኝ" ፋይዳ ወንጀለኛን በማጋለጥ ሠላም የሰፈነበት አካባቢ መፍጠር ነው።

### 3.2.1.3 የማኅበረሰቡ የተግባቦት ሂደት አውድ

ተግባቦታዊ አውድ የሚጠናውን ፎክሎራዊ ጉዳይ ከሌላ የፎክሎር ቅርጽ ጋር እያነጻጸረ ይመረምራል፡፡ ይህም የሚጠናውን ፎክሎራዊ ጉዳይ ቅርጽ፣ አንዱን ከሌላው ጋር ያለውን ዝምድናና ማኅበረሰቡ አንዱን ከሌላው ለመለየት የሚጠቀምባቸውን ዘዴዎች ያካትታል፡፡

"አውጫጭኝ" ከሌሎች ፎክሎራዊ ጉዳዮች በምን ይለያል?

"አውጫጭኝ" ባህላዊ የፍትሕ ስርዓት ሲሆን ከአካባቢ አካባቢ በተለያዩ መጠሪያዎች ይታወቃል፡፡ "አውጫጭኝ" ከሀገረሰባዊ ሽምግልና ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ሀገረሰባዊ ሽምግልና የአካባቢው አዛውንቶች ሁለት ግራና ቀኝ ወገኖችን አዳምጠው፣ ጥፋተኛውን ኮንነው፣ አስታርቀው፣ ይቅር አባብለው፣ ጉልበት አሳስመው አንዳንዴ ደግሞ ሁለቱ ወገኖች በጉዳዩ ላይ እንዳያስቡበት የጥሞና ጊዜ ሰጥተው ሸንጎ የሚበትኑበት ሂደት ነው፡፡ "አውጫጭኝ" ከሀገረሰባዊ ሽምግልና ጋር ተመሳሳይነት ቢኖረውም በመጠኑ ይለያል፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው በ"አውጫጭኝ" ፍርድ አይሰጥም፡፡ በተቃራኒው በሀገረሰባዊ ሽምግልና በጥፋተኛው ግለሰብ ላይ የካሳ ቅጣት ሊወሰን ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የ"አውጫጭኝ" ዋና ዓላማ ወንጀለኛውን አጋልጦ ለዘመናዊ ዳኝነት ማስተላለፍ ሲሆን ሀገረሰባዊ ሽምግልና ግን ጉዳዩ ወደ ዘመናዊ ዳኝነት ከመድረሱ በፊት (የግለሰቦቹ ገበና አደባባይ ሳይወጣ) በሀገር ሽማግሌ የሚያልቅበት ሂደት ነው፡፡

"አውጫጭኝ" ሁሉም የአካባቢው ነዋሪዎች (ከህጻናት በስተቀር) እንዲሳተፉ የሚያስገድድ ሲሆን የሀገር ሽማግልና ግን ተቃራኒ ወገኖችን፣ የሀገር ሽማግሌዎችንና ጥቂት ታዛቢዎችን ብቻ የሚያካትት ነው፡፡

### 3.2.1.4 ማኅበራዊ መሰረት

ማኅበራዊ መሰረት የሚጠናውን ፎክሎር የሚከውነውን የማኅበረሰብ ክፍል፣ የትኛውን ማኅበራዊ ደረጃ እንደሚያሳይና በክዋኔው ውስጥ የማኅበረሰቡ ተሳትፎ ምን እንደሚመስል ያስረዳል፡፡ "አውጫጭኝ" በአብዛኛው በቅርብ ዘመናዊ የፍትሕ ተቋም (ፖሊስ ጣቢያ ወይም ፍርድ ቤት) በሌለው ገጠራማ አካባቢ ህብረተሰቡ ወንጀሉን ፈጽሟል ብሎ ያመነበትን ግለሰብ ለዘመናዊ የፍትሕ ተቋም አሳልፎ የሚሰጡበት አሰራር ነው፡፡ ባህላዊ የዳኝነት ስራርአቱ

“አውጫጭኝ” እድሜ (ከህጻናት) በስተቀር ማኅበራዊ ደረጃ፣ እምነት፣ ሙያ፣... የማይለይሁሉንም የማህበረሰብ ክፍላሳታፊ ስርዓት ነው፡፡ አስረጅ እንመልከት፦

> /የጥሩንባ ድምጽ ከሩቅ ይሰማል ጭቃሹም ሙሉ ቀን አመሸ ከአስተዳዳሪው በደረሰው ትዕዛዝ መሰረት የአካባቢው ነዋሪ ዕውስ እንዲወጣ ያሳስባል/ ጡጥ ...ጡጥ ጡጡጡጥ ... በጎበና አውራጃ ለምትገኙ ነዋሪዎች በሙሉ ዛሬ ተጠዋቱ ሁለት ሠዓት ጀምሮ ተደረሳችሁ ታራስ ሴቶችና ሕጻናት በስተቀር “አውጫጭኝ” እንድትወጡ አስተዳዳሪው አዘዘዋል፡፡ /የጥሩንባ ድምጽ እየራቀ ይሄዳል.../ አለኸኝ (2009፣ 12) (አፅእኖት የኔ)

ከሰረዙ ለመረዳት እንደምንችለው በቅርቡ ከወለደች ሴትና ከህጻናት በስተቀር ሸንጎውን መታደም የሁሉም የአካባቢው ነዋሪ የውዴታ ግዴታ ነው፡፡ ይሄም የሚሆንበት ዋነኛው ምክንያት የአውጫጭኙን ፍትሐዊነት እና ተጠያቂነት ጥያቄ ውስጥ ላለመክተት ነው፡፡ በ“አውጫጭኝ” ተጠርጣሪው ግለሰብ በሌለበት ምንም አይነት ውሳኔ አይተላለፍም፡፡ ከተጎጂው ቤተሰቦች ጋር በቀጥታ የተያያዘ ከሆነ ልጁ የሞተበት ሰው እንኳን ቢሆን ሸንጎውን ለመታደም ይገደዳል፡፡ አስረጅ እንመልከት፦

> አቶ ተሁሉ፡- (የዳኞቹን ዝምታ ሲያዩ) የታል ታዲየ ታለ ይመጣና ይጠየቃ ?
>
> መሪጌታ ፡- ልጁ ሙታበት ለቅሶ ላይ ነው እኮ ነው የሚል፡፡
>
> አቶ ተሁለ እዚህስ የሞተው ሰው አይደለም ? የሰው አሬሳ አጋድሞ የራሱን ቢየሸሞነሙኑ ምን ዋጋ አለው አድርጎታል ተብሎ ከተጠረጠረ ይጠራ አለኸኝ (2009፣ 21)
>
> ---
>
> መሪጌታ፡- ..../ተዳኞቹ/ተማክረው ምሽትየዋ እንድየት ሁና ይሆን /ወደ አቶ ተሁለ ተጠግተው /ምሽትየው እንድትጠራ አማክረው /ና ማነህ አንድ ሎሌ በፍጥነት ፊታቸው ይቆማል/ በፍጥነት ትፈለጊያለሽ ብለህ የሚችን ምሽት ይዘሀት ና /ሎሌው ይኸዳል/
>
> አስረኬ፡- ተቅሰብለባ በመነሳት /እንድየት ነው አስክሬን ትታ የምትመጣ !
>
> ሙሉ ቀን ፡- ዝም በይ አንቺ ከላባ ሲየት!

አያሌው፡- እህ እንዬ የወንድሜን ሬሳ ጥዬ የመጣሁት አንሶ ነው እሷ የምትመጣ ? አለኝኝ (2009፣ 25)

ከጥቅሶቹ ለመረዳት እንደምንችለው አያ በላይ (ሴት ልጁ በሞተችበት በማግስቱ)፣ ባንቺይርጋ (ባለቤቷ "ምስጢሩ" በተገደለ በማግስቱ)፣ አያሌው (ወንድሙ በሞተበት በማግስቱ)፣...በአውጫጭኙ ተገኝተው "ምስጢሩ"ን ገድሎ ቤቱን ያቃጥላል ብለው የሚጠረጥሩት ሰው ካለ እንዲመሰክሩና አንዳንድ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ታዘዋል። ይሄ ደግሞ የአውጫጭኙን አሰራር መርህ ያሳያል።

**ማኅበራዊ መሰረት** በ"አውጫጭኝ" የተባለው ተውኔት ውስጥ፣ የቅርብ ዘመን የፍትሕ ተቋማት እንደፖሊስ ወይም ፍርድ ቤት በሌለበት መንገድ፣ ማኅበረሰቡ ራሱን በፎክሎራዊ መርህና የማህበራዊ ስርዓት መሰረት ወንጀል መመለከት እና መፍታት የሚችል እንደሆነ ይታያል። የአውጫጭኙ ስርዓት ሕጻናትን ከማህበራዊ ድርሻ በስተቀር ሌላ ማንኛውም እድሜ ባላቸው እንዲተሳሰሩ እና ውሳኔ እንዲወስኑ የሚጠይቅ ነው። ከተቀመጡት አስረጃዎች እና የተወሰኑ ንግግሮች እንደታወቀው፣ ተዳኞቹ አካባቢ ነዋሪዎች መሆናቸው እንዲሁም በሰባት እሴቶች አስተማማኝነት፣ ፍትሐዊነት፣ የተለዋዋጭ የማኅበረሰብ ተጠያቂነት እንደሚሰሩ ይታወቃል።

**ዋና ትኩረቶች፦ የማኅበራዊ ተቋማት አቀፍ ድርሻ** — "አውጫጭኝ" የመስመር ላይ የማይሆን ፍትሕን በየአካባቢው ሕዝብ ማድረግ እንደተለመደ ያሳያል።

**የሕዝብ አጋርነትና የአሰራር ድርሻ** — አካባቢው ሁሉም ነዋሪዎች ካልተሰኘው የህግ ተቋም በተመለከተ አንፃፃፅ በፍትሐዊ ተውኔት ውስጥ በተሳትፎ ይገኛሉ።

**አካባቢያዊ ባህላዊ ፍትሕ አዋጅ** — "ዘመናዊ የፍትሕ ተቋማት ሳይኖሩ፣ አውጫጭኝ እንደሚያሳይው ፎክሎራዊ መርህ የተግባር ትርፍ እና ትስስር እንደሚኖረው ይገለጻል።

**በጾታ የተገደበ ብቻ አለመሆኑን** — በሚሰጥበት ትዕዛዝ እንደተሰኘው በአካባቢው ሰዎች ሁሉ እንዲሁም በወንድ አባላት ብቻ ሳይሆን ሴቶችም ከህጻናት በስተቀር ውሳኔው ላይ እንዲካተቱ ይገለጻል። **የሚወጣው**

ከፍ ያለ የማኅበራዊ ተጠያቂነት፣ እምነታዊ ውሳኔ እና ፎክሎራዊ መርህ በአካባቢያዊ ሕዝብ በእምነት የተቀበለ መሆኑን ይገልጻል። ይህ ስርዓት የፍትሕን አስፈላጊነትና የሰብዓዊ ክብር ማዕከላዊነት በፍላጎት ያስረዳል።

#### 3.2.1.5 ግለሰባዊ አውድ

አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከወን የግለሰቡ ሕይወት ምን እንደሚመስል፣ ፎክሎራዊ ጉዳዩ ከግለሰቡ ኑሮ፣ ሀሳብና ስሜት ጋር ያለው መስተጋብር ይንጸባረቃል። ይህም ከግለሰቡ መንፈሳዊ፣ አስተዳደራዊና ባህላዊ ማንነት ጋር ሊያያዝ ይችላል። ከዚህ ቀጥዬ ፎክሎራዊ ጉዳዩ ከገጸባህሪያቱ ህይወት ጋር እንዴት እንደሚቆራኝ አሳያለሁ። ቀደም ሲል በማኅበራዊ መሠረት ላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት "አውጫጭኝ" ሁሉን አካታች ነው። በዚህም የተነሳ ማኅበረሰቡ እርስበርስ በደንብ ይተዋወቃል። ማን የት እንደሚወል፣ ማን ምን እንደሚሰራ፣ ማን ምን እንዳቀደ፣ ማን ከማን ጋር እንደሚስማማና እንደማይስማማ፣...ይታወቃል። ይሄ ደግሞ ግለሰቦች የጎረቤታቸቸውን ምስጢር በመፈልፈል እንዲጠመዱ ያደርጋቸዋል። አንዱ የሰማውን ለአንዱ ያቀብላል። በራሱ አፍ መናገር የማይፈልገውን ደግሞ ለእረኛ ከፍሎ ያስገጥማል። እረኞች በቃላዊ ግጥም ለአየሩ ይዘፍኑታል። እረኛን ወሬውን ከማን ሰማኸው ብሎ የሚጠይቀው የለም። እረኛ እንደ ጋዜጠኛም እንደ ወሬ አቀባይም (whistleblower) ነው። አስረጅ እንመልከት፦

> ሞቼ፡- እኔ የምጠረጥረው የሚች የምሽቱን ወንድም አስቻለው ሆዴን ነው! ይህንንም ልል የቻልኩት ተይህ በፊት ሚች ሚስጥሩና አስቻለው ድንበር ገፋህብኝ በሚል ሰበብ በጠብ መለያየተቸውን አውቃለሁ ኃላ ሚስጥሩ የአስቻለውን እህት ባንቺይርጋን ስላገባት አስቻለው በቁጭት ነዶ አስደፈርሽኝ አያለ ነጋ ጠባ ታባቱ ጋር እሰጥ አገባ ይገጥም እንደነበር ሰምቻለሁ፤ ኸረ እንዳውም እንደደፈረኝ ተግሬ በታች ባላደርገው እያለ ሲፎክር በጆሮዬ ሰምቻለሁ! በዚያ ላይ ደግሞ በየቀኑ ሲወርድ ሲወጣ እረኛው ሁሉ በህቱ የተነሳ እየወረፈ አላሳልፍ ስላለው አምርሮ ይሆናል። አለኸኝ (2009፣ 14)

በ"አውጫጭኝ" አሰራር አንድ ግለሰብ በአንድ አስነዋሪ ወንጀል ተከሰሰ ማለት ወንጀሉን በእርግጠኝነት ፈጽሞታል ማለት አይደለም። ተከሳሹ ዉንጀላውን ውድቅ የሚያደርግ መከራከሪያ ያቀርባል። መከራከሪያው አሳማኝ ሆኖ ከተገኘ ክሱ ተሽሮ ወደሌላ ክስ ይኬዳል። በ"ምስጢሩ" ጉዳይ የተሰበሰበው ሸንጎ በርካቶችን ተጠርጣሪ አድርጓል። ከእነዚህም ውስጥ ለዚህ አውድ ተስማሚው ሞቼ የ"ምስጢሩ"ን ሚስት የባንቺ ይርጋን ወንድም የከሰሰበት አጋጣሚ ነው። ሞቼ አስቻለው ምስጡሩን ሊገድሉት ይችላሉ ብሎ ከሚጠረጥራቸው ሰዎች መካከል

ዋነኛው መሆኑን ለሸንጎው ያስረዳል። ይሁንና የሞቼ ክስ በልመንህ ውድቅ ይደረጋል። አስረጅ እንመልከት፦

> ልመንህ፦ መነሾዬ ተፊቱ ጥቆማ ነው... እረኛው ሲገባ ሲወጣ አየወረፈ ስላስቸገረው ነው ያለ ባልሳሳት... እረኛውን አየዞረ የሚያስገጥመው ማን ሁኖ ነው ቀድሞ... ደግሞ አንዳች ሸር ቢሸርብይ እንድሁ አያስገጥምም፤ ሆን ብሎ፤ ወይ እራሱ ገድሎ ባስቻለው ሊደፈድፍ አስቦ ነው። አለኸኝ (2009፣ 18) (ሰረዝ የኔ)

በ"ምስጢሩ" ሞት ሞቼ አስቻለውን ቢከስም ልመንህ ግን ይሄን ሁሉ ያደረገው ራሱ ሞቼ ነው በማለት ክሱን ይገለብጥበታል። በልመንህ ክስ መሰረት አስቻለው በእህቱ ባል በ"ምስጢሩ" ላይ ጥላቻ እንዲያድርበት ለእረኞች የሚያስገጥመው፣ "ምስጢሩ"ን የገደለው፣ ቤቱን ያቃጠለው፣... ራሱ ሞቼ ነው። ልመንህ መከራከሪያውን ሲያጠናክር እንዲህ ይላል፦

> ልመንህ፦ እዝህም ባልፈጠመው የሚደነፋው ፊሪ ላለመባል ነው እንጂ እሱ እንኳንስ ይቅርና ሰው.....አይጥ! እንኳ ..../ ሕዝቡ አይጥ ሲባል አይጥ አይጥ እያለ ይንጫጫል ፤ አስቻለው እመር ብሎ በፍርሀት ተዳኞች ፊት ይቆማል/... ይኸ ሰው እንኳንስ ሰው ይቅርና ምናምንም መግደል አይሆንለትም፤ ተልጅነታችን አንስቶ በረኝነቱም አውቀዋለሁ....ቀበሮ በጎቻችንን ሊያድን ሲመጣነኳ በጎቹን ትቶ ነበር እግሬ አውጭኝ የሚል ቤቱም ቢሆን ዶሮ ንኳ አያርድም ደም ይፈራል፤ ስለት ሲያይ ይበረግጋል። ታላመናችሁ የገዛ እህቱ ትመስክር! "ምስጢሩ" (2009፣ 16-18) (ሰረዝ የኔ)

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደምንችለው ልመንህ የሞቼን ክስ ውድቅ ማድረግ ችሏል። ሞቼ ካቀረበው ውንጀላ አንጻር የልመንህ መከራከሪያ ከበቂ በላይ ነው። ይሄ ሲባል ግን ልመንህ ሞቼ ላይ የገለበጠው ክስ ልክ ነው ማለት አይደለም። የሞቼን ክስ ውድቅ የሚያደርግ ሌላ ግለሰብ ደግሞ ይነሳል። እዚህ ላይ በዋናነት ለማንሳት የፈለኩት ፎክሎራዊ ጉዳዩ ከግለሰቡ ሕይወት ጋር ምን ያህል በጥብቅ የተቆራኘ እንደሆነ ነው። ከሰረዙ እንደምንረዳው ልመንህ አስቻለው "ምስጢሩ"ን እንዳልገደለ ያቀረበው መከራከሪያ እንዴት በሸንጎው ድጋፍ እንዳገኘ ልብ ይሏል። ነዋሪው ጉዳዩን መወያየት ትቶ አይጥ የሚፈራውን አስቻለውን ሲያብሸቀው እንመለከታለን።

ይሄ ደግሞ ነዋሪው እርስበርሱ ምን ያኽል እንደሚተዋወቅ፣ መስተጋብሩ ምን እንደሚመስል፣ ሕይወቱን፣ ማህበራዊ ደረጃውን፣… ያስገነዝበናል፡፡

### 3.2.1.6 ሁኔታዊ አውድ

ሁኔታዊ አውድ ማህበረሰቡ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን የሚከውንበትን ሁኔታና ፎክሎራዊ ጉዳዩ ለማህበራዊ ህይወቱ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይህም አካላዊ መቼቱን፣ የተሳታፊዎችን ማንነትና ሚና፣ ክዋኔውን የሚገነዘቡባቸውን ህግጋት፣ በከዋኙናበታዳሚዎቹ መካከል ያለውን ተግባቦት፣ የክዋኔውን አተረጓጎም፣ በየደረጃው የሚከናወኑ ድርጊቶችንና ተግባራትን እንዲሁም ቅደም ተከተላቸውን ያካትታል፡፡ "ምስጢሩ" ውስጥ የምንመለከተው ፎክሎራዊ ጉዳይ "አውጫጭኝ" የተባለው ማኅበረሰቡ ተሰብስቦ ወንጀለኛውን ግለሰብ የሚያጋልጥበት ሂደት ሲሆን ይህንን የመሰለ ቅደም ተከተል አለው፡፡

በመጀመሪያ ለነዋሪው መሰባሰብ ምክንያት የሚሆን ወንጀል ማንነታቸው በግልጽ ባልታወቀ አካላት ሊፈጸም ይገባል፡፡ ቀጥሎ የአካባቢው ሹም እና የሃይማኖት አባቶች ስለ ጉዳዩ መረጃ ይደርሳቸዋል፡፡ የአካባቢው ሹም ጉዳዩን ያጣራና በማግስቱ በጠዋት ነዋሪው የተለመደ የመሰብሰቢያ ስፍራ (ብዙ ጊዜ ትልቅ ዋርካ ዛፍ ወይም ደግሞ ተራራማ ስፍራ) ላይ እንዲሰባሰብ በጭቃ ሹሙ አማካኝነት ይነግራል፡፡ ጭቃ ሹም ጥሩንባ እየነፋ መረጃውን ያስተላልፋል፡፡ ሰዉ ይሰበሰባል፡፡ የአካባቢው ሹምና የሃይማኖት አባቶች ቦታ ቦታቸውን ይይዛሉ፡፡ የተፈጸመውን ወንጀል ይናገራሉ፡፡ ከዚያም ያለ ምንም ፍርሃት ሆነ ይሉኝታ ወንጀለኛውን እንዲያጋልጡ ያሳስባሉ፡፡ ከዚያም ጉዳዩን ፈጽሞ ይሆናል ብለው የሚጠረጥሩት ሰው ካለ እጅ እያወጡ በማስረጃ የተደገፈ ጥቆማ እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡

በዚህ መልኩ አንዱን ተከሳሽ አንስተው አንዱን ሲጥሉ ከዋሉ በኋላ የመጨረሻዎቹኝን ሦስት ተጠርጣሪዎች እንደ አካባቢው ልማድ ቃለ መሃላ ወይም ደግሞ ወንጀለኛ ሆኖ የተገኘውን ግለሰብ እግዚብሔር ይቀጣዋል ተብሎ የሚታመንበት (መሬት ላይ የተደረደረ መሣሪያ መዝለል የመሰለ) ፈተና ይሰጣል፡፡ ሁሉም ፈተናውን ካለፉና ወንጀለኛው አሁንም ካልተገኘ እንደ ወንጀሉ ክብደትና ቅለት ለወደፊት ጥንቃቄና ቁጥጥር እንዲያደርጉ ማሳሰቢያ ተሰጥቶ ሸንጎው ይበተናል፡፡ ወንጀሉ ከባድ ከሆነ ግን መንግስት በጉዳዩ ላይ ጣልቃ እንዲገባ ይደረጋል ("አውጫጭኝ" እጅግ ቆየት ባለው ጊዜ ይደረግ የነበር የፍትሕ ስርዓት ነው)፡፡ ከሞላ

ጎደል በ"አውጫጭኝ" ወቅት በየደረጃው የሚከናወኑ ድርጊቶችንና ተግባራት እንዲሁም ቅደም ተከተሉ ከላይ የተጠቀሰውን ይመስላል።

## 3.3 የፎክሎራዊ ጉዳዩ (የ"አውጫጭኝ") ማህበራዊና ሀገራዊ ፋይዳ

ማህበራዊና ሀገራዊ ልማዶች በማህበረሰብ እንዲሁም በሀገር ደረጃ ያላቸው ሁለንተናዊ አስተዋጽኦ የጎላ ነው። ይህ ክፍል በ"ምስጢሩ" ተውኔት ውስጥ በሰፊው የተዳሰሰውን "አውጫጭኝ" የተባለውን ባህላዊ የፍትህ አሰጣጥ ሥርዓት እና ማህበራዊ እንዲሁም ሀገራዊ ፋይዳውን በጥልቀት ይዳስሳል።

"አውጫጭኝ" ዘመናዊ የፍትህ ተቋማት (ፖሊስ ጣቢያ፣ ፍርድ ቤት፣ አቃቢ ሕግ፣...) በሌሉባቸው ገጠራማ አካባቢዎች ወንጀለኛን ለመለየትና ለፍርድ ለማቅረብ የሚያገለግል ባህላዊ ሥርዓት ነው። በዚህ ሥርዓት መሰረት የአካባቢው ሹም፣ የሃይማኖት አባቶች እና ነዋሪዎች በጋራ በመሆን ወንጀለኛውን ለይተው ለመንግስት ያስረክባሉ። ይህ ሂደት የአቃቢ ሕግን ሚና በከፊል የሚተካ ሲሆን፣ በ"አውጫጭኝ" ጥፋተኛ የተባለ ግለሰብ በቀጥታ ለፍርድ እንደማይቀርብ ልብ ሊባል ይገባል። ይልቁንም ፍርድ ቤት ቀርቦ ለተከሰሰበት ወንጀል ማስረጃ እንዲያቀርብ እና ክሱን እንዲክድ ይጠየቃል። ክሱ አሳማኝ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር ውሳኔ አይተላለፍም። በ"አውጫጭኝ" ሥርዓት በጥርጣሬ ብቻ ተነስቶ ሰዎች አይፈረድባቸውም፤ ይልቁንም በማስረጃ የተደገፈ ክስ ያስፈልጋል።

ምንም እንኳን "አውጫጭኝ" በአንጻራዊ ሁኔታ ግልጽነት እና ተአማኒነት ያለው ሥርዓት ቢሆንም፣ እንደማንኛውም ባህላዊ ሥርዓት የራሱ የሆኑ ድክመቶች አሉት። ለምሳሌ፣ በባህላዊ እምነቶች ተጽዕኖ ስር የወደቀ ነው። በ"ምስጢሩ" ተውኔት ውስጥ እንደምናየው፣ ወንጀሉን የፈጸመው ግለሰብ በግልጽ ካልታወቀ እና በርካታ ተጠርጣሪዎች ካሉ፣ "አራት የተቀባበለ መሣሪያ" የተባለ ባህላዊ ዘዴ ጥቅም ላይ ይውላል። በዚህ ዘዴ መሰረት፣ ተጠርጣሪዎቹ በተራ በተቀባበለው መሣሪያ ላይ እንዲዘሉ ይደረጋል። በአካባቢው ማህበረሰብ እምነት መሰረት ወንጀሉን የፈጸመው ሰው መሣሪያውን መዝለል አይችልም፤ ይልቁንም ይቆስላል ወይም ይሞታል። ይህ እምነት ከዘመናዊው የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዕውቀት ጋር የማይጣጣም እና አመክንዮአዊ ያልሆነ ነው። በተውኔቱ መጨረሻ ላይ እንደታየው አያ በላይ ባልፈጸሙት ወንጀል በባረቀ መሣሪያ እግራቸውን ይመታሉ። ይህም የ"አውጫጭኝ" ሥርዓት ምንም እንኳን

ግልጽ እና ቀጥተኛ ቢመስልም፣ በባህላዊ እምነቶች ተጽዕኖ ስር በመውደቁ ምክንያት ፍትሃዊ ያልሆነ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል ያሳያል።

ይህ ሲባል ግን "አውጫጭኝ" ምንም ጠቀሜታ የለውም ማለት አይደለም። በተቃራኒው፣ ይህ ባህላዊ የፍትህ አሰጣጥ ሥርዓት በዘመናዊው የፍትህ ሥርዓት ባልተዳረሱ አካባቢዎች የማህበረሰቡን ሰላምና ደህንነት ለመጠበቅ ወሳኝ ሚና ተጫውቷል። በተጨማሪም፣ ዛሬ የምንጠቀምባቸው ብዙዎቹ የወንጀል እና የሕግ ጽንሰ-ሐሳቦች ከጥንታዊ ባህላዊ ሥርዓቶች እንደ "አውጫጭኝ" የተወረሱ እና ለዘመናዊው ዓለም እንዲዋጡ ተደርገው የተሻሻሉ ናቸው። "አውጫጭኝ" እንደ ባህላዊ ቅርስ እና እንደ ታሪካዊ የፍትህ አሰጣጥ ዘዴ መታየት ይኖርበታል። በተጨማሪም "አውጫጭኝ" ከነ ድክመቶቹ ለሀገር እድገትና ስልጣኔ፣ እንዲሁም ለዜጎች ንቃተ ህሊና እና ተሳትፎ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

ስለሆነም "አውጫጭኝ" ምንም እንኳን ዘመናዊ ባይሆንም፣ በኢትዮጵያ ታሪክ እና ባህል ውስጥ ትልቅ ቦታ ያለው ባህላዊ የፍትህ አሰጣጥ ሥርዓት ነው። ጥናቱ እንዳመለከተው ይህ ባህላዊ ሥርዓት በተለያዩ መንገዶች ለማህበረሰቡ እና ለሀገር እድገት አስተዋጽኦ አድርጓል። ሆኖም ግን፣ ከዘመናዊው የፍትህ አስተሳሰብ አንጻር ሲታይ የሚታዩትን ድክመቶች በመቅረፍ የበለጠ ፍትሃዊ እና አሳማኝ እንዲሆን ማሻሻያዎችን ማድረግ አስፈላጊ ነው።

### 3.3.1 የ"ተጠየቅ" ተውኔት ፎክሎራዊ አውድ ትንተና

- . **ፎክሎራዊ የግጭት መፍትሄ ሥርዓት** በተውኔቱ ውስጥ የተቀመጠው የሽማግሌ መነሳሳት እና አስተዳደር በቅድሚያ የታሪካዊ ፎክሎራዊ የግጭት መፍትሄ መረጃ ነው። ሽማግሌዎች በመዘርፉ የመነኮሳነት፣ የመገናኛ ቅድመ ልማድ እና የማህበረሰብ ዘዴ ማሳየት ይደረጋል። እነዚህ ሽማግሌዎች እንደ መለኮታዊ ፈራጆች የሚቆጠሩት የባህል የመንግስት መቀመጫ ናቸው።

- . **የባህላዊ ባለሀብትነት እና አካባቢ የግል መወዳደር** በተውኔቱ ውስጥ የታየው አቶ ካሳና ወ/ሮ አጀቡሽ መካከል የተፈጠረው በጤና እክል ምክንያት የባልነት ግዴታቸውን መወጣት ባለመቻላቸው በትዳር ልይ የሚመጣውን መዘዝ እና ማህበረሰቡ መፍትሔ የሚለውን መንገድ ምን እንደሚመስል ማህበረሰቡ ውስት ያለውን ባህል የሚኖረውን ፎክሎራዊ ያሳያል። ይህ እንዲሁም የባህላዊ የትዳር ግንኙነት ደንብና ውድቀት በአካባዊ ባህል ቅኝት እንዴት እንደሚታወቅ ያቀርባል።

- . **የፎክሎር ባህላዊ ስርአት የማህበረሰቡ ማስተማማኝ ሥርዓት** ነው የአካባቢ ሽማግሌዎች መሰብሰብ እና መወሰን የባህላዊ መፍትሄ መንገድ ነው። ይህ እንደ ፎክሎራዊ ሥርዓት በአቅሙ መንፈስ ተግባራዊ ሲሆን፣ የማህበራዊ እምነትና አንድነት ድንኳን እንደሆነ ይታያል።
- . **የግል ችግርን እና የህብረተሰብ ተግባር** በመናገርና በተውኔት ውስጥ የታየው በተመለከተው የእርቁን ሂደት መሪ በመሆን የፎክሎር የህብረተሰብ ተግባር ነው። ተውኔቱ የአካባቢ የህዝብ አካላትን በመስበክ አንደኛ ችግኝን ለአጠቃላይ መፍትሄ እንዴት እንደሚቀርበው ያሳያል።
- . **የቃላትና የአነጋገር ፎክሎራዊ ቅርጸ** በተውኔቱ ውስጥ የተጠቀሱ ቃላት፣ የአነጋገር ዘይቤ፣ አንዳንድ ባህላዊ አቀማመጦች (ምሳሌዎች፣ ተምሳሌት ቃላት፣ አንቀጸ ቃላት) ፎክሎራዊ ቅርፅን እንዴት እንደሚያሳዩ መታየት ይገባል።

> **"ተጠየቅ"** ተውኔት ፎክሎራዊ አውድ በመሆኑ፣ የተለያዩ የህዝብ ባህላዊ አቅሞችን በመቀላቀል አንደኛ የግል ችግርን በማህበረሰብ መሰረት መፍትሄ የሚያቀርብ ማዕከላዊ ፎክሎራዊ ተውኔት ነው።

### 3.3.1.1 ፍቻዊ አውድ

ፍቻዊ አውድ በፎክሎራዊ ጉዳዩ ምን ለማለት እንደተፈለገ የሚመረምርና ማኅበረሰቡ ስለሚከውናቸው ፎክሎሮች ያለውን ግንዛቤና አረዳድ እንዲሁም ፎክሎሩን ለመከወን ያነሳሳውን ጉዳይና የትኛውን የህይወት ገጽታ እንደሚያሳይ ይዳስሳል።

**ማኅረሰቡ "ተጠየቅ"ን ለመተግበር ያነሳሳው ምንድን ነው?**

"ተጠየቅ" በአማራ ክልል በዋናነት በጎጃምና በጎንደር የሚተገበር ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴ ነው። ተበድያለሁ ብሎ የሚያምን ግለሰብ በሀገር ሽማግሌ (በዳኛ) ፊት ይቀርብና በዳዩን "ተጠየቅ" ይላል። ዳኞች ወይም ተከሳሹ "ጠይቅ" ካላለ በስተቀር ከሳሽ አቤቱታውን አያሰማም።

"ተጠየቅ" ውስጥ አቶ ካሳ በመጀመሪያ ከሳሽ ሆነው የቀረቡ ሲሆን በስተመጨረሻ ግን ተከሳሽ ሆነው እናገኛቸዋለን። ባለቤቴንና ልጄን አስሸፍቷል በሚል እረኛቸው ዕውነቱን ዳኞች ፊት

ያቀረቡት አቶ ካሳ አድርጓል ብለው ያመኑትን ሁሉ አንስተው በሚወነጅሉበት ቅጽበት ወይዘሮ አጀቡሽ ድንገት ይደርሱና ክሱን አቶ ካሳ ላይ ይገለብጡታል። አስረጅ እንመልከት፦

...አጀቡሽ፡- "ተጠየቅ"!

አቶ ካሳ፡- ባልጠየቅ

አጀቡሽ፡- ኧረ "ተጠየቅ"!

አቶ ካሳ፡- ባልጠየቅ

መሀል ዳኛ፡- "ተጠየቅ" እንጂ ጌታው

አቶ ካሳ፡- ይቅርብኝ፣

መሀል ዳኛ፡- እንዴት

አቶ ካሳ፡- የግል ጉዳይ ነው ጌታዬ ይተውት

እኔንም አይበጀኝ እሷንም አይጠቅማት። /ንዴቱ ያይላል/

የቤትን ገመና በቤት እንጂ መፍታት

ድብቅ፣ ሽሽግ አድርጎ ሳይሰማ ጎረቤት ደሳለኝ (2013፣ 41)

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደምንችለው አቶ ካሳ "ተጠየቁ" ሲባሉ "ባልጠየቅ" በማለት ክሱ እንዳይቀርብባቸው ሲቃወሙ እንመለከታለን። ምንም እንኳ አቶ ካሳ "ባልጠየቅ" ብለው እምቢ ቢሉም ከሳሽ ወይዘሮ አጀቡሽ የራሳቸው ጉዳይ ብለው አልተናገሩም። በዚያ ፋንታ የዳኞቹን ወይም የአቶ ካሳን ፈቃድ ጠይቀዋል። ይሄ ከ"ተጠየቅ" ደንቦች ውስጥ አንዱ ነው። ከሳሽ መናገር ስለሚችል ብቻ መናገር አይችልም። ጉዳዩ በዳኞች እና በጀማው ፊት መቅረብ ይችላል አይችልም የሚለውን የሚወስነው ተከሳሹ ወይም ዳኛ ነው።

አቶ ካሳ ከባለቤታቸው ጋር ባልጋ ዙሪያ የገጠማቸው ጊዜያዊ ችግር ለቅናት ዳርጓቸዋል። ይሄ ቅናት አድጎ ከልጃቸው ወዳጅ ከእረኛቸው ከዕውነቱ ጋር ነገር ሳይጀምሩ አልቀሩም የሚል ግምት ውስጥ እንዲገቡ አድርጓቸዋል። ከባለቤታቸው ከወ/ሮ አጀቡሽ ጋር የገቡት ጠብ ምንጩም ይሄው ቅናት ነው። አቶ ካሳ ታድያ ከመንፈቅ ወዲህ የገጠማቸውን ስንፈተ ወሲብ በአደባባይ እንዲቀርብ አልፈለጉም። ወደ ርዕስ ጉዳዩ አብይ ጥያቄ ማኅበረሰቡ "አውጫጭኝ"ን ለመጠቀም ያነሳሳው ምንድን ነው ወደሚለው ስንመጣ ሁለት መልስ እናገኛለን። የመጀመሪያው የተጣላን ለማስታረቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ተበዳይን ለመካስ ነው።

**በ"ተጠየቅ" ለማለት የተፈለገው ምንድን ነው?**

ተውኔቱ የሚጠናቀቀው ወይዘሮ አጀቡሽ እና አቶ ካሳ ችግራቸውን በግልጽ ለሀገር ሽማግሌ ካሰሙ በኂላ አቶ ካሳ ለችግራቸው መፍትሔ የሚፈልጉበት፣ ወይዘሮ አጀቡሽ ደግሞ ጉዳዩን ጊዜ ወስደው የሚያስቡብት የጥሞና ጊዜ ተሰጥቷቸው ነው፡፡ በ"ተጠየቅ" ለማለት የተፈለገው ዋነኛው ነገር የእርቅ አስፈላጊነት ነው፡፡ ጸብ በህይወታችን ውስጥ ልንከላከለው የማንችለው ነገር ነው፡፡ ባልና ሚስት ይጣላሉ፡፡ ድንበርተኞች ይቀያየማሉ፡፡ ወንድማማቾች ይኮራረፋሉ፡፡ ባልንጀራሞች ይተዛዘባሉ፡፡ ባላንጋራቸው ጥር ይነካከሳሉ፡፡... በዚህ ጊዜ ታድያ እርቅ ብቸኛው መፍትሄ ነው፡፡ ተበደልኩ የሚል ዳኛ (የሀገር ሽማግሌ) ፊት ቀርቦ "ተጠየቅ" ይላል፡፡ ተከሳሹ "ልጠይቅ" ይላል፡፡ ከሳሽ ክሱን ያቀርባል፡፡ ተከሳሽ ይከላከላል፡፡ ... የሀገር ሽማግሌ ግራ ቀኙን አዳምጦ ፍርድ ይሰጣል፡፡ ለከሳሽ እንደ ጉዳቱ መጠን ካሳ ይቆረጥለታል፡፡ ባላንጋራዎች ጉልበት ይሳሳማሉ፡፡ እርቅ ይወርዳል፡፡ ሠላም ይሰፍናል፡፡

ማኅበረሰቡ ስለ ፎክሎራዊ ጉዳዩ ("ተጠየቅ") ያለው አረዳድ ምንድን ነው?

ወይዘሮ አጀቡሽ ሆኑ አቶ ካሳ "ተጠየቅ"ን የሚመለከቱት እንደ ፍትሕ ተቋም ነው፡፡ አቶ ካሳ በእረኛቸው በዕውነቱ የተታለሉ መስሎ በተሰማቸው ጊዜ አቤቱታቸውን ለሀገር ሽማግሌ አስምተዋል፡፡ ወ/ሮ አጀቡሽም አቶ ካሳ በሽማግሌ ፊት እንዲጠየቁላቸው አድርገዋል፡፡ ከዚህ በመነሳት ማኅበረሰቡ "ተጠየቅ"ን የሚመለከተው እንደ አንድ የፍትሕ ተቋም ነው ብለን መደምደም እንችላለን፡፡

### 3.3.1.2 ተቋማዊ አውድ

ተቋማዊ አውድ ፎክሎራዊ ጉዳዩ የት ቦታ እንደሚከወን፣ በምን ዓይነት ተቋማት አማካይነት እንደሚተገበር እና ይህ አተገባበር የሚያስገኘውን ማህበራዊ ፋይዳ ይመረምራል፡፡ "ተጠየቅ" በሚለው ተውኔት ውስጥ እንደታየው፣ ይህ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት የሚከናወነው በባህላዊ ፍርድ ቤቶች ወይም በሽማግሌዎች መሪነት በሚተዳደሩ ስብሰባዎች ላይ ነው፡፡ ተበድያለሁ የሚል ሰው በድሎኛል ብሎ የሚያስበውን ግለሰብ በዳኛ (የሀገር ሽማግሌ) ፊት አቅርቦ "ተጠየቅ" በማለት የደረሰበትን በደል ይገልጻል፡፡ ዳኞቹ ሁለቱንም ወገኖች በጥሞና ካዳመጡ በኂላ እርቅ እንዲወርድ የሚያስችል ሀሳብ ወይም ውሳኔ ያስተላልፋሉ፡፡

በ“ተጠየቅ” ሥርዓት ውስጥ የተለያዩ ተቋማት ወይም አካላት ሚና ይጫወታሉ፡፡ እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- ባህላዊ ፍርድ ቤቶች/ሽማግሌዎች፦ እነዚህ አካላት የግጭት አፈታት ሂደቱን የሚመሩ፣ ክርክሩን የሚያዳምጡ እና ፍትሃዊ ውሳኔ የሚያስተላልፉ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በማህበረሰቡ ውስጥ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን የሚያደርጉ ባህላዊ ሕጎችን እና እሴቶችን በመተግበር ሂደቱን ይቆጣጠራሉ፡፡

- የማህበረሰብ አባላት፦ የማህበረሰብ አባላት በ“ተጠየቅ” ሥርዓት ውስጥ እንደ ምስክር፣ አማካሪ ወይም የእርቅ ፈጣሪ ሆነው ይሳተፋሉ፡፡ የእነሱ ተሳትፎ ለሂደቱ ተአማኒነት እና ተቀባይነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

- ቤተሰብ እና ዘመድ አዝማድ፦ ቤተሰብ እና ዘመድ አዝማድ በተከራካሪ ወገኖች መካከል እርቅ እንዲወርድ በማድረግ ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በተለይም በግጭቱ ውስጥ ያልተሳተፉ የቤተሰብ አባላት ገለልተኛ አማካሪዎች በመሆን ሁለቱን ወገኖች ለማቀራረብ ይረዳሉ፡፡

አስፈላጊ ሲሆን፣ ለተጎጂው ወገን ካሳ ይከፈላል፡፡ የካሳው ዓላማ ተጎጂው ቂም በቀልን በመርሳት እና ለሰላምታ እጁን እንዲዘረጋ ያስችለዋል፡፡ “ተጠየቅ” አብዛኛውን ጊዜ የሚጠናቀቀው ሁለቱን ወገኖች በማስታረቅ ነው፡፡ በ“ተጠየቅ” ተውኔት ውስጥ እንደታየው፣ አቶ ካሳ እና ወ/ሮ አጀቡሽ በሽማግሌዎች አማካይነት ስምምነት ላይ ደርሰዋል፡፡

የዚህ ዓይነቱ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት በማህበረሰቡ ውስጥ ሰላም፣ ፍቅር እና መተሳሰብን በማስፈን ረገድ ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡ በተጨማሪም፣ በማህበረሰቡ ውስጥ የፍትህ ስርዓቱን ተደራሽነት በማሳደግ፣ በተለይም ዘመናዊ የፍትህ ተቋማት በሌሉባቸው አካባቢዎች የዜጎችን መብት ለማስከበር ይረዳል፡፡ ይህም በአጠቃላይ ለሀገሪቱ ሰላምና እድገት አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

### 3.3.1.3 የማኅበረሰቡ የተግባቦት ሂደት አውድ

ተግባቦታዊ አውድ የሚጠናውን ፎክሎራዊ ጉዳይ ከሌላ የፎክሎር ቅርጽ ጋር እያነጻጸረ ይመረምራል፡፡ ይህም የሚጠናውን ፎክሎራዊ ጉዳይ ቅርጽ፣ አንዱን ከሌላው ጋር ያለውን ዝምድናና ማኅበረሰቡ አንዱን ከሌላው ለመለየት የሚጠቀምባቸውን ዘዴዎች ያካትታል፡፡

“ተጠየቅ” ከሽምግልና ጋር ይመሳሰላል፡፡ “ተጠየቅ”ን ቀደም ሲል በ“ምስጢሩ” ተውኔት ካየነው “አውጫጭኝ” ጋር ልናነጻጽረው እንችላለን፡፡ “አውጫጭኝ” እና “ተጠየቅ” የሚለያዩባቸው በርካታ ነገሮች ቢኖሩም የሚመሳሰሉባቸው ጉዳዮችንም ማንሳት እንችላለን፡፡ “ተጠየቅ” እና “አውጫጭኝ” ሁለቱም በአብዛኛው በገጠራማው ክፍል የሚከወኑ ሲሆን “ተጠየቅ” ተበዳይ የደረሰበትን በደል የሀገር ሽማግሌና ታዛቢ ፊት አቅርቦ ፍትሕ እንዲሰጠው የሚጠይቅበት መንገድ ነው፡፡ “አውጫጭኝ” ደግሞ የአካባቢው ማኅበረሰብ አንድ ትልቅ ዋርካ ስር ወይም ደግሞ ተራራማ ስፍራ ላይ ተሰብስቦ ባልታወቁ አካላት ተፈጽሟል የተባለውን ወንጀል የሚያወጣጣበት ሂደት ነው፡፡

በ“አውጫጭኝ” በመጨረሻ የአውጫጭኙ ሰብሳቢዎች ፍርድ አይሰጡም፡፡ ወንጀለኛውን ከለዩ በኋላ ለበላይ አካል አሳልፈው ይሰጣሉ፡፡ “ተጠየቅ” በተቃራኒው የሽምግልናው መሪዎች ሁለቱን ወገኖች ካዳመጡ በኋላ ፍርድ ይሰጣሉ፡፡

በ“አውጫጭኝ” የተከሰሰው ግለሰብ ይግባኝ መጠየቅ ይችላል፡፡ ተከሳሹ ራሱን በአግባቡ መከላከል ከቻለና ሽንነውን ማሳመን ከቻለ ለተከሰሰበት ወንጀል ተጠያቂ ነህ የሚለው የለም (ተጨባጭ ማስረጃ እስካልቀረረበበት ድረስ)፡፡ በ“ተጠየቅ” ግን ተከሳሹ ሽማግሌዎች የወሰኑበትን ቅጣት በጸጋ ለመቀበል ይገደዳል፡፡ ይሄ ሲባል ግን በ“ተጠየቅ”ም ክርክር የለም ማለት አይደለም፡፡ በ“ተጠየቅ”ም ተከሳሹ የተከሰሰበትን ጉዳይ ጨርሶ ሊክድ ይችላል፡፡

“አውጫጭኝ” ሁሉንም የማኅበረሰብ ክፍሎች የሚያጠቃልል ሲሆን “ተጠየቅ” በተቃራኒው ተካሳሾችን፣ ዳኞችን (የሀገር ሽማግሌ ) እና ጥቂት ታዛቢዎችን ብቻ የሚያካትት ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ በ“አውጫጭኝ” ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰው በቀጥታ ወደ ዘመናዊ ዳኝነት ከመላኩ በፊት ጉዳዩን በ“ተጠየቅ” የሚጨርስበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ ለማጠቃለል ያህል ሽምግልና፣ “አውጫጭኝ” እና “ተጠየቅ” በመጠኑ ቢለያዩም ሶስቱም የአካባቢ እና የቤተሰብን እንዲሁም የሀገርን ሁለንተናዊ ሠላም ለማረጋገጥ የሚያገለግሉ መሆናቸው ያመሳስላቸዋል፡፡

### 3.3.1.4 ማኅበራዊ መሰረት

“ተጠየቅ”ን የሚከውነው የማኅበረሰብ ክፍል እና የሚያሳየው ማኅበራዊ ደረጃ፦

“ተጠየቅ” በገጠርም ሆነ በከተማ የሚከወን ባህላዊ የግጭት አፈታት መንገድ ነው፡፡ ምንም እንኳን ቅርፁና አካሄዱ ሊለያይ ቢችልም፣ በሁለቱም አካባቢዎች በስፋት ይተገበራል፡፡ አንዳንድ

ጊዜ ዘመናዊ የፍትሕ ተቋማት እንኳን አንዳንድ ጉዳዮችን በእርቅ እንዲፈቱ ይመክራሉ፡፡ ይህም የ"ተጠየቅ"ን ማኅበራዊ ተቀባይነት ያሳያል፡፡ በተለምዶ "ተጠየቅ" የሚከናወነው በሀገር ሽማግሌዎች፣ በባላገሮች፣ በሃይማኖት አባቶች ወይም በማኅበረሰቡ ዘንድ በሚታመኑ ሰዎች ነው፡፡ ይህም የሽምግልናውን ሂደት ፍትሃዊ እና ተዓማኒነት ያለው ያደርገዋል፡፡ "ተጠየቅ" በተለያዩ ማኅበራዊ ደረጃዎች ላይ ባሉ ሰዎች መካከል ሊከወን ይችላል፡፡ ከዚህ አንጻር የተወሰነ ማኅበራዊ ደረጃን ብቻ የሚያሳይ አይደለም፡፡

በ"ተጠየቅ" ውስጥ የማኅበረሰቡ ተሳትፎ፦

ከ"አውጫጭኝ" በተለየ መልኩ "ተጠየቅ" ሰፊ የማኅበረሰብ ተሳትፎን አይጠይቅም፡፡ በዋናነት ባለጉዳዮቹ (በዳይ እና ተበዳይ)፣ የሀገር ሽማግሌዎች/አሸማጋዮች እና አስፈላጊ ከሆነ ጥቂት ታዛቢዎች በሥርዓቱ ላይ ይገኛሉ፡፡ ሆኖም ግን፣ ሌላው የማኅበረሰብ ክፍል በተዘዋዋሪ መንገድ ሊሳተፍ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ጎረቤቶችና ቤተዘመዶች ቡና በማፍላት፣ ምግብ በማዘጋጀት፣ ቦታ በማሳመር፣ እና ሌሎች ዝግጅቶችን በማድረግ ለ"ተጠየቅ" ሥነ ሥርዓት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡ ነገር ግን እንደ "አውጫጭኝ" ሁሉ በሁለቱ ወገኖች መካከል ጣልቃ አይገቡም ወይም ሀሳብ እንዲሰጡ አይጠየቁም፡፡ የእነሱ ሚና የ"ተጠየቅ" ሂደት በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲከናወን ድጋፍ መስጠት ነው፡፡

### 3.3.1.5 ግለሰባዊ አውድ

"ተጠየቅ"ን የመሰለ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከወን የግለሰቡ ሕይወት ምን እንደሚመስል፣ ፎክሎራዊ ጉዳዩ ከግለሰቡ ኑሮ፣ ሀሳብና ስሜት ጋር ያለው መስተጋብር አብሮ ይንጸባረቃል፡፡ "ተጠየቅ" ከማኅበረሰቡ ህይወት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ መሆኑን በአስረጅ ጥቅስ ማሳየት ይቻላል፡፡

የ"ተጠየቅ" ተውኔት ገጸባህርያት ህይወት ምን ይመስላል?

የገጸባህርያት ህይወት ምን ይመስላል ስንል ገጸባህሪያት በእለት ተእለት ህይወታቸው የሚያከናውኗቸውን ድርጊቶች፣ የገቢ ምንጫቸውን፣ ሞያቸውን፣ አካባቢያቸውን፣ የእርስበርስ ግንኙነታቸውን፣... ያጠቃልላል፡፡ አስረጅ እንጀመልከት፦

አቶ ካሳ፡- ዘሬ... የተከበረ ነበረ የታፈረ
ቅድመ አያቴ ደጅ አዝማች አበረ
የእሱም ልጅ ግራ አዝማች ደመላሽ አባቴ ነበረ፡፡

እኔም ካገር ጋር የምኖር ራሴን ጠብቄ

ገበሬ ነኝ ጌቶች

ክረምቱን ከበጋ ሳልታክት የማመርት። የከብቶች ጌታ …

/በቁጭት/ ምን ዋጋ አለው

ደጉ ዘመን አልፎ ከንቱው ዘመን መጥቶ

የዘር ማንዘር ውርሴ በዘመን ተትቶ

የአባቶቼ ማዕረግ በጊዜ ተከድቶ

የባላባቶች ዘር ደረጃው ተረስቶ

ተዚህ ላይ ደረስኩኝ ተዘመን ድሪቶ።… ደሳለኝ (2013፣ 19)

አቶ ካሳ ይህንን የሚሉት ዕውነቱ በድሎኛል ብለው ሽማግሌ ፊት ቀርበው ራሳቸውን ሲያስተዋውቁ ነው። ገጸባህሪው ስለ ዘር ሀረጋቸው፣ ስለ ከብቶቻቸው፣ ስለ ገበሬነታቸው፣ ስለ ታታሪነታቸው፣… በልበ ሙሉነት ይናገራሉ። ይሄ ደግሞ በተዘዋዋሪም ቢሆን ገጸባህሪያቱ ስለሚኖሩበት አካባቢና ስለ ዘመኑ መንፈስ ፍንጭ ይሰጠናል። የተውኔቱ የጊዜ መቼት በ1980 ዓ.ም ሲሆን የተውኔቱ የቦታ መቼት  ደግሞ ጎጃም ክፍለ ሀገር ነው። “ዘሬ… የተከበረ ነበረ የታፈረ…” የሚለው የአቶ ካሳ ቁጭት ያዘለ ቀረርቶም የፊውዳሉ ስርዓት መውደቅ ያስከተለውን የማኅበራዊ መደብ መፋለስ እና የገገርው መደብ የገጠመውን ስነልቦናዊ ቀውስ ያሳየናል። ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ከጭሰኛው መደብ የመጣውን የዕውነቱን ንግግር እንመለከታለን።

በል ተከሳሽ ራስህን አስተዋውቅ ቅረብ ና።

ዕውነቱ ፡-

/ጋቢውን አስተካክሎ ለዳኛው እና ለጀማው የአክብሮት ሰላምታ ይሰጣል / …

ዕውነቱ እባላለሁ በአጭሩ እረኛ ነኝ ስሙ-ጥሩ ፣ እጀ-ኩሩ ።

መሀል ዳኛ ፡- ማለፊያ ! ! ….

ቢሆንም ያስፈልጋል ማብራሪያ ፣

አንተነትህን መርምሮ ማንጠሪያ ።

ዕውነቱ ፡- በኋላ ቀር ልማድ በአገራችን ባህል

ዘሬ ከዚህ ግባ ባይሆን የማይባል

በስልጣን ኮረቻ ባይፈናጠጡ

ዙፋን ላይ ቁጭ ብለው መሪነት ባይሰጡ

ደጅ አዝማች ቀኝ አዝማች ሹመት ባይጨብጡ

ዙፋን ላይ ቁጭ ብለው መሪነት ባይሰጡ

ደጅ አዝማች ቀኝ አዝማች ሹመት ባይጨብጡ ከሀብት ማማ ወጥተው ምን ባይቀናጡ

አያቴ ነበሩ በደግነት የተመረቁ

በህዝባዊ ኑሮ የታወቁ

የተራራቀን አቀራርበው የተጋጨን የሚያስታርቁ፡፡ ... ደሳለኝ (2013፣ 20)

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደምንችለው ዕውነቱ በመጠኑ ተራማጅ ይመስላል፡፡ ተወልዶ ያደገው ዘርና ሀረግ በሚቆጠርበት ገጠራማ አካባቢ ቢሆንም በጊዜው ፈንድቶ ከነበረው የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም መርህ ጋር ሲራመድ እንመለከተዋለን፡፡ ሰዎችን በዘር ሀረጋቸው ሳይሆን በሥራቸው ሲያወድሳቸው እንመለከታለን፡፡ አያ ካሳ የየትኛው ጌታ ልጅ እንደሆኑ እንጂ አያት ቅድመ አያቶቻቸው የሰሩትን በጎ ሥራ አልጠቀሱም፡፡ ዕውነቱ ስለ እረኝነቱ በኩራት ከተናገረ በኋላ አያት ቅድመ አያቶቹ እንደ አያ ካሳ ጌቶች ባይሆኑም ትጉህና መልከም ሰዎች እንደነበሩ ይጠቅሳል፡፡ ይሄ ደግሞ ስለ ገጸባህሪያቶቹ ማንነት፣ ስለ አካባቢያቸው፣ ስለ ፖለቲካዊ ዝንባሌያቸው፣ ስለሞያቸው፣ ከማኅበረሰቡ ጋር ስላላቸው መስተጋብርና ዓለምን ስለሚመለከቱበት መንገድ ፍንጭ ይሰጠናል፡፡

### 3.3.1.6 ሁኔታዊ አውድ

ሁኔታዊ አውድ ማህበረሰቡ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን የሚከውንበትን ሁኔታና ፎክሎራዊ ጉዳዩ ለማህበራዊ ህይወቱ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይህም አካላዊ መቼቱን፣ የተሳታፊዎችን ማንነትና ሚና፣ ክዋኔውን የሚገነዘቡባቸውን ህግጋት፣ በከዋኙና በታዳሚዎቹ መካከል ያለውን ተግባቦት፣ የክዋኔውን አተረጓጎም፣ በየደረጃው የሚከናወኑ ድርጊቶችንና ተግባራትን እንዲሁም ቅደም ተከተላቸውን ያካትታል፡፡

ከአካላዊ መቼት አንጻር “አውጫጭኝ” እና “ተጠየቅ” በአብዛኛው የሚከወኑት ከመንደሩ ብዙም ሳይርቅ የሚገኝ ትልቅ (የዋርካ) ዛፍ ስር ሲሆን በየደረጃው የሚከናወኑ ድርጊቶችና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡ አስረጅ እንመልከት፦

/መስክ መሃል ቅርንጫፉን ያሰፋ ዋርካ ይታያል፡፡ ከዋርካው ስር የተጋደመ ወፍራም ግንድ አለ፡፡ ዳኛው እና ጀማው ቦታቸውን ይዘዋል፤ ዕውነቱ በቀኝ በኩል አቶ ካሳ ደግሞ በግራ በኩል እንደ ቆሙ ጀማው ይቀላቀላቸዋል፡፡ ዳኛው እንዲቀመጡ በምልክት ያዝዛሉ/

መሀል ዳኛ ፡- እንደምን አደራችሁ ?

ጀማው ፡- / በአንድነት / እዝጌር ይመስገን…

እስኪ ከሳሽ ማነህ ተነስ… ማንነትህን ለጀማው አድርስ፡፡

አቶ ካሳ፡- /በጥንቃቄ ተነስቶ አለባበሱን ካስተካከለ በኋላ ለዳኛውና ለጀማው ለሰላምታ ይሰግዳል/

ክቡር ዳኛ እኔ ነኝ ከሳሽ

ስሜም ካሳ ደመላሽ፡፡ ደሳለኝ (2013፣ 17)

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደምንችለው ሽምግልናው የሚካሄደው ትልቅ ዋርካ ስር ሲሆን ከሀገር ሽማግሌዎች መካከል ዳኞችና ታዛቢዎች ተመርጠው በየቦታቸው ይሰየማሉ፡፡ ከዚያ ተከሳሽ በቀኝ፣ ከሳሽ በግራ ይቆምና ስማቸውን እንዲናገሩና ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ ይጠየቃሉ፡፡ ከዚያም ከሳሽ ክሱን ያቀርባል፡፡ ዳኞች ያዳምጣሉ፡፡ ተከሳሽ ራሱን እንዲከላከል እድል ይሰጠዋል፡፡… ዳኞች ግራ ቀኙን ያዳምጣሉ፤ይመካከራሉ፤ ይወስናሉ፡፡ አንዳንዴ ደግሞ ልክ ፍርድ ቤት ለተጨማሪ ሌላ ወር ቀጥሮ እንደሚሰጠው ሁሉ የጥሞና ጊዜ በመስጠት ተካሳሾችን ያሰናብታሉ፡፡ ለማሳያነት ያህል የወ/ሮ አጀቡሽ እና የአቶ ካሳን ታሪክ ማንሳት እንችላለን፡፡ አቶ ካሳ በአልጋ ዙሪያ የገጠማቸው ችግር የጤና እክል መሆኑን ስላልተገነዘቡ ከባለቤታቸው ደብቀዉት ቆይተዋል፡፡ በስተመጨረሻ ግን የጤና እክል ሊሆን እንደሚችል አንድ ሰው ይነግራቸዋል፡፡ ዳኞችም ይሄንን ከግምት ውስጥ በማስገባት የአንድ ሳምንት ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጧቸዋል፡፡ አስረጅ እንመልከት፡-

መሀል ዳኛ፡- /ከግራና ከቀኛቸው ይማከራሉ፤ ጀማው ጎን ለጎን መጎሻሸምና ማውራት ይጀምራል፡፡ ዳኛው ጥቂት ቆይተው በማጨብጨብ/…

ከአቶ ለሁሉ አይጠፋምና መድኃኒቱ

ሳምንት እድሜ ሰጥተንሃል እስኪታይ ውጤቱ፡፡

አንቺም!

አይበልጥምና እስከ ዛሬ ከጠበቅሽው

ውጤቱ እስኪታወቅ ለሳምንት ታገሸው፡፡

እኛም ብይን እንሰጣለን የዛሬ ሳምንት

የሰንበት እለት እሁድ በዚሁ ሰዓት

ሁላችሁም እንድትገኙ በጀማው ፊት፡፡

/ሁሉም በእሽታ ከወገባቸው ዝቅ ሲሉ መብራት ድርግም ብሎ ይጠፋል/ ደሳለኝ (2013፣ 45)

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደምንችለው በተጠየቅ የዳኞች ውሳኔ ሁልጊዜም በዘላቂ መፍትሄ የሚጠናቀቅ አይደለም፡፡ ጉዳዩ የማሰቢያ ጊዜ የሚያስፈልገው ከሆነ ለሌላ ተለዋጭ ቀጠሮ ይራዘማል፡፡ ይሄ የሚሆንበትም ዋነኛው ምክንያት መጥፎ ውሳኔ ላይ ላለመድረስና ተከትሎት የሚመጣውን ጸፀት ለመቀነስ ነው፡፡ ከሞላ ጎደል በ“ተጠየቅ” በየደረጃው የሚከናወኑ ድርጊቶችና ተግባራት እነዚህ ናቸው፡፡

## 3.4 የፎክሎራዊ ጉዳዩ ማኀበራዊና ሀገራዊ ፋይዳ

ማህበረ ሀገረሰባዊ ልማዶች ሲከወኑ በማኀበረሰብ ሆነ በሀገር ደረጃ ያላቸው ሁለንተናዊ አስተዋጽኦ የጎላ ነው፡፡ ቀደም ሲል ተደጋግሞ እንደተገለጸው “ተጠየቅ” የሽምግልና አይነት ነው፡፡ “ተጠየቅ” ተብድያለሁ የሚል ግለሰብ በዳይ ተብዬውን የሀገር ሽማግሌ ፊት አቅርቦ “ተጠየቅ” በማለት የፈጸመበትን በደል አስረድቶ ዳኝነት የሚያገኝበት ሂደት ነው፡፡ የእርቅ ወይም የሽምግልና ግብ በሁለት ባላንጋራዎች መካከል ሠላም ማውረድ ነው፡፡ ባላንጋራዎቹ በጋብቻ የተጣመሩ ጥንዶች፣ ወንድማማቾች፣ ጓደኛሞች፣ የሥራ ባልደረቦች፣ ...ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በሁለቱ ወገኖች መካከል ሠላም መውረዱ የሚያመጣው ፋይዳ የላቀ ነው፡፡ አስረጅ እንመልከት፦

> መሀል ዳኛ ፡- ዛሬ ይህን ጀማ ያጠራነው … በአባቶቻችን ደንብ መሰረት ሰላም እንዲሰፍን፣ አብሮነታችን እንዲጠነክር፣ የመረዳዳት የመቻቻል ባህላችን እንዳይጓደል ፤ ሰው ሲጣላ ችግር ሲፈጠር ፣ ሁሉም ሰው እንዳቅሙ ፍትሕን እንደ ዳቦ በእጁ እንዳይቆርስ ፣ እንደ ወግ እንደ ባህላችን ስርዓት ልናስከብር ፣ ችግሩ ስር ሳይሰድ እልባት ማበጀት የእኛ የአባቶች የነበረ ፣ ያለ ፣ የሚኖር ተግባራችን ነውና ፤ የበደለም ክሶ ፣ የተበደለም ተክሶ ፣ እርቀ ሰላም እንዲወርድ … ስልጣን ሳያስፈራን ፣ ዝምድና ሳይጎትተን ፣ ጉቦ ሳያታልለን ፣ ወደ ማንም ሳናዘነብል፣ በእኩልነት ሁሉንም ልንዳኝ ነውና ዛሬ የተገኘን የተፈጠረውን ችግር

እናያለንና ... እስኪ ከሳሽ ማን ነህ ተነስ፣ ማንነትህን ለጀማው አድርስ። ደሳለኝ (2013፣ 17)

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደምንችለው "ተጠየቅ" ሰላምን እና አንድነትን ለማስፈን የሚያገለግል ባህላዊ የሽምግልና ስልት ነው። ይህ ባህል በግለሰብ፣ በማኅበረሰብ እና በሀገር ደረጃ የሚያስገኛቸው በርካታ ፋይዳዎች አሉት። ከእነዚህም መካከል በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፦

**1. በግለሰብ ደረጃ፦**

- የስነልቦና እፎይታ፦ በደል የደረሰበት ግለሰብ "ተጠየቅ" በማለት ችግሩን ለሽማግሌዎች ሲያቀርብ የስነልቦና እፎይታ ያገኛል።
- የፍትህ ማግኘት፦ በዳዩ በሽማግሌዎች ፊት ሲጠየቅ እና ፍትሃዊ ውሳኔ ሲሰጥ የተበደለው ግለሰብ የፍትህ ስሜት ያድርበታል።
- ከበቀል መዳን፦ "ተጠየቅ" የበቀል እርምጃን በመከላከል ግለሰቦች ችግራቸውን በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ያግዛል።
- የግንኙነት መሻሻል፦ በተጋጩ ወገኖች መካከል የነበረው ቅራኔ በሽምግልና ሲፈታ የግንኙነታቸው ይሻሻላል።

**2. በማኅበረሰብ ደረጃ፦**

- የሰላም ማስፈን፦ "ተጠየቅ" በማኅበረሰቡ ውስጥ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ በመፍታት ሰላም እንዲሰፍን ያደርጋል።
- አንድነትን ማጠናከር፦ በሽምግልና የተፈቱ ግጭቶች የማኅበረሰቡን አንድነት ያጠናክራሉ።
- የመረዳዳት እና የመቻቻል ባህል መጎልበት፦ "ተጠየቅ" በማኅበረሰቡ ውስጥ የመረዳዳት እና የመቻቻል ባህል እንዲጎለብት ያደርጋል።
- ወንጀልን መከላከል፦ ችግሮች በሰላማዊ መንገድ ሲፈቱ ወንጀል የመከሰት እድል ይቀንሳል።

### 3. በሀገር ደረጃ፦

- የሀገር ሰላም እና መረጋጋት፦ በሀገር ውስጥ የሚኖሩ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ በመፍታት የሀገሪቱን ሰላምና መረጋጋት ለማስጠበቅ ይረዳል።
- ኢኮኖሚያዊ ልማት፦ ሰላም እና መረጋጋት ሲኖር ኢኮኖሚያዊ ልማት ይበረታታል።
- የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ፦ "ተጠየቅ" ሕዝብ በራሱ ጉዳይ ውሳኔ የመስጠት እድል በመስጠት የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን ያግዛል።
- የባህል ቱሪዝም፦ የ"ተጠየቅ" ባህል ለባህል ቱሪዝም እድገት አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል።

### 3.4.1. የ"ሽምጋይ" ተውኔት ፎክሎራዊ አውድ ትንተና

መንደርደሪያ፡- ይህ ተውኔት ቀደም ሲል ከተተነተኑት ሁለት ተውኔቶች በአንጻሩ ለየት ይላል። "ምስጢሩ" እና "ተጠየቅ" ሙሉ በሙሉ በተተነተኑበት ፎክሎራዊ ጉዳይ የሚያጠነጥኑ ሲሆን "ሽምጋይ" በአንጻሩ አንድ ወጥ የሆነ ፎክሎራዊ ርዕሰ ጉዳይ የለውም። ምናልባትም እንደ አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሊታይ የሚችለው የአለቃ ገብረሃና የሽምግልና ታሪክ ነው። ይሄ አይነቱ ሽምግልና ከ"ተጠየቅ" ሆነ ከሀገረሰባዊ እርቅ ጋር ተመሳሳይ አይደለም። ይሄኛው ሽምግልና ይበልጡን ፖለቲካዊ ነው። ትንተናውም በዚሁ የአለቃ ገብረሃና የሽምግልና ታሪክ ላይ ያጠነጥናል።

#### 3.4.1.1. ፍቻዊ አውድ

ፍቻዊ አውድ በፎክሎራዊ ጉዳዩ ምን ለማለት እንደተፈለገ የሚመረምርና ማኅበረሰቡ ስለሚከውናቸው ፎክሎሮች ያለውን ግንዛቤና አረዳድ እንዲሁም ፎክሎሩን ለመከወን ያነሳሳውን ጉዳይ የሚዳስስ ቢሆንም፣ በ"ሽምጋዩ" ውስጥ በቡድን የሚከወን ፎክሎራዊ ጉዳይ ስለሌለ በተውኔቱ ምን ለማለት እንደተፈለገ አቀርባለሁ።

በተውኔቱ ለማለት የተፈለገው ምንድን ነው?

መንደርደሪያው ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው "ሽምጋይ" ከፎክሎራዊነቱ ይልቅ ፖለቲካዊ ይዘቱ ያይላል። ...ከአጼ ቴዎድሮስ ህልፈት በኋላ የንጉሠ ነገሥቱን መንበር ለመጨበጥ

የነበረው ትንቅንቅ ከፍተኛ ነበር። በንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ እግር የተተኩት አጼ ዮሐንስ በጎጃምና በጎንደር ጥሩ ስም አልነበራቸውም። ብዙ የቀድሞ ሹማምንቶች በንጉሡ ላይ አምጸው ጫካ ገብተው ነበር። ከእነዚህ ሹማምንቶች መካከል  የቀድሞ የእቴጌ መነን አጋፋሪ በጅሮንድ አሞኘ አባተ ይገኙበታል። የሽፍቶቹ አላማ አንድ ቀን እንደ አጼ ቴዎድሮስ ቤተ መንግስት እንገባለን የሚል ነበር። በጊዜው ንጉሥ ለመሆን እነዚህ ሁለት ነገሮች እጅግ በጣም አስፈላጊ ነበሩ። የመጀመሪያው ብርቱ የጦር ሠራዊት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የህዝብ ተቀባይነት ነው። በጅሮንድ አሞኘ ስምንት ሺህ ብርቱ ሠራዊት ቢኖራቸውም የህዝብ ተቀባይነት አልነበራቸውም። በዚያ ላይ ምኒልክን ያህል ተቀናቃኝ ነበረባቸው። የበጅሮንዱ ስጋትም ምኒልክ ቀድሞኝ ይነግስ ይሆናል የሚል ነበር። ለዚህ መፍትሄው ታድያ በጊዜው ከንጉሡ ነገሥቱ ያልተናነሰ ዝና የነበራቸው አለቃ ገብረሃና በፎገራና በአካባቢው ለሚኖረው የጎንደር ሕዝብ የገጽታ ግንባታ ፕሮፓጋንዳ እና ድጋፍ (Endorsement) እንዲሰጧቸው ነበር።

> በጅሮንድ፦ ...ቢያምርብዎ አንዲት ዘገር ሳትነቀነቅብዎ ያልኩትን ይፈፅሙ፣ ያለዚያ ግን ንፍር ዉሃ ቀቅሎዎ ነዋ ያውም እሚራዱን። /ወደ መድረኩ የቀኝ ታችኛ ተገነጠለ - ለጎንታ/ እናንተ ዝነኞች አግዙን እንጂ ያዳግተናል ብቻችንስ።... መቼም ሀገር እምታዉቀውን ሰው ማቀፍ ከሀገር የመተቃቀፍ ያህል ነው። ... ወደው ነው "አሁን ማወደሽ ነው ገጣቢት ንጉስ ምትመርቂ!!?" ታደለ (2009፣ 31)

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደምንችለው በጅሮንዱ አለቃን ቢያንገራግሯቸውም አልተስማሙም። በጅሮንዱ በሕይወታቸውና በቤተሰቦቻቸው     ቢያስፈራሯቸውም ፖለቲካዊ ድጋፍም ሆነ የገጽታ ግንባታ ፕሮፖጋንዳ አልፈጸሙላቸውም። ለዚህ ደግሞ ዋነኛ ምክንያታቸው የእቴጌ መነን እጅ አስታጣቢ የነቡረትን አሞኘ አባተን ፖለቲካዊ ብስለታቸውን ስለሚጠራጠሩ ነው። ለዚህ ዋነኛ ማሳያው ደግሞ አሞኘ አባተ በሕይወታቸውና በቤተሰቦቻቸው አስፈራርተው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር እንዲያሸማግሏቸው ጠይቀዋቸው እምቢ ያሉት አለቃ ገብረሃና፣ ጌታነህ የተባለ ፋቂ ምኒልክ ለፋቂዎችና  ለሌሎች የእጅ ባለሞያዎች ክብር ይሰጣልና እሱ እንዲነግስ ይርዱት ብሎ በለመናቸው ጊዜ የፋቂውን ምክር ተቀብለው ከምኒልክ ጋር መተባበራቸው ነው። የበጅሮንዱ እቅድ አጼ ዮሐንስ መተማ ሄደው ሲሞቱ መንገስ ነበር። አስረጅ እንመልከት፦

> በጅሮንድ፡-     ከሞቱ ደግሞ ቀድሞውን ሲገዳደራቸው የነበረው ምኒልክ ልንገሥ ባይ ነው። ከዚያ አበክረን ግን እኛና እስዎ እናብራለን። እግዜር ብሎ ንጉሡ ነገሥቱ ቢወድቁልን፣ እኛው እንቀድማለን። ድፍን ጎንደር! ድፍን ኢትዮጵያ ድፍን ዓለም የእኛን መንግስትነት ያውቃል። እና እስዎ

> ካገዙን ... የንጉሥ ተክለሃይማኖትን ምኞት እናከስማለን! የንጉሥ ምኒልክን አንኮበር ቤተ መንግሥት እናወድማለን! የንጉስ ሚካኤልን ግዛት እናኮላሻለን! በኢትዮጵያ ላይ እኛ እንነግሳለን! እኛ የቴዎድሮስን አጥንት ተበቅለን፤ የእመቤቴ እቴጌ መነንን አጥንት እንታመናለን! ያኔ ... እኛ እኛ አገር እንገዛለን! ... ብቻ ዋናውና ጠንካራው ጋሬጣችንን ምኒልክን ሸውክ ሰርተው ይጣሉልን፡፡ ታደለ (2009፣ 31)

ቀደም ሲል አለቃ በምኒልክ ላይ በማሴር አልተባበሩም፡፡ ይልቁንም ምኒልክን አግዘዋቸዋል፡፡ ምኒልክም አጼ ዮሐንስ እንዳረፉ ንጉሠ ነገሥትነታቸውን አውጀዋል፡፡ ፋቂ፣ ቀጥቃጭ፣... እየተባልን እየተሰደብን ነው በማለት አቤቱታቸውን ሲያሰሙ የነበሩት እነ ጌታነህም ፍትሕ አግኝተዋል፡፡

> አዋጅ፡- ካሁን ወዲያ አባት ያለህ የአባትህን እሰጥሀለኹ፤ አባትህን መርቅ፡፡ አባት የሌለህ ደግሞ አባትህ እኔ ነኝና ደጅ ጥናኝ ተብለሀል፡፡ ካሁን ወዲያ ድሀ እወደደበት ቦታ በሀይማኖቱ በዘሩ ተከብሮ ይኑር እንጂ በወገን በዘር ልዩነት አይከልከል ተብለሀል! ታደለ (2009፣ 57)

በፎክሎራዊ ጉዳዩ (ሽምግልና) ለመባል የተፈለገው ምንድን ነው ወደሚለው ጥያቄ ስንመለስ በቀዳሚነት የሚነሳው ታዋቂ ሰዎች ወይም ምሁራን ለእጩ የሀገር መሪዎች ድጋፋቸውን ሲሰጡ የግለሰቦችን ፖለቲካዊ ብስለት መሠረት አድርገው እንጂ የመጡበትን አካባቢና ወዳጅነትን ተንተርሰው መሆን እንደሌለበት ነው፡፡ አለቃ ገብረሃናና በጅሮንድ አሞኘ አባተ በእቴጌ መነን ቤተ መንግስት ኖረዋል፡፡ ጓደኛሞችም ነበሩ፡፡ ሁለቱም የጎንደር ሰው መሆናቸው ያመሳስላቸዋል፡፡ ይሁንና አለቃ በጅሮንድ አሞኘ አባተ ለንጉሠ ነገሥትነት ይመጥናሉ ብለው አያምኑም፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው የበጅሮንዱ ፍላጎት ሀገሪቱን ወደ አዲስ ምዕራፍ ማሸጋገር ሳይሆን የቀድሞ ባላንጋራዎቻቸውን መበቀልና የእቴጌ መንን ክብር ማስመለስ ነው፡፡ ይሄ ደግሞ ሀገሪቱን ወደፊት አያራምዳትም፡፡ ጠቅለል ለማድረግ ያኽል በተውኔቱ/ በፎክሎራዊ ጉዳዩ ለማለት የተፈለገው አለቃ ገብረሃናን የመሰሉ ምሁራን ፖለቲካዊ ድጋፍ ( Endorsement) ከማሳየታቸው በፊት የግለሰቡን ብቁነት ማገናዘብ እንዳለባቸው ነው፡፡

### 3.4.1.2. ተቋማዊ አውድ

ተቋማዊ አውድ የፎክሎራዊ ጉዳዩን የሚከናወንበትን ቦታ እና ከቦታው ጋር ያለውን ዝምድና ያሳያል፡፡ በተጨማሪም ፎክሎራዊ ጉዳዩ መከናወኑ በተቋማት ላይ የሚያመጣውን ለውጥ ይዳስሳል፡፡ በ"ሽምጋዩ" ተውኔት ውስጥ እንደ "ምስጢሩ" እና "ተጠየቅ" ሁሉ የቡድን ፎክሎራዊ

እንቅስቃሴ የለም። ትኩረቱ በአለቃ ገብረሃና የግል ሕይወት እና በዘመኑ በነበረው የፖለቲካ ውጥረት ላይ ነው። "ሽምጋዩ" የሚለው መጠሪያ የተሰጠው አለቃ ገብረሃና ለእደ ጥበብ ባለሞያዎች ላደረጉት ውለታ ነው። ለምኒልክ በጻፉት ደብዳቤ የፋቂው ጌታነህን እና የሌሎች ባለሞያዎችን ሕይወት ለዘለዓለም ቀይረውታል። ይህ ዘላቂ ለውጥ የአለቃ ገብረሃና የሽምግልና ውጤት ነው። ስለሆነም፣ በዚህ ተውኔት ውስጥ ሽምግልና ለተጎጂዎች ፍትሕ ማስገኘቱን እንረዳለን። በተጨማሪም፣ ይህ ሽምግልና የተከናወነው በደብዳቤ አማካኝነት ለንጉሡ በመማጸን ነው ማለት እንችላለን። ይህም ሽምግልና በተለያዩ መንገዶች ሊከናወን እንደሚችል ያሳያል።

### 3.4.1.3. የማኅበረሰቡ የተግባቦት ሂደት አውድ

ተግባቦታዊ አውድ የሚጠናውን ፎክሎራዊ ጉዳይ ከሌላ የፎክሎር ቅርጽ ጋር እያነጻጸረ ይመረምራል። ይህም የሚጠናውን ፎክሎራዊ ጉዳይ ቅርጽ፣ አንዱን ከሌላው ጋር ያለውን ዝምድናና ማኅበረሰቡ አንዱን ከሌላው ለመለየት የሚጠቀምባቸውን ዘዴዎች ያካትታል። ሽምግልና ተበድያለሁ የሚል ሰው በሌላ ሦስተኛ ወገን አማካኝነት አቤቱታውን የሚያሰማበት መንገድ ነው። ሂደቱ ይለያይ ይሆናል እንጂ ይሄ አይነቱ ሽምግልና ዛሬም ይተገበራል። የሀገራችንን ጂኦፖለቲካ በማሳያነት መጥቀስ እንችላለን። ታጣቂዎች በመንግስት ላይ ሲያምጹ በሀገር ሽማግሌዎች አደራዳሪነት ስምምነት ላይ ይደርሳሉ። ይሄ የሀገር ሽማግሌዎች ጥረት ሽምግልና ይባላል።

የሽምግልና ቅርጽ ከዘመን፣ ከቦታና ከሁኔታው ክብደት አንጻር ይለያይ ይሆናል እንጂ ግቡ ተመሳሳይ ነው። በተውኔቱ ውስጥ የተመለከትነው ሽምግልና ቅደም ተከተል የሚከተለውን ይመስላል። በአንድ ወገን በዳይ በሌላ ወገን ደግሞ ተበዳይ አለ። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ሁለቱን ወገኖች የሚዳኝ ሦስተኛ ወገን አለ። “ሽምጋይ” የምንለው ጉዳዩን ለሦስተኛ ወገን የሚያደርሰውን አካል ነው። በተውኔቱ ውስጥ ጌታነህ የፋቂውን፣ የሽክላ ሠሪውን፣ የቀጥቃጩን፣ የአንጥረኛውን፣... አቤቱታ ሰብስቦ በአለቃ ገብረሃና አማካኝነት ለንጉሠ ነገሥቱ አድርሷል። ይሄን ሽምግልና ከ“ተጠየቅ” እና ከሀገረሰባዊ ሽምግልና የሚለየው ተካሳሾች በቀጥታ ሀሳባቸውን የሚያሰሙበት እድል የማይሰጥ መሆኑ ነው። በ“ተጠየቅ” ሆነ በሀገረሰባዊ ሽምግልና ተከሳሹ የተከሰሰበትን ጉዳይ ሊክድ ይችላል። የሀገር ሽማግሌዎችም ከሳሽ ማስረጃ እስካላቀረበ ድረስ ውሳኔ አይሰጡም። በዚህኛው ሽምግልና ግን የተከሳሽን ቅሬታ የሚያሰማው አሸማጋዩ ነው። ዳኛው የከሳሽና የተከስሽን ሀሳብ በቀጥታ አያዳምጥም። ሙሉ መረጃው

የሚደርሰው በአሸማጋዩ አማካኝነት ነው። ከሞላ ጎደል በ"ሽምጋይ" ተውኔት የተመለከትነው ሽምግልና ቅርጽ ይህንን ይመስላል።

### 3.4.1.4. ማኅበራዊ መሰረት

ሽምግልና ተበድያለሁ ያለ ሰው አቤቱታውን በሌላ ሦስተኛ ወገን (ሽምጋይ) አማካኝነት የሚያሰማበት የግጭት አፈታት መንገድ ነው። በተውኔቱ ውስጥ አለቃ ገብረ ሐና በጌታነህ እና በንጉሠ ነገሥቱ መካከል አሸማጋይ ሆነው ቀርበዋል። ይህ የሚያሳየው ሽምግልና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ እንኳን ጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችል ነው። በዘመናዊው ዓለምም ሽምግልና በተለያዩ አለም አቀፍ እና አገራዊ ግጭቶችን ለመፍታት እንደ አንድ ዘዴ ጥቅም ላይ ይውላል።

ሽምግልናን የሚያከናውነው የማህበረሰብ ክፍል በባህል፣ በዘመን፣ በስፍራ እና በአጋጣሚ ሊለያይ ይችላል። ለምሳሌ፦

- ሽማግሌዎች፦ በባህላዊ ማህበረሰቦች ውስጥ ሽማግሌዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ አክብሮት እና ተቀባይነት ስላላቸው እንደ አሸማጋይ ሆነው ያገለግላሉ። የእነሱ ጥበብ፣ ዕውቀት እና ተሞክሮ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ይረዳል።

- የሃይማኖት አባቶች፦ የሃይማኖት አባቶችም በማህበረሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ተጽዕኖ ስላላቸው እንደ አሸማጋይ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ። በተለይም በሃይማኖታዊ እሴቶች ላይ ተመስርተው እርቅ እንዲወርድ ያደርጋሉ።

- የማህበረሰብ መሪዎች፦ የማህበረሰብ መሪዎች፣ እንደ አባ ገዳዎች፣ የጎሳ መሪዎች ወዘተ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ተሰሚነት በመጠቀም ግጭቶችን ለመፍታት እና ሰላምን ለማስፈን ይረዳሉ።

- ባለሙያዎች፦ በዘመናዊው ዓለም፣ በግጭት አፈታት ሥልጠና የወሰዱ ባለሙያዎች እንደ አሸማጋይ ሆነው ያገለግላሉ። እነዚህ ባለሙያዎች በተለያዩ ዘዴዎች እና ስልቶች በመጠቀም ወገኖችን ወደ ስምምነት ለማምጣት ይጥራሉ።

ስለዚህ ሽምግልናን “ይሄኛው የማህበረሰብ ክፍል ነው የሚተገብረው” ብሎ ብሎ መናገር አይቻልም። ሽምግልና በተለያዩ ማህበራዊ ክፍሎች፣ በተለያዩ ባህሎች፣ ዘመናት፣ ስፍራዎች እና አጋጣሚዎች ሊተገበር የሚችል ሁለንተናዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ነው።

### 3.4.1.5. ግለሰባዊ አውድ

አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከወን የግለሰቡ ሕይወት፣ የግል አቋም፣ አስተሳሰብና ስሜት በጉዳዩ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። ይህ ተጽዕኖ ከግለሰቡ መንፈሳዊ፣ አስተዳደራዊና ባህላዊ ማንነት ጋር የተቆራኘ ነው። የሽምግልና ሥርዓት በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች ሊተገበር ስለሚችል፣ በተውኔቱ ውስጥ የተገለጸውን የሽምግልና ሂደት የሚመራው የተወሰነ የማኅበረሰብ ክፍል ነው ብሎ መጠቆም አያስችልም። ለምሳሌ፣ በገጠርም ሆነ በከተማ፣ በተለያዩ ማኅበራዊ ደረጃዎች ላይ የሚገኙ ሰዎች ሽምግልና ሊያደርጉ ይችላሉ። ስለሆነም ሽምግልናን የሚተገብረው የማኅበረሰብ ክፍል እንደ ጊዜው እና አካባቢው ሁኔታ ይለያያል።

### 3.4.1.6. ሁኔታዊ አውድ

ሁኔታዊ አውድ ማህበረሰቡ ፎክሎራዊ ጉዳዩን የሚከውንበትን ሁኔታና ፎክሎራዊ ጉዳዩ ለማህበራዊ ህይወቱ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ያሳያል። ይህም አካላዊ መቼቱን፣ የተሳታፊዎችን ማንነትና ሚና፣ ክዋኔውን የሚገነዘቡባቸውን ህግጋት፣ በከዋኙና በታዳሚዎቹ መካከል ያለውን ተግባቦት፣ የክዋኔውን አተረጓጎም፣ በየደረጃው የሚከናወኑ ድርጊቶችንና ተግባራትን እንዲሁም ቅደም ተከተላቸውን ያካትታል።

ይሄ ሽምግልና እንደ “ተጠየቅ” እና እንደ ““አውጫጭኝ”” አንድ ቋሚ መቼት የለውም። ተሳታፊዎቹ ከሳሽ፣ ተከሳሽ፣ አሸማጋይ እና ዳኛ ናቸው። በዚህ አይነቱ ሽምግልና ከሳሽና ተከሳሽ ቀጥተኛ ተሳትፎ የላቸውም። ጉዳዩ የሚያልቀው በአሸማጋዩ እና በዳኛው አማካኝነት ነው። አሸማጋዩ የተከሳሽን አቤቱታ በማዳመጥ (እውነት ሆኖ ካገኘው) ክሱን ለዳኛው ያሰማል። ዳኛው መሬት ላይ ወርዶ ጉዳዩን አያጣራም። ውሳኔውን የሚያስተላልፈው ከአሸማጋዩ ሀሳብ በመነሳት ነው። የጉዳዩን እውነት ማጣራት የራሱ የአሸማጋዩ ሥራ ነው። ይሄ የአሸማጋዩ ገለልተኛ ሚና አቃቢ ሕግ ፍርድ ቤት ውስጥ ካለው ሚና ጋር ይመሳሰላል። አለቃ ገብረሃና የጌታነህንና የባልንጀሮችን አቤቱታ ለንጉሠ ነገሥቱ ከማድረሳቸው በፊት የጉዳዩን እውነትነት ፈትሸዋል። አስረጅ እንመልከት፦

ጌታነህ፡- ከንጉስ እስከ ገባሪ፣ ከደገኛ እስከ ቆለኛ አንድም በችሎት ችሎታዎ፣ አንድም ባቋቋም ፈጠራዎ፣ ደግሞም በተሸጋሪ ጨዋታዎ ታዋቂ ነዎ። አገር ይሰማዎታል። አገር ይታዘዝዎል። ንጉስ ይፈራዎታል። ዝም አይበሉን። እና ... እግዚሃር ቢያሳይዎ፣ መላኩ ቢያመላክትዎ ለምንድን ነው አገርዎ እምትጠየፈኝ አለቃ? ለምንድን ነው እምትገፋኝ? ለምንድን ነው ፋቂ›› እምትለኝ?!

ገብረሐና፡- አገሬ "ፋቂ" ትልሃለች?

ጌታነህ፦ "ፋቂ-ቆዳ ፈቅፋቂ" ያውም...

ገብረሐና፡- እና ከስምህ ሌላ በምን ጥሪኝ ነው እምትላት አገሬን?

ጌታነህ፡- እና "ፋቂ ወግድ!፣ ሽማኔ ወዲያ! ቀጥቃጭ ወግድ፣ ድሃ ወዲያ" ተብለን አያዝኑልንም? አይለምኑልንም አለቃ? አገርዎን አያባብሉልንም? ኧረ እባክዎ እባክዎ? እንዲያው በናበጋው ጊዮርጊስ?

ገብረሐና፡- /ያለ ጠባያቸው በጠና ጥሞና አስጨረሱት/ መሆኑን ዉሎህ ከእረኞች ጋር ነው ልበል? ንግግርህ ጠጠረብኝሳ። ታደለ (2009፣ 14)

ከጥቅሱ ለመረዳት እንደምንችለው አሸማጋዩ አለቃ ገብረሃና የጌታነህንና የባልንጀሮቹን አቤቱታበጥሞና አዳምጠዋል። የቅሬታቸውን እውነትነትም በአመክንዮ ሞግተዋል። አዋዋልህ ከእረኛ ጋር ነው የሚለው ጥያቄም የነጌታነህን ቅሬታ እውነተኛነት ያረጋግጥልናል። አለቃም ከዚህ የጌታነህ አቤቱታ በመነሳት ቅሬታውን አሰምተዋል። ንጉሠ ነገሥቱም በአቤቱታው መሠረት "ካሁን ወዲያ ድሀ እወደደበት ቦታ በሀይማኖቱ በዘሩ ተከብሮ ይኑር እንጂ በወገን በዘር ልዩነት አይከልከል ተብለሀል!" ታደለ (2009፣ 57) የሚል አዋጅ አስነግረዋል። ቀደም ተከተሉም በመጀመሪያ ክሳሽ ክሱን እንደ አለቃ ላለ ተዳማጭነት ላለው ሰው ያሰማል፣ ቅሬታ አድማጩ የጉዳዩን እውነተኛነት ያረጋግጣል፣ እውነት ሆኖ ካገኘው ለበላይ አካል ቅሬታውን ያሰማል፣ የበላዩ አካል ቅሬታውን ሰምቶ ውሳኔ ያስተላልፋል። ከሞላ ጎደል የዚህኛው ሽምግልና ቅርጽ ይህንን ይመስላል።

## 3.5 የፎክሎራዊ ጉዳዩ (የሽምግልና) ማኅበራዊና ሀገራዊ ፋይዳ

ማኅበራዊና ሀገራዊ ልማዶች ለማኅበረሰብና ለሀገር ግንባታ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። የሽምግልና ባህልም ከዚህ የተለየ አይደለም። የሽምግልናው አፈጻጸም ከዘመን፣ ከቦታና ከሁኔታው ክብደት አንጻር ሊለያይ ቢችልም፣ ዓላማው ሰላምና አንድነትን ማስፈን ነው።

"ሽምጋይ" ወይም "አሸማጋይ" በዳይና ተበዳይ መካከል ድልድይ በመሆን ግጭትን በሰላማዊ መንገድ ፈቶ ፍትሕ እንዲሰፍን ያደርጋል። ይህ ባህላዊ ዘዴ በተለያዩ የሕይወት ዘርፎች፣ በተለይም በፖለቲካ፣ ጉልህ ሚና ይጫወታል።

በአሸማጋይ የሚመጣ እርቅ በርካታ ማኅበራዊና ሀገራዊ ፋይዳዎች አሉት። ለአብነት፦

1. የግጭት አፈታትና የሰላም ግንባታ፦ አሸማጋይ ግጭቶችን በሰላም ፈቶ ግንኙነቶችን ያድሳል፤ ዘላቂ ሰላምንም ያሰፍናል። ይህም የማኅበረሰቡን አንድነት አጠናክሮ ልማትን ያቀላጥፋል።

2. ፍትሕ፦ ፍትሐዊ ውሳኔ በመስጠት የተበዳዩን መብት ይጠብቃል፤ በማኅበረሰቡም የእኩልነትና የፍትሐዊነት ስሜት እንዲሰፍን ያደርጋል።

3. ማኅበራዊ ካፒታል፦ ሽምግልና የመተማመን፣ የመከባበርና የመረዳዳት መንፈስን በማጎልበት ማኅበራዊ ካፒታልን ያሳድጋል።

4. ኢኮኖሚ፦ ሰላምና መረጋጋት ለኢኮኖሚ ልማት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። ሽምግልናም ይህን በማስፈን የኢኮኖሚ እድገትን ያፋጥናል።

2. ዴሞክራሲ፦ ሕዝብ በራሱ ጉዳይ ውሳኔ የመስጠት አቅምን በማሳደግ የዴሞክራሲ ሥርዓትን ያጎለብታል።

3. አንድነት፦ የሚፈጠሩ ግጭቶችን በሰላም በመፍታት አንድነትንና ብሔራዊ መግባባትን ያጠናክራል፤ የሀገርን ሰላምና ደኅንነትም ያስጠብቃል።

4. የፖለቲካ መረጋጋት፦ በፖለቲካ ኃይሎች መካከል የሚፈጠሩ ቅራኔዎችን በሽምግልና በመፍታት የፖለቲካ መረጋጋትን ያስፈናል።

ከላይ የተጠቀሱት ጥቂቶቹ ሲሆኑ በአሸማጋይ የሚመጣ እርቅ ሌሎች በርካታ ማኅበራዊና ሀገራዊ ፋይዳዎች አሉት።

# ምዕራፍ አራት

## 4. ማጠቃለያ እና መደምደሚያ

ይህ ጥናት "ሽምጋይ"፣ "ተጠየቅ" እና "ምስጢሩ" በተሰኙ ትውፊታዊ ተውኔቶች ውስጥ የፎክሎራዊ ጉዳዮችን ይዘት፣ ባህሪ እና ፋይዳ በጥልቀት ለመዳሰስ የተሰራ ነው:: ዋና ዓላማው እነዚህ ተውኔቶች የኢትዮጵያን ባህል፣ ማህበራዊ እሴቶች እና ትውፊታዊ እምነቶች እንዴት እንደሚያንፀባርቁ መፈተሽ ነው:: በተጨማሪም እነዚህ ፎክሎራዊ ክዋኔዎች በተውኔቶቹ ውስጥ የሚጫወቱትን ሚና፣ ከተውኔቶቹ ጭብጥ ጋር ያላቸውን መስተጋብር እና ለማህበረሰቡ የሚያስተላልፉትን መልእክት ለማሳየት ያለመ ነው::

ጥናቱ የፎክሎራዊ ጉዳዮችን ይዘት ከመግለጽ ባለፈ፣ ከዘመን አንፃር ያላቸውን ጠቀሜታ መተንተን፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሃይማኖታዊ ፋይዳቸውን መዳሰስ፣ እንዲሁም ፎክሎር በአገር አቀፍ ደረጃ ያለውን ስነ-ጽሑፋዊ አስተዋጽኦ ማሳየትን እንደ ንዑሳን ዓላማዎች አድርጎ ይዞ ተንቀሳቅሷል። ይህንንም ለማሳካት ሰነድ ዳሰሳ እና የተውኔት ትንተናን እንደ ዋና የጥናት ዘዴዎች ተጠቅሟል። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ከኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም፣ ከብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት እና ከሌሎች ተመሳሳይ ምንጮች የተገኙ ሰነዶች ጥናቱን ለማበልጸግ አግዘዋል።

በተውኔቶቹ ውስጥ የተለያዩ የኢትዮጵያ ባህላዊ እሴቶች፣ እምነቶች፣ ሥርዓቶች እና ልማዶች በግልጽ ተንፀባርቀዋል:: "ሽምጋይ" የንጉሠ ነገሥቱንና የሠራተኛውን መደብ ግንኙነት በአለቃ ገብረሐና አማካኝነት የማሳየት ጉዳይ ላይ ያተኮረ ነው:: "ተጠየቅ" ባህላዊ የእርቅ ሥነ-ሥርዓትን እና አፈታቱን ያሳያል:: "ምስጢሩ" ደግሞ በባህላዊ መንገድ "አውጫጭኝ" በመባል የሚታወቀውን፣ ማህበረሰቡ ወንጀለኛን ለመለየት የሚጠቀምበትን ዘዴ ያቀርባል:: እነዚህ ፎክሎራዊ ክዋኔዎች በተውኔቶቹ ውስጥ ጭብጥን ለማሳየት፣ ገጸ-ባህሪያትን ለመግለጽ፣ አስቂኝ ወይም አሳዛኝ ሁኔታዎችን ለመፍጠር እንዲሁም ለማህበረሰቡ የተለያዩ መልእክቶችን ለማስተላለፍ መሳሪያ ሆነው አገልግለዋል::

ጥናቱ የተግባራዊ ቲዎሪ አተያይን በመጠቀም እነዚህ ፎክሎራዊ ክዋኔዎች በማህበረሰቡ ውስጥ የሚጫወቱትን ሚና ዳስሷል። የBaumanን ስድስት የአውድ ዓይነቶች (ፍቺያዊ፣ ተቋማዊ፣ የተግባቦት ሂደት፣ ማህበራዊ መሰረት፣ ግለሰባዊ እና ሁኔታዊ) በመተግበር ተውኔቶቹ

በባህላዊ፣ ማህበራዊ እና ስነ-ልቦናዊ ጉዳዮች ላይ የሚኖራቸውን ተጽእኖ ለማብራራት ሞክሯል። ለምሳሌ የፍቺያዊ አውድ ትንተና የተውኔቶቹን መልእክት ለመረዳት፣ ተቋማዊ አውድ ደግሞ የሚቀርቡበትን ባህላዊ አካባቢ ለማሳየት ይጠቅማል። በተመሳሳይ ሁኔታ ማህበራዊ መሰረት ተውኔቶቹ ከማህበረሰቡ የትኛው ክፍል ጋር እንደሚተሳሰሩ ያሳያል።

ምንም እንኳን ይህ ጥናት በሦስት ተውኔቶች ("ሽምጋይ"፣ "ተጠየቅ" እና "ምስጢሩ") ላይ ብቻ የተገደበ ቢሆንም፣ ስለ ኢትዮጵያ ትውፊታዊ ቴአትር እና ፎክሎር ያለውን ግንዛቤ በማስፋት ረገድ ጠቃሚ ግኝቶችን አስገኝቷል። ጥናቱ እንዳመለከተው ፎክሎር የኢትዮጵያን ባህላዊ እሴቶች፣ ታሪክ፣ ማህበራዊ እምነቶች እና የአኗኗር ዘይቤዎች ለመጠበቅ፣ ለማስተላለፍ እና ለማስረጽ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። በተለይም በተውኔቶቹ ውስጥ የተለያዩ ባህላዊ ሥርዓቶች፣ ልማዶች፣ እምነቶች እና አስተሳሰቦች በግልጽ በመንፀባረቃቸው፣ የማህበረሰቡን ማንነት እና ታሪካዊ አመጣጥ ለመረዳት ያስችላሉ። ከዚህም በተጨማሪ፣ እነዚህ ተውኔቶች በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ አስተያየት በመስጠት፣ በትውልዶች መካከል ግንኙነት እንዲፈጠር፣ ማህበራዊ ትምህርት እንዲሰጥ እና ለመዝናኛም ጭምር እንደሚያገለግሉ ጥናቱ አረጋግጧል። ይህ ጥናት ለቀጣይ ተመራማሪዎች በኢትዮጵያ ፎክሎርና ትውፊታዊ ቴአትር ላይ የበለጠ ጥልቀት ያለው እና ሰፋ ያለ ጥናት እንዲያካሂዱ በር ይከፍታል። በተለይም በሌሎች ተውኔቶችና በተለያዩ የፎክሎር ዘርፎች (እንደ ተረት፣ አባባል፣ ዘፈን፣ ወዘተ) ላይ ተመሳሳይ ጥናቶች መካሄድ ስለ ኢትዮጵያ ባህልና ትውፊት የበለጠ ሰፊ እና ግልጽ ግንዛቤ ለማግኘት ያስጨብጣል። ይህም የኢትዮጵያን ባህል ለመጠበቅ፣ ለማዳበር እና ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ለማስተዋወቅ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

# ዋቢ ፅሁፎች

## ቀዳማይ መዘርዝር


ታደለ አያሌው ፣ (2015 ዓ.ም)፣**ሽምጋይ** (አለቃ ገብረሃና) ፣(ያልታተመ ተውኔት)

አለሽኝ ብርሃኔ (2011 ዓ.ም) ፣ **ምስጢሩ**፣ (ያልታተመ ተውኔት )

ደሳለኝ ተጠየቅ ፣(2013 ዓ.ም)፣**ተጠየቅ** ( ነገሩ አይቆምም) ፣ (ያልታተመ ተውኔት)


## ካልአይ መዘርዝር


ሀገር ፍቅር። (1991)። ልዩ መፅሄት። ማተሚያ ቱ ያልተጠቀሰ።

መንገሻ አማረ።(1992)። "የወገልጤና አዝማሪዎች የሚጠቀሙባቸው ቃላዊ ግጥሞች ይዘት ትንተና። አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ። ያልታተመ።

ማርታ ንጉሴ።(1998)። "የሰላሌ አካባቢ የጉማ ስርአት ክዋኔዎች እና ተውኔታዊ አላባዎች"። አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ። ያልታተመ።

በላይ መኮንን። (1999)። የደቡብ ንግስት ከአፈ ታሪኩ አንፃር"፡ ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል። አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ። ያልታተመ።

ብሩክ ተፈራ።(2004)። "የተከፋኝ ሐገረሰባዊ ልማዶች ስርዓት በመኢኔት ብሔረሰብ" የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር።ያልታተመ።

ብርሃኑ መኮንን። (1973)። "የአማርኛ የሙሾ ግጥሞች ይዘት እና የዘይቤ አጠቃቀም"። አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ።ያልታተመ።

ተመስገን ፋናዬ። (1995)። የዛር ትውፊት እና በውስጡ የሚገኙ ቴአትራዊ አላባውያን በራያ እና ቆቦ አካባቢ"። አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ። ያልታተመ።

ተስፋዬ ገሠሠ። (1966)። "አጭር የኢትዮጵያ ቴአትር ጥናት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው "። የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም።

ደስታ ሎሬንሶ እና ጫንያለው ወልደ ጊዮርጊስ፡፡(2007)፡፡ “የቃቂ ወርዳዎት ታሪክና የጉራጌ ብሔረሰብ ባህል ስነ ቃልና ትውፊታዊ ትውን ጥበባት"፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር፡፡

ደስታ ተክለወልድ፡፡(1962)፡፡ አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ግርማ ተረፈ ጫኔ፡፡(2011)፡፡የህልውናዊነት በእንዳለ ጌታ ከበደ ደርሶ መልስ ውስጥ፡፡ያልታተመ

ፈቃደ አዘዘ፡፡ (2004)፣ ባህልና ልማት በኢትዮጵያ፣ ቁዘማ፣ ፎክሎር (ባህል) እና ልማት በኢትዮጵያ (በፎረም ፎር ሳሻል ስተዲስ የውይይት መድረክ ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ጽሁፎች)፣ ገጽ 97-134፣ ኢክሊፕስ ማተሚያ ቤት፡፡

Abrahams, M. H. (1981). *A glossary of literary terms*. Holt, Rinehart, and Winston.

Alvin, G., & Wilson. (1994). *Living theatre: An introduction to theatre history* (2nd ed.).

Barnard, A., & Jonathan, S. (2002). *Encyclopedia of social & cultural anthropology*. Routledge.

Bascom, W. (1954). Four functions of folklore. *Journal of American Folklore, 67*(266), 333-349.

Bauman, R. (1977). *Verbal art as performance*. Newbury House.

Bauman, R. (1983). The field study of folklore in context. In *Handbook of American folklore*. Indiana University Press.

Bauman, R. (Ed.). (1992). *Folklore, cultural performances, and popular entertainment*. Oxford University Press.

Bell, C. (1997). *Ritual: Perspective and dimensions*. Oxford University Press.

Ben-Amos, D. (1975). Folklore in African society. *Research in African Literature*.

Ben-Amos, D. (1979). Toward a definition of folklore in context. *The Journal of American Folklore, 84*(331).

Ben-Amos, D. (1993). *Theorizing folklore: Towards new perspectives on the politics of culture*.

Berger, P., & Luckmann, T. (1966). *The social construction of reality*. Doubleday.

Best, J., & Kahn, J. V. (1993). *Research in education* (7th ed.). Prentice Hall of India Private Limited.

Dorson, R. M. (1963). Current folklore theories. *Current Anthropology, 4*(1), 93-112. https://www.jstor.org/stable/2739820

Dorson, R. M. (1972). *Concept folklore and folk life studies: An introduction*. University of Chicago Press.

Dundes, A. (1965). *The study of folklore*. Prentice Hall Inc.

Dundes, A. (1972). *Concept folklore and folk life studies: An introduction*. University of Chicago Press.

Dundes, A. (1980). *Interpreting folklore*. Indiana University Press.

Dundes, A. (1989). *Folklore matters: The psychoanalytic study of the Grimm's tales*. University of Tennessee Press.

Dundes, A. (2004). Folkloristics in the twenty-first century (AFS invited presidential plenary address). *Journal of American Folklore, 118*(470), 2005.

Eahleman, J. R., Cashion, B. G., & Basirico, L. A. (1993). *Sociology: An introduction* (4th ed.). Harper Collins College Publishers.

Edwin, Wilson and Alvin, (1994). Goldfarb, Living Theatre: An Introduciton to Theatre Hisotry, 2nd ed.

Fekade, A. (2003). *Teaching material selected and compiled, readers for ETLI 621*. Ethiopian Languages and Literature, MA in Ethiopian Literature and Folklore.

Finnegan, R. (1970). *Oral literature in Africa*. Nairobi University Press.

Finnegan, R. (1992). Oral poetry. In R. Bauman (Ed.), *Folklore, cultural performances, and popular entertainment: A communication-centered handbook*. Oxford University Press.

Fitterman, D. M. (2010). *Ethnography: Step by step* (3rd ed.). Sage Publications.

Geertz, C. (1973). *The interpretation of cultures*. Basic Books.

Hartnoll, Phyllis. (1968). A Concis History of the Theatre. London: Thames and Husson,

Jones, M. O. (1994). *Putting folklore to use: Essays on applied folkloristics*. University Press of Kentucky.

Kothari, C. (2004). *Research methodology: Methods and techniques* (2nd rev. ed.). New Age International Publishers.

Kottak, P. (1994). *Anthropology: The exploration of human diversity*. McGraw-Hill.

Lamphere, L., & Pridel, E. (1974). *Domestic power of women*.

Legman, G. (1962). Toward a motif index of erotic humor. *The Journal of American Folklore, 48*(75).

Marshall, C., & Rossman, G. (2006). *Designing qualitative research* (4th ed.). Sage Publications.

Matthews, B., & Ross, L. (2010). *Research methods: A practical guide for the social sciences*. University of Birmingham.

Mieder, W. (1993). *Proverbs are never out of reason: Popular wisdom in the modern age*. Oxford University Press.

Mills, M. A. (2008). What is theory? *Journal of Folklore Research, 45*(1). Indiana University.

Mullen, B. (1969). The function of magic folk belief among Texas coast fishermen. *The Journal of American Folklore, 82*(325).

Ododo, S. (2001). The theatrical aesthetics and functional values in Nigeria Ekuechi masquerade ensemble of the Ebira people. *Journal of Performing Arts, University of Ilorin, Nigeria*.

Okpewho, I. (1992). *African oral literature*. Indiana University Press.

Okpewho, I. (2004). *African oral literature: Background and character*. Indiana University Press.

Peoples, J., & Bailey, G. (1991). *Humanity: An introduction to cultural anthropology* (2nd ed.). West Publishing Company.

Propp, V. (1984). *Theory and history of folklore* (A. Y. Martin, P. Martin, & Others, Trans.; A. Liberman, Ed.). University of Minnesota Press.